# የሰማያዊው ሙሽራና የምድራዊቷ ሙሽሪት የወደፊት ቤት

ልቦቻችንን አሁን በእግዚአብሔር ፊት ዝቅ አድርገን፡ ለአፍታ ቆመን እንቆይ።

2 የሰማዩ አባታችን ሆይ፡ በጌታ በኢየሱስ ስም በአንድነት ተሰብስበን፡ ዛሬ እዚህ ለመገኘት ስላገኘነው እድል እናመሰግናለን። ትኩረታችንን ወደ ዘላለማዊ ነገሮች፡ እንዲሁም ከዚህ ሟቾች ከሚደርሱበት በላይ ወዳለው ህይወት ለመመለስ እዚህ ስለሆንን ሀጢያቶቻችንን ይቅር እንድትል እንጸልያለን። የተሰፋ ቃል የተሰጠንን ያንን ስፍራ ለማግኘት፡ እንዴት መዞር እንዳለብን፡ ወደፊት ምን ማድረግ እንዳለብን፡ እንዲሁም አሁን ባለንበት ሁኔታ፡ መመሪያዎችህን እንድትሰጠን… አሁን እንጸልያለን።

3 በምድሪቱ ውስጥ ብዙ የታመሙና የተቸገሩ አሉ፡ ጉዟቸውንም አላጠናቀቁም። ታላቁ ጠላታችንም፡ የኛ ጠላት ብቻ ሳይሆን፡ ነገር ግን ያንተ ጠላት የሆነው፡ ሊያጠቃቸው እ—እንዲሁም ህይወታቸውን ለማሰቆም፡ ያ—ያለጊዜያቸው ወደ መቃብር ሊልካቸው መጥቷል። ጌታ ሆይ፡ ዛሬ፡ በምህረትህና በጸጋህ፡ ቀኖቻቸውን ወደ ተመደበው ጊዜ እንድታራዝምላቸው፡ ስለእነርሱ እንጠይቅሃለን።

4 በመድረኩ ላይ፡ ወይም በፑልፒት ላይ፡ እዚህ መሀረቦችና ጨርቆች ተቀምጠዋል። እዚያ ውጪ በአዳራሾቹ ውስጥ እንዲሁም በዙሪያው፡ በአልጋዎች፡ በቃሬዛዎች ላይ ያሉ፡ የታመሙና የሚሰቃዩ፡ ለመቆም የሚያስችል በቂ አቅም ሳይኖራቸው በጉባኤው ውስጥ የቆሙ አሉ።

5 ዘላለማዊ አምላክ ሆይ፡ የተባረክህ ሆይ፡ በጌታ በኢየሱስ ደም፡ ዛሬ ጠዋት፥ ሀጢያታችንን ሳትመለከት፡ ነገር ግን እርሱ በእኛ ቦታ እንደቆመ፡ ለዚህም ጸሎት እኛን ወክሎ የሚጸልየው እርሱ እንደሆነ በማወቅ ጸሎታችንን ሰማ። ጌታ ሆይ፡ ለክብርህ እያንዳንዱ ሰው ይፈወስ።

6 እነዚህን መሀረቦች ባርካቸው። በታመሙት ሰዎች ላይ ሲደረጉ፡ እነርሱም ይፈወሱ።

7 አሁንም፡ አባት ሆይ፡ ከዚህ ቀጥሎ ይሆናል ብለን ወደምናምነው፡ ወደ ታላቁ የፈውስ አገልግሎት ከመግባታችን በፊት፡ ጌታ ሆይ፡ በቃልህ በኩል ምን ማድረግ እንዳለብን እናውቅ ዘንድ፡ የህይወትን መንገድ ቁረስልን። በኢየሱስ ስም እንጠይቃለንና። አሜን።

8 እንደ ሁልጊዜውም፡ በእግዚአብሔር ቤት መገኘትና ለህዝቡ መናገር፡ ከሁሉ የላቁ እድሎቼ መካከል አንዱ ሆኖ ይቆጠራል። አሁንም ቤቱ በጣም እንደተጨናነቀ አውቃለሁ፡ በጣም ረጅም ትምህርት አለኝ። ስለዚህ እኔ… መ—መልእክቱን እስክንጨርስ ድረስ፡ በተቻላችሁ መጠን፡ ምቾት እንደሚኖራችሁ እ—እምናለሁ።

9 አሁን፡ ይሞቃል፡ ነገር ግን ስለ አየር ማቀዝቀዣው ደስተኞች ነን። ነገር ግን፡ እንደዚህ አይነት መጠን ያለውን ቡድን፡ ሊቋቋመው የሚችል ምንም አይነት የአየር ማቀዝቀዣ አይኖርም፡ እያችሁ፡ ምክንያቱም የገዛ ስጋችሁ ሙቀት አመንጪ ነው፡ ዘጠና-ሰምንት ዲግሪ ያህል፡ ሁልጊዜም ሙቀትን ያወጣል፡ በዛ ላይ ተጠጋግታችሁ ተቀምጣችኋል። ነገር ግን በ—በተቻለው መጠን እግዚአብሔር ምቾት እንዲሰጣችሁ አምናለሁ።

10 እንደዚህ ባሉ በማስታወቂያ በተሰበሰበ ስብሰባዎች፡ ውስጥ ስንሆን፡ እ—እናንተን እንደሚረዳችሁ ባላሰብ ኖሮ፡ መልካም እንደሚያደርግላችሁና፡ በመምጣታችሁም፡ እንደምትጠቀሙበት ባላሰብ ኖሮ፡ በማንኛውም መንገድ፡ ወደዚህ እንድትመጡ አላደርግም ነበር። ከዚያም፡ ይህንን ለማድረግ ብዙ ጊዜ እንደሌለን፡ ወ—ወ—ወደ መጨረሻዎቹ ሰዓታት እየመጣን መሆናችንን በማወቅ፡ ለ—ለመንግስቱ ሰል፡ የምችለውን ያህል፡ እያንዳንዱን ደቂቃ ዋጋ ያለው ማድረግ እፈልጋለሁ። አሁንም በአንድነት ስንሰበሰብ ጌታ እግዚአብሔር እንደሚባርከን አምናለሁ።

11 ላመሰግናችሁ እፈልጋለሁ፡ ይህም፡ በሞቴሎች ውስጥ ያሉትን አንዳንድ የታመሙትንና የተጎዱትን ለማየት፡ ትላንትና፡ የተለያዩ ቦታዎች ሄጄ ነበር፡ በዚህ ሳምንት አንዳንድ ሰራ አስኪያጆችን ለማግኘት ችያለሁ፡ አንዳንድ የምግብ ቤቶችን ጭምር። ለምሳሌ፡ በዚህ ሳምንት እዚህ ያለውን፡ ራንች ሀውስ ሄጄ ነበር፡ ስንወጣም ሰራ አስኪያጁ እጄን እየጨበጠ ነበር። እንዲህም አለ፡ “ወንድም ብራንሃም፡” ብሎ ጠራኝ። እንዴት እንዳወቀኝ ገረመኝ። እንዲህም አለ…

እኔም፡ “ሰራ አስኪያጁ አንተ ነህ” አልኩት?

12 እርሱም፡ “ባለቤቱ ነኝ” አለኝ። ስለዚህም እንዲህ አለ፡ “አዎ፡ ህዝብህ ከዚያ ታች፡ ለመብላት ወደዚህ ይመጣሉ” አለኝ። እንዲህ አለ፡ “እነርሱ… ”

እኔም፡ “እንግዲህ፡ ያጨናነቁህ ይመስለኛል” አልኩት።

13 እርሱም፡ “ወዳጄ፡ ካየኋቸው ህዝቦች መካከል ከሁሉ የተሻሉት ናቸው” አለኝ። “በጣም ጥሩ ናቸው፡” አለኝ።

14 ላናግራት የፈለግሁትን አንዲት ወጣት ሴት ለማየት፡ ትላንትና ወደ አንድ ሞቴል ሄጄ ነበር፡ አባቷና እናቷ በቦታው ነበሩ፡ ያሉበትንም ሞ—ሞት-… ያሉበትን ክፍል ለማወቅ ወደ ሰራ አስኪያጁ መሄድ ነበረብኝ።

15 እርሱም፡ “አንተ ወንድም ብራንሃም ነህ” አለኝ? ያ እዚያ ኦክስ ውስጥ ነበር።

እኔም፡ “አዎ፡ ወዳጄ” አልኩት።

16 እርሱም፡ “እጅህን መጨበጥ እፈልጋለሁ” አለኝ። እንዲህ አለ… ከሚስቱ ጋር አስተዋወቀኝ፥ በጣም ጥሩ ባልና ሚስት ናቸው። እነርሱም፡ “በዚህ ሞቴል ውስጥ ያለው እያንዳንዱ ሰው አገልግሎቶችህን እየተካፈለ ነው። ለእነርሱ አሰይዘነዋል” አሉኝ። “ሌሎቹን ደንበኞቻችንን በሙሉ መለስናቸው፡” አሉ።

እኔም፡ “መልካም፡ ስለዚህ ነገር አመሰግናችኋለሁ” አልኳቸው።

17 እንዲህ አለ፡ “ወንድም ብራንሃም፡ ካየኋቸው ህዝብ መካከል እጅግ ጥሩ የሆኑት፡ ስብሰባዎችህን የሚካፈሉትና፡ ወደዚህ የሚመጡት ሰዎች ናቸው” አለኝ።

18 ትላንት ማታ እዚህ ታች ወዳለው ወዳጄ፡ ወደ ሚስተር ቤከር ሄጄ ነበር፡ ሳንድዊቾቹን ሁልጊዜ እወዳቸው ነበር። እርሱ በጣም... እርሱ፡ ልጅ ሳለሁ አውቀዋለሁ፥ በህይወቴ ሙሉ አውቀዋለሁ። ከዚያ ታች ከ—ከቀድሞው ሰፍራ፡ እዚያ ታች ከሪቨርሳይድ ሆቴል የመጡ ባልና ሚስት እዚያ ተቀምጠው ነበር። ስለዚህ እነርሱ... ሚስተር ቤከር፡ “ቢሊ” አለኝ?

19 እኔም፡ “ምንድነው፡ ሆሜር” አልኩት? እርሰ በርሳችን በጣም በደንብ እንተዋወቃለን።

እርሱም፡ “እዚያ ያሉትን ህዝብህን በሙሉ እመግባችኋለሁ” አለኝ።

20 በእያንዳንዱ እሁድ፡ ሁለት መቶ፡ ወይም እንደዛ የሚያክሉ፡ ብሉ ቦር ውስጥ ይበላሉ። በምሄድበትም ቦታ ሁሉ፡ ምን ያህል ጥሩ እንደሆናችሁ አስተያየቶችን እሰማለሁ።

21 ይህም ሰው፡ “እዚያ ታች ባለው በ—በሪቨርቪው፡” “ያ ሰፍራ ሁሉ ስብሰባውን በሚካፈሉ ሰዎች ተሞልቷል፡” አለ። እሱም፡ “መግባት የማይችሉ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ይኖራሉ” አለ።

22 ስለዚህ፡ እንደዚህ በመሆኑ፡ ለእኔ የምድር ጨው ናችሁ። እ—እንዲህ ላሉ ሰዎች የመሰበክ ዕድል እንዳለኝ በማወቄ እጅግ አመስጋኝ ነኝ ኃጢአተኞችም ሆኑ ሌሎች ሰዎች እንኳን ሳይቀሩ... እነዚህ ሰዎች ኃጢአተኞች ናቸው እያልኩ አይደለም፡ ነገር ግን ለማለት የፈለኩት፡ በንግድ ስራ ያሉትና የመሳሰሉት ሰዎች እንኳ፡ እናንተ ጥሩ ሰዎች መሆናችሁን መናገር ችለዋል፡ እንዲሁም በንግዳቸው ውስጥ፡ አካባቢያቸው ያደንቋቸዋል። ታውቃላችሁ፡ ጨዋማ መሆን ማለት ይህ ነው። ባህሪያችሁን፡ ለነገሮች የሚትጠነቀቁበትን መንገድ፡ ያንን አደንቃለሁ።

23 ሁልጊዜ፡ “አንድ ሰው መጥቶ፡ ሂሳቡን የሚከፍልበት ገንዘብ ከሌለው፡ ለኔ ደውሉልኝ” እላለሁ። አያችሁ? “የሆነ ነገር እናደርጋለን፡” አልኩት። “ገንዘብ ቢኖራቸውም ባይኖራቸውም፡ ሁልጊዜም መግቧቸው፡” አልኩት። አያችሁ፡ ምንም ነገር ማድረግ ይቻላል።

24 ልጆቼ እንደሆናችሁ ይሰማኛል። እ—እናንተ ኮከቦች... እዚያ ሰደርሰ አንድ ዘውድ የማገኝ ከሆነ፡ በአገልግሎቴ ዘ—ዘውድ ውስጥ፡ የምታንጸባርቁት ክፍል፡ ያ ዕንቁ እናንተ ትሆናላችሁ። ዘውድ ሲጫንልኝ፡ ያ ዕንቁ ትሆኑልኛላችሁ።

25 ባለፉት ጊዜያትም፡ ሰለ ሰባቱ ማህተሞች፡ ሰለ ቤተክርስቲያን ዘመናት፡ እንዲሁም እየሆኑ ሰላሉት ነገሮች፡ እ—እየነገርኳችሁ ነበር።

26 አሁንም፡ በዚህ ማለዳ፡ በጣም አስፈላጊ የሆነ ርዕሰ አዘጋጅቻለሁ፡ ለእኔ፡ እጅግ አስደሳች የሆነ ርዕሰ ነው፥ እናንተንም በዚሁ መንገድ እንደሚነካችሁ ተሰፋ አደርጋለሁ። መገለጡን በተቀበልኩበት በዚያው መንፈሰ ላካፍላችሁ ብችል ኖሮ፡ ድንቅ ይሆን ነበር፡ ነገር ግን ያንን ማድረግ የእግዚአብሔር ኃላፊነት ነው።

27 **የት** እና **ምን** እየተከናወነ እንዳለ ስነግራችሁ ቆይቻለሁ፡ እነዚህም ሁሉ ነገሮች ሲፈጸሙ እያየን ነው።

28 አሁን፡ ዛሬ ጠዋት፡ በዚህ፥ **የሰማያዊው ሙሽራና የምድራዊቷ ሙሽሪት የወደፊት ቤት** በሚል ርዕስ፡ የት እንደሚኖሩ እናገራለሁ። እንዲሁም፡ ደግሞ፡ በእግዚአብሔር ጸጋ ሁላችንም የዚያ ታላቅ የእግዚአብሔር እቅድ አካል እንደሆንን እምናለሁና።

29 አሁንም እ—እንደምትታገሱኝ አምናለሁ፡ መጽሐፍ ቅዱሳችሁን፡ በዕሮቻችሁን፡ ወይም አብራችሁኝ ለማንበብ የምትጠቀሙበትን ማንኛውንም ነገር ያዙ፡ ምክንያቱም ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን እጠቅሳለሁና። ለታመሙት ለመጸለይ በቂ ጊዜ እንዲኖረን ቶሎ ለመጨረስ እሞክራለሁ፥ ይህንንም ቃል ገብቻለሁ። ወደ ውስጥ ስገባ፡ ምንም ማድረግ ለማይችሉትና ተስፋ ለሌላቸው ሰዎች፡ ከመግባቴ በፊት ባለው አጭር ጊዜ፡ በክፍሎች ውስጥና በአካባቢው ላሉት ስጸልይ ነበር።

30 እንዲሁም፡ ጌታ ቢፈቅድ፡ በአስራ ስድስተኛው ቀን ሌላ አገልግሎት ሊኖረን ይችላል፡ ምናልባትም ለታመሙት የሚደረግ ጸሎት ብቻ ሊሆን ይችላል።

31 አሁን እረፍቴን እጀምራለሁ። ካለፈው ጥር ወር ጀምሮ፡ ስጓዝ ቆይቻለሁ፡ ወደዚህም እየተመለስኩ ነው። ጠዋት ቤተሰቤን ወደ ቱክሰን፡ መውሰድ ብቻ ነው የሚጠበቅብኝ፡ ከዚያም ጌታ ወደ ሌላ ስፍራ ካልመራኝ በስተቀር፡ ለሁለት ሳምንታት፡ ወይም ምናልባት ለሰባት ወይም ስምንት፡ ወይም አሥር ቀናት፡ በኬንታኪ ከሚገኙ፡ አንዳንድ ጓደኞቼ ጋር፡ አደን፡ እንዲሁም የሽኮኮ አደን እያደንኩ፡ ጊዜ ለማሳለፍ እመለሳለሁ። የት እንደምንሆን፡ ፈጽሞ አላውቅም፥ ያንን ፈጽሞ አናውቅም፡ ምክንያቱም ያ ያለው በእግዚአብሔር እጅ፡ በእግዚአብሔር እጅ ብቻ ነውና።

32 አሁን ለዚህ ታላቅ ርዕስ፡ እኛ—... በዚህ ላይ ጊዜ ብወስድበት፡ ብዙ ነገሮችን ማካተት ስለሚያስፈልግ፡ ሳምንታትን ይወስዳል፡ ብዬ እሰባለሁ። ሆኖም እንድታጠኑት በመተው፡ ዋና ዋና ነጥቦቹን ለመዳሰስ ያህል፡ አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችንና፡ ማስታወሻዎችን ጽፌያለሁ።

33 ከዚያም በቅርቡ፡ ምናልባት፡ ጌታ ቢፈቅድ፡ በጥቅምት ወር፡ መቼ እንደሆነ አላውቅም፡ ነገር ግን እርሱ ባዘጋጀው ጊዜ፡ ከዚህ ትምህርት ጋር ለማስተሳሰር፡ በራእይ ምዕራፍ 12 ላይ፡ ለ—ለተወሰኑ ቀናት፡ የተከታታይ ስብሰባ እንዲኖረን እፈልጋለሁ። ኦህ፡ ያ ታላቅ እንደሚሆን አምናለሁ። እንዲሁ ይሆናል። እርሱ እንዴት እንዳደረገው ማየት እጅግ አስደናቂ ይሆናል።

34 ከዚያም፡ አሁን በአንድነት ስንሰበሰብ፡ ትናንት ማታ፡ እንዲህ አልኩ፡ "ታውቃላችሁ፡ ስ... " በጠዋት፡ እንደማንኛውም፡ ጠዋት፡ "ወደዚህ ስመጣ፡ እዚያ ያሉትን ጓደኞቼን በሙሉ ስማቸውን በመጥራት እውቅና እሰጣለሁ" ብዬ አስቤ ነበር። አሁን ያንን እንዴት አደርገዋለሁ?

35 ጥሩ ጓደኛዬ፡ ዶክተር ሊ ቬይል፡ ከውድ ሚስቱና ሴት ልጁ ጋር ከኋላ ተቀምጠው፡ አብረውኝ እዚህ መገኘታቸው። ወንድም ሮይ ቦርደርስ፡ እንዲሁም፡ ወንድም ሩዴል፡ ወንድም ቢለር፡ ወንድም ፓልመር፡ እንዲሁም ወንድም ጃክሰን፡ እዚህ ናቸው። ኦህ፡ ማይ! የ—የ... ከልዩ ልዩ ስፍራዎች የመጡት፡ እነዚያ ውድ ወንድሞች! ወንድም አንቶኒ ሚላኖ፡ እንዲሁም፡ ኦህ፡ ወደየትኛውም አቅጣጫ

ብትመለከቱ፡ ሌላ ወንድም ታያላችሁ! ከታች ከአርካንሳስ የመጡት፡ ስማቸው ትዝ አይለኝም፥ ወንድም ጆን፡ ወንድም ኧርል ማርቲን፡ እንዲሁም ወንድም ብሌየር። እንዲሁም፡ ኦህ፡ ብቻ... እናንተ... ቁጥር ስፍር የለውም፡ እያችሁ። የእግዚአብሔርን ቃል ሳስተምር እንዲህ ዓይነት ህዝብ በዙሪያዬ በመሰብሰቡ በጣም ደስተኛ ነኝ፡ እነዚህም ጀግኖችና፡ እውነተኛ የእግዚአብሔር ሰዎች ናቸው ብዬ የማስባቸው ናቸው።

36 ስለዚህች ትንሽ ተበርናክል ደስተኛ ነኝ። ለሕዝብ ክፍት ስለሆኑት አምስት በሮቿም አመሰግናለሁ። እያንዳንዱ በር... በመንፈስ-የተሞሉ አራት ዲያቆናት፡ እዚህ አሉን፥ በመንፈስ-የተሞሉ፡ አራት ባለአደራዎችም አሉ። ይህ ማለት በእያንዳንዱ በር ላይ ሁለት ሁለት ናቸው። ከፊት ለፊቱ ደግሞ ለሁለቱ ፓስተሮች፡ ማለትም ለእረኞቹ የሚሆን፡ ባለ ሁለት በር አለው።

37 ስለመጣችሁ ደስ ብሎናል፥ ለዚህም እግዚአብሔርን እናመሰግናለን። እርሱም ለዘላለም ይባርካችሁ።

38 አሁን ለጥቂት ጊዜ እንቁም፡ ከሁለተኛ ጴጥሮስ 3ኛው ምዕራፍ፡ እንዲሁም ከራእይ መጽሐፍ 21 እናነባለን።

39 ጌታ ሆይ፡ ቆመን ሳለን፡ ቃልህን በማንበባችን ልባችንን በደስታ ሙላው፡ ይህም፡ ኢየሱስም፡ "ሰማይና ምድር ያልፋሉ፡ ቃሌ ግን አያልፍም" ያለውን በማወቅ እንጠይቅሃለን። ዳግመኛም፡ "መጽሐፍ ቅዱስ ሁሉ ሊፈጸም ይገባል" ማለቱን እናውቃለን። እነዚህንም ነገሮች ሰናነብ፡ ስለምንኖርበት ዘመን ከአንተ ዘንድ፡ ማስተዋል ይኑረን። የመጽሐፉ ደራሲ በሆነው፡ በኢየሱስ ስም እንጠይቀዋለን። አሜን።

40 ሁለተኛ ጴጥሮስ 3።

**ወዳጆች ሆይ፡ አሁን የምጽፍላችሁ መልእክት፡ ይህች ሁለተኛይቱ ናት፥ በቅዱሳን ነቢያትም ቀድሞ የተባለውን ቃል፥**

**በሐዋርያቶቻችሁም ያገኛችኋትን የጌታንና፡ የመድኃኒትን** ትእዛዝ **እንድታስቡ በሁለቱ እያሳሰብኋችሁ ቅን ልቡናችሁን አነቃቃለሁ፥**

**በመጨረሻው ዘመን እንደ ራሳቸው ምኞት የሚመላለሱ፡ ዘባቾች በመዘበት እንዲመጡ፡ ይህን በፊት እወቁ፡**

**እነርሱም፡ የመምጣቱ የተሰፋ ቃል ወዴት ነው**? (ይህ እዚያ ካለችው ከሃዲ ሴት ጋር ካልተገናኘ... )... **አባቶች ከሞቱባት ጊዜ፡ ከፍጥረት መጀመሪያ ይዞ ሁሉ እንዳለ ይኖራልና ይላሉ።**

**ሰማያት ከጥንት ጀምረው፡ ምድርም በእግዚአብሔር ቃል ከውኃ ተጋጥማ፡ በውኃ መካከል እንደ ነበሩ ወደው አያስተውሉምና፥**

**በዚህም ምክንያት፡ በዚያን ጊዜ የነበረው ዓለም፡ በውኃ ሰጥሞ ጠፋ፥**

አሁን ያሉ፡ **ሰማያትና ምድር ግን፡ እግዚአብሔርን የማያመልኩት ሰዎች እስከሚጠፉበት፡ እስከ ፍርድ ቀን ድረስ ተጠብቀው በዚያ ቃል ለእሳት ቀርተዋል።**

**እናንተ ግን፡ ወዳጆች ሆይ፡ በጌታ ዘንድ አንድ ቀን፡ እንደ ሺህ ዓመት፡ ሺህ ዓመትም እንደ አንድ ቀን እንደ ሆነ ይህን አንድ ነገር አትርሱ።**

**አሁን፡ ለአንዳንዶች የሚዘገይ እንደሚመስላቸው፡ ጌታ ስለ ተሰፋ ቃሉ አይዘገይም፥ ነገር ግን ሁሉ ወደ ንስሐ እንዲደርሱ እንጂ፡ ማንም እንዳይጠፋ ወዶ፡ ስለ እናንተ-ይታገሣል።**

**የጌታ ቀን ግን እንደ ሌባ ሆኖ ይመጣል፥ በ... በዚያም ቀን ሰማያትና** ምድር፡ በታላቅ ድምፅ... **በታላቅ ድምፅ ያልፋሉ፡ የሰማይም ፍጥረት በትልቅ ትኵሳት ይቀልጣል፡ ምድርም በእርሰዋም ላይ የተደረገው ሁሉ ይቃጠላል።**

**ይህ ሁሉ እንዲህ የሚቀልጥ ከሆነ፡ የእግዚአብሔር**ን **ቀን መምጣት እየጠበቃችሁና እያሰቸኰላችሁ፡**

**በቅዱስ ኑሮ እግዚአብሔርን**ም **በመምሰል፡ እንደ ምን ልትሆኑ ይገባችኋል? ስለዚያ ቀን ሰማያት ተቃጥለው ይቀልጣሉ የሰማይም ፍጥረት በትልቅ ትኵሳት ይፈታል፡**

**ነገር ግን፡ ጽድቅ የሚኖርባትን አዲስ ሰማይና፡ አዲስ ምድር፡ እንደ ተሰፋ ቃሉ እንጠብቃለን።**

**ስለዚህ፡ ወዳጆች ሆይ፡ ይህን እየጠበቃችሁ፡ ያለ ነውርና... ያለ ነውርና፡ ያለ ነቀፋ ሆናችሁ፡ በሰላም በእርሱ እንድትገኙ ትጉ።**

**የጌታችንም ትዕግሥት መዳናችሁ እንደ ሆነ ቍጠሩ፥ እንዲህም የተወደደው ወንድማችን... ጳውሎስ... ደግሞ እንደ ተሰጠው ጥበብ መጠን ጻፈላችሁ፥**

**እንዲሁም... በመልእክቱም ሁሉ፡ ደግሞ እንደ ነገረ ስለዚህ ነገር ተናገረ፥... በእነዚያ ዘንድ ለማሰተዋል የሚያሰቸግር ነገር አለ፡ ያልተማሩትና፡ የማይጸኑትም ሰዎች፡ ሌ—ሌሎችን መጻሕፍት እንደሚያጣምሙ፡ እነዚህን ደግሞ ለገዛ ጥፋታቸው ያጣምማሉ።**

**እንግዲህ እናንተ፡ ወዳጆች ሆይ፡ ይህን አሰቀድማችሁ ሰለምታውቁ፡ በዓመፀኞቹ ስሕተት፡ ተሰባችሁ... ከራሳችሁ፡ ጽናት እንዳትወድቁ... ተጠንቀቁ።**

**ነገር ግን በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ፡... ጸጋና እውቀት እደጉ። ለእርሱ አሁንም እሰከ ዘላለምም ቀን ድረስ ክብር ይሁን። አሜን።**

41 አሁን በ—በክርስቶስ መገለጥ፡ በ 21 ኛው ምዕራፍ ላይ፡ እነዚህን ቃላት አነባለሁ።

**አዲስ ሰማይንና አዲስ ምድርንም አየሁ፥ ፊተኛው ሰማይና ፊተኛይቱ ምድር አልፈዋልና፥ ባሕርም ወደ ፊት የለም።**

**ቅድስቲቱም ከተማ፡ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም፡ ለባልዋ እንደ ተሸለመች ሙሽራ ተዘጋጅታ፡ ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስትወርድ አየሁ።**

**ታላቅም ድምፅ ከሰማይ፡ እነሆ፡ የእግዚአብሔር ድንኳን በሰዎች መካከል ነው፡ ከእነርሱም ጋር ያድራል፡ እነርሱም ሕዝቡ ይሆናሉ፡ እግዚአብሔርም እርሱ ራሱ ከእነርሱ ጋር ሆኖ፡ አምላካቸው ይሆናል።**

**እንባዎችንም ሁሉ ከዓይኖቻቸው ያብሳል፥ ሞትም ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፡** ኀዘንም **ቢሆን፡ ወይም ጩኸት፡ ወይም ሥቃይ ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፥ የቀደመው ሥርዓት አልፎአልና** ብሎ **ሲናገር ሰማሁ።**

**በዙፋንም የተቀመጠው፡ እነሆ፡ ሁሉን አዲስ አደርጋለሁ አለ!... ለእኔም፡ እነዚህ ቃሎች የታመኑና እውነተኛዎች ናቸውና፥ ጻፍ አለኝ።**

**አለኝም፡ ተፈጽሞአል። አልፋና ዖሜጋ፡ መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ። ለተጠማ ከሕይወት ውኃ** ምንጭ **እንዲያው እኔ እሰጣለሁ።**

**ድል የሚነሣ ይህን ይወርሳል፥ አምላክም እሆነዋለሁ፡ እርሱም ልጅ ይሆነኛል።**

እንደገና እንጸልይ።

42 ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ ኢየሱስ ራሱና ሐዋርያው እየተቃረብን ስላለው ዘመን በሰጡን እንዲህ ባለ የተሰፋ ቃልና እንዲህ ባለ ጥብቅ ንግግር መሰረት፡ በትክክለኛው መንገድ እንዴት መቅረብ እንዳለብን እናውቅ ዘንድ፡ ጌታ ሆይ፡ መመሪያህን፡ ሰጠን። ምክንያቱም፡ እንደሚመጣ፡ እናውቃለንና። መጽሐፍ ቅዱስ ሊፈጸም ይገባዋል፡ እንዲሁም ይሆናልና። አሁንም፡ ጌታ ሆይ፡ ቃልህን ስናጠና፡ እንደገና ምሕረትህን በሁላችን ላይ እንጠይቃለን። ጌታ ሆይ፡ ከእኛ ጋር ሁንልን ግለጥልንም፡ በኢየሱስ ስም እንጠይቃለንና። አሜን።

መቀመጥ ትችላላችሁ።

43 አሁን፡ ምናልባት፡ የዋናው አዳራሽ መብራቶችን አጥፍተው፡ እዚህ መድረኩ ላይ ያሉትን ብቻ የሚተውበት መንገድ ይኖር ይሆን ብዬ አስባለሁ፡ ይህም የተሻለ ይሆናል፡ የኤሌክትሪክ ኃይሉንም ይቀንስለታል። በቀደም ምሽት፡ ትራንስፎርመሩን ልናቃጥለው ምንም አልቀረንም ነበር። ጠባቂውም ይሄንን ቢያደርግልን፡ የታችኛውን መብራቶች፡ ማለትም የዋናውን አዳራሽ መብራቶችን፡ ቢያጠፋልን ደስ ይለናል። ከዚያም ለማየት፡ ለመጻፍም በቂ ብርሃን እንደሚኖራችሁ አስባለሁ።

44 አሁን፡ እንደገና፡ ርዕሱን ለማሳወቅ ያህል፡ ዛሬ እየቀረብን ያለነው ር—ርዕስ እንዲህ ነው፥ **የሰማያዊው ሙሽራና የምድራዊቷ ሙሽሪት የወደፊት መኖሪያ ቤት**።

45 አሁን... ይህንን ማድረግ ግድ ይለኛል። እዚህ ጋር በጣም ይሞቃል፡ አያችሁ። አዎን፡ ወዳጄ። እኛ... ባለቤቴ ይህንን እንዳደርግ እንደማትወድ

አውቃለሁ፥ ነገር ግን፡ ኮቴን፡ ማውለቅ አለብኝ። እዚህ እጅግ ይሞቃልና። እያችሁ፡ እናንተ እዚያ አየር ታገኛላችሁ፡ እዚህ ግን ትንሽ ጥግ ላይ ተዘግቷል፡ እያችሁ። አሁን፡ ወ—ወደፊት፡ ወይም...

46 ከዚህ በፊት፡ ማለትም፡ ባለፉት ጊዜያት **ሰባቱን ማኅተሞችና፡ ሰባቱን አብያተ ክርስቲያናት አጥንተናል።** ወንድም ቬይልና ሌሎቹም እነዚያን በመጽሐፍ መልክ ለማዘጋጀት አሁን፡ በታማኝነት፡ እየሰሩባቸው ነው።

47 እነዚህን ሲፈጸሙ ያየናቸውን ሚስጥራዊ ነገሮች ሁሉ ስናይ፡ ያንን ከተረዳን በኋላ፡ አሁን በምንኖርበት፡ ዘመንና፡ ባለንበት ሁኔታ፥ ማንም በትክክል ቁጭ ብሎ በጥንቃቄ የተነገረውን እንደሚሆን ተሰፋ የተሰጠውን፡ እንዲሁም የሆነውን ከመረመረ በኋላ፡ እነዚህ ነገሮች ተፈጽመዋል ከማለት ውጪ፡ ሌላ የሚል አይኖርም ብዬ አስባለሁ። እያችሁ? እግዚአብሔር አደርገዋለሁ ያለውን፡ ልክ በቃሉ መሰረት በትክክል አድርጎታል። እያችሁ?

48 አሁን፡ በዚህ ላይ ሳስብ፡ እንግዲህ፡ ጌታ ኢየሱስ በምን ሰዓት ሊገለጥ እንደሚችል ስለማናውቅ፡ ይሄኛው ጥሩ ይሆናል ብዬ አሰብኩ፡ ከዚያም፡ በዚህ ላይ ብንነጋገር ለመንፈስ ቅዱስም ደስ የሚያሰኝ መሰሎ ታየኝ፥ ይህንንም ሁሉ አውጥቼ ለማስረዳት በቂ ጊዜ ስለማይኖረኝ፡ ምናልባትም ወደዚሁ፡ ሁለት ወይም ሦስት ጊዜ ልንመለስ እንችላለን።

49 ለአንድ ሰው ትንሽ ማሰናከያ ሊሆን የሚችልን ር—ርዕስ ስታነሱ፡ ግልጽ ለማድረግ እስከ መጨረሻው ይዛችሁት መሄድ ስለማትችሉ፡ ቀጣዩን ርዕስ ለመያዝ እንደገና ትመለሳላችሁ።

50 ከዚያም በኋላ፡ በ... ጌታ ቢፈቅድ፡ ወደ 12ኛው ማኅተም እንገባለን፡ ወይም አይደለም... ይቅርታ አድርጉልኝ። በጌታ መምጣትና በመለከቶቹ ፍጻሜ መካከል ወዳለውና፡ ወደመሳሰሉት፡ ወደ ራእይ ምዕራፍ 12 እንመጣለን። ሰይጣን ማን እንደሆነ፡ ምን እንዳደረገ፡ ከየት እንደመጣ፡ አላማው ምን እንደሆነ፡ የተሰጠውም ታላቅ ውበቱ እንዴት ለመውደቁ ምክንያት እንደሆነ፡ ለማሳየት ያንን አምጥተን ለማስረዳት እንሞክራለን። አታላይነቱ ለመውደቁ ምክንያት ሆነ፥ ውበቱ።

51 እንግዲህ፡ ያንን የእባብ "ዘር" በትክክል ማየት ለሚፈልግ ለማንኛውም ሰው፡ እንዴት የማይቻል እንደሆነ እንጃ። ይኸውላችሁ፡ ማንኛውም ሰው ጋር፡ መወራረድ እፈልጋለሁ፡ በ—በተራ የጋራ ግንዛቤ፡ ማየት የሚፈልግ ከሆነ ማለት ነው። ህጻን እንኳ ሊያየው ይችላል። እያችሁ? አሁን፡ በኋላ ላይም ወደዚያ እንመለስበታለን።

52 አሁን፡ እዚህ ጋር እንደምንረዳው እነዚህ ሁለት ጥቅሶች... ሁለተኛ ጴጥሮስ ምዕራፍ 3ን ያነበብኩበት፡ ከራእይ 21 ጋርም ያነጻጸርኩበት ምክንያት፡ ሁለቱም እዚህ ጋር የሚናገሩት ስለ አንድ ዓይነት ርዕስ ነው፡ ነገር ግን ዮሐንስ እንደ ጴጥሮስ አድርጎ በ—በፍጹም አላብራራውም። እያችሁ? ይህ ታላቅ የሙሽራይቱ መኖሪያ እዚሁ ምድር ላይ እንደሚሆን እንረዳለን።

53 አሁንም ልክ ምዕራፍ 21ን፡ ራእይ 21ኛው ምዕራፍ፡ ብታነቡ፡ ሐዋርያው እዚህ ጋር፡ ወይም ነቢዩ፡ "አዲስ ሰማይና አዲስ ምድርን አየሁ፡" ይላል። ሙሉ በሙሉ መጥፋት እየመጣ ያለ ይመስላል።

54 አሁን፡ ሁልጊዜ መልእክቶቼን የማገኝበት መንገድ በጸሎት ነው። በጸሎት እቀመጣለሁ አንድ ነገርም ይገለጥልኛል። ለጥቂት ደቂቃዎችም እጠብቀዋለሁ ትክክል መሆኑንም እያለሁ፡ ከዚያም በደንብ እንደቀረበኝ ይሰማኛል። ከዚያም አንዳንድ ጊዜ ወደ ራእይ እስኪለወጥ ድረስ መጠበቄን እቀጥላለሁ። ነገር ግን መምጣት ሲጀምር፡ ከእግዚአብሔር እንደመጣም ስረካ፡ ያኔ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ እሄዳለሁ። አያችሁ፡ ያ፡ ለሚደረገው መንፈሳዊ ነገር ሁሉ ማረጋገጫ መሆን አለበት፡ ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ የኢየሱስ ክርስቶስ ሙሉ መገለጥ ነው፥ አያችሁ፡ የእርሱ አካል ነው።

55 አሁንም፡ በዚያ ውስጥ፡ ምናልባት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ልክ ያልመሰለኝን ቦታ ሳገኝ፡ እገረማለሁ። ደግሜ ወደ ጸሎት እመለሳለሁ። እንደገና ይመጣል። ከ—ከዚያም መጽሐፍ ቅዱሴን መ—መመርመር እጀምራለሁ።

56 አሁን፡ መጽሐፍ ቅዱሳችን በእንግሊዝኛ የተጻፈ ነው፡ የእንግሊዝኛ ቃላት ደግሞ፡ ሁልጊዜ ይቀያየራሉ። ለምሳሌ፡ ልክ እንደ ዮሐንስ ወንጌል 14፡ "በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያዎች አሉ፡" እንዳለው፡ ቤት ውስጥ ያለው መኖሪያ ማለት ነው። እንግዲህ፡ እንደዛ ከሆነ፡ እናንተ፡ በዚህ ማድረግ ያለባችሁ፡ ወ—ወደ መጀመሪያው መልሳችሁ ጄምስ ምን ማለቱ እንደነበር ማየት ነው፡ ወይም ወደ ዕብራይስጡ፡ ወይንም ወደ መጀመሪያው ትርጉም ወደሆነው፡ ወደ ግሪኩ መመለስ አለባችሁ። በዚያም፡ "በአባቴ መንግሥት ብዙ ቤተ መንግሥቶች አሉ" ይላል። እንግዲህ፡ እንደዛ ከሆነ፡ ተርጓሚዎች ለንጉሥ ጄምስ ወደ ተረጎሙበት ጊዜ ስትመለሱ፡ በዚያን ጊዜ **መንግሥት፡** በእንግሊዝኛ፡ "ቤት" ተብሎ ይጠራ ነበር፡ ንጉሡም በሹማምንቶቹ ላይ እንደ አባት ነበር። "በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያዎች አሉ፡" ብለው የተረጎሙበት ምክንያት ይህ ነው። አያችሁ? ከዚያም እነዚያን ቃላት ታገኛላችሁና መፈለግም ይኖርባችኋል።

57 ከዚያም፡ አያችሁ፡ ከዚያ መነቃቃት... ይህ መድረክ ዛሬ ጠዋት፡ እነግራችኋለሁ፡ አንድም ጊዜ በቀጥታ ከመጽሐፍ ቅዱስ በቀር፡ ሌላን ነገር አስተምሮ አያውቅም። **የእባብ ዘርና** እነዚህ ሌሎች ነገሮች ሁሉ የመጡት እንዲሁ ነው። አያችሁ? በ...

58 እናም፡ በእርግጥ፡ አንድ ሰው እንዲሁ ዝምብሎ አንብቦ፡ "በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያዎች አሉ" ቢል፡ ለማጥናትና ለመጸለይ፡ ጊዜ ካልወሰዳችሁ፡ ሙሉ በሙሉ ግራ ትጋባላችሁ። አያችሁ? ነገር ግን መጸለያችሁን ቀጥሉ። ከእግዚአብሔር የመጣ ከሆነ፡ እግዚአብሔር ሁልጊዜ ትክክል ያደርገዋል።

59 አሁን፡ ዮሐንስ ለውጡንና መ-... እንዴት እንደሚመጣ ያብራራል... ማለቴ፡ እሱ አያብራራውም፡ ነገር ግን ጴጥሮስ ያብራራዋል። ዮሐንስ እንዲሁ፡ "አዲስ ሰማይንና አዲስ ምድርን አየሁ፥ ፊተኛው ሰማይና ፊተኛይቱ ምድር አልፈዋልና። ባሕርም ወደ ፊት የለም። እኔም ዮሐንስ ቅድስቲቱ ከተማ ከእግዚአብሔር ዘንድ ከሰማይ፡ ለባሏ እንደ ተሸለመች ሙሽራ ተዘጋጅታ ስትወርድ አየሁ" አለ። ነገር ግን፡ ጴጥሮስ ይህ ሂደት እንዴት እንደሚመጣ ስለሚያብራራ፡ ይህንን ለማወቅ አሁን ወደ ሁለተኛ ጴጥሮስ እንመለሳለን። አሁን፡ ዮሐንስ ያለውን ብትመለከቱ፡ እንደዚህ ያለ ይመስላል፡ "ፊተኛው ሰማይና ፊተኛይቱ ምድር አልፈዋልና፡" ሙሉ በሙሉ ጠፍተዋል። አያችሁ፡ እንደዛ ከሆነ፡ ያ በጣም እንግዳ ይመስላል። ስለዚህ ትኩረቴን የሳበው ይሄ ነው፡ እኔም "አልፈዋልና፡"

የሚለውን ቃል መፈለግ ጀመርኩ። አሁንም፡ ነገር ግን ሁለቱም፡ ሐዋርያውና ነቢዩ፡ ስለ ተመሳሳይ ነገር ይናገሩ እንደነበር፡ ግልጽ ነው።

60 አሁንም፡ ደግሞ፡ በኢሳይያስ መጽሐፍ፡ አሁን፡ እነዚህን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች መጻፍ የምትፈልጉ፡ በኢሳይያስ 65፥17 ላይ ይገኛል። ኢሳይያስ፡ ስለ ሚሊኒየሙ፡ ለ—ለእግዚአብሔር ሕዝብ ስለሆነው ስለዚያ ስለ ሺህ አመት እረፍት እየተናገረ ነበር። ኢሳይያስ ስለዚህ ተናገረ፡ እንዲህም አለ፡ "እኔ... አንድ ነገር ነበረ... የፊተኛው ነገር ሁሉ አልፏል፡" ቤቶችን እንዴት እንደሚሠሩ፡ በእነርሱም ውስጥ እንዴት እንደሚኖሩ። ጊዜ ቢኖረን... ምናልባት ትንሽ ጊዜ ወስደን ይህንን ለጥቂት ደቂቃ እ—እናነበዋለን፡ ኢሳይያስ 65 ላይ፡ እስቲ ይህንን ለጥቂት ደቂቃዎች እናንብበው። ለኛም ያለው፡ ትክክለኛው ነገር፡ እዚህ አለ። አሁን፡ ለመጀመር፡ ኢሳይያስ 65፥17።

እነሆ፡ **አዲስ ሰማይና፡ አዲስ ምድር እፈጥራለሁና፥...**

61 አሁን፡ ነቢዩ፡ ኢሳይያስ፡ ሙሉውን መጽሐፍ ቅዱስ በትክክል በትንቢቱ ውስጥ ከጻፉት ነቢያት አንዱ ነበር። እርሱም በፍጥረት ይጀምራል፥ በመጽሐፉ መካከል፡ በ40ኛው ምዕራፍ አካባቢ፡ ስለ መጥምቁ ዮሐንስ፡ ስለ አዲስ ኪዳን ያወራል፥ በመጽሐፉ፡ በራእይ፡ በሚሊኒየም ውስጥ፡ ያጠቃልለዋል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስልሳ-ስድስት መጻሕፍት አሉ፥ በኢሳይያስም ውስጥ ስልሳ-ስድስት ምዕራፎች አሉ። ሙሉ ማብራሪያ ጽፏል።

62 አሁን፡ እዚህ ጋር 65ኛውን ምዕራፍ ሲጽፍ፡ እናገኛለን፡ ለመጨረስ አንድ ምዕራፍ ይቀረዋል፡ እርሱም ስለ ሚሊኒየሙ ይናገራል። አስተውሉት፡ እንዴት ያማረ ነው።

> **... እነሆ፡ አዲስ** ሰማይና... **አዲስ ምድር እፈጥራለሁና፥ የቀደሙትም አይታሰቡም፡ ወይም ወደ ልብም አይገቡም።** ("ያልፋል።")
>
> **ነ—ነገር ግን በፈጠርሁት ደስ ይበላችሁ... ለዘላለምም ሐሤት አድርጉ፥ እነሆ፡ ኢየሩሳሌምን ለሐሤት፡ ሕዝብዋንም፡ ለደስታ፡ እፈጥራለሁና።**
>
> **እኔም በኢየሩሳሌም ሐሤት አደርጋለሁ፡ በሕዝቤም ደስ ይለኛል፥ ከዚያም ወዲያ የልቅሶ ድምፅና፡ የዋይታ... ድምፅ አይሰማባትም።**
>
> **ከዚያም ወዲያ... ጥቂት ዘመን ብቻ የሚኖር ሕፃን፡ ወይም... ዕድሜውን ያልፈጸመ ሽማግሌ አይገኝም፥ ጕልማሳው የመቶ ዓመት ሆኖት ይሞታልና፥ ኃጢአተኛውም የመቶ ዓመት ሆኖት የተረገመ ይሆናልና።** ከዚያም...
>
> **ቤቶችንም ይሠራሉ፡ ይቀመጡባቸውማል፥ ወይኑንም ይተክላሉ፡ ፍሬውንም ይበላሉ።**
>
> **ሌላ እንዲቀመጥበት፡ አይሠሩም፥** (ማለትም፡ እርሻህን፡ ልጅህ፡ ወይም ከወራሾችህ መካከል አንዳንዶቹ ይወርሳሉ)... **ሌላም እንዲበላው፡ አይተክሉም፥** (ራሳቸው ይተክላሉ በዚያም ይኖራሉ፥ የዘላለም ሕይወትን ያገኛሉ)... **የሕዝቤ ዕድሜ እንደ ዛፍ ዕድሜ**

**ይሆናልና፡** እኔም... **የመረጥኋቸው በእጃቸው** *ሥራ* **ረጅም ዘመን ደስ ይላቸዋልና።**

**እነርሱ ከነልጆቻቸው፡ የእግዚአብሔር ቡሩካን ዘር ናቸውና፥ በከንቱ አይደክሙም፡ ለጥፋትም አይወልዱም።**

63 አሁን አስተውሉ፡ ከአፍታ በኋላ፡ ወደዚህ እመጣለሁ።

**እንዲህም ይሆናል፡ ሳይጠሩ፡ እመልስላቸዋለሁ፥ ገናም ሲናገሩ፡ እሰማለሁ።**

**ተኩላና ጠቦት በአንድነት ይሰማራሉ፡ አንበሳም እንደ በሬ ገለባ ይበላል፥... የእባብም መብል ትቢያ ይሆናል። በተቀደሰው ተራራዬ ሁሉ አይጐዱም አያጠፉምም፡ ይላል እግዚአብሔር።**

64 እነዚህ ነቢያትና ታላላቅ ጠቢባን፡ የመጽሐፍ ቅዱስ መምህራን፡ ድሮ በጥንት ዘመን የነበሩት፡ ይህ ክቡር ዘመን ሲመጣ ማየታቸው፡ እንዴት ያለ የተሰፋ ቃል ነው!

65 አንድ ሰው፡ ከእነዚህ ምንባቦች በመነሳት፡ የዚህች ምድር ፕላኔት፡ ሙሉ በሙሉ እንደምትጠፋ፡ "አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር እፈጥራለሁ" ስላለ፡አያችሁ፡ ሰማያት እንደሚያልፉና፡ ምድርም እንደሚያልፍ፡ ሙሉ በሙሉ እንደሚጠፋ አድርጎ ሊያስብ፡ ወይም ይልቁንም፡ እንዲያምን ሊመራ ይችላል። ዳሩ ግን በቅርበት ስናጠና፡ በመንፈስ ቅዱስም እርዳታ፡ የዚህን እውነት ማየት እንችላለን፥ አሁን የምንገባው ወደዚህ ነው።

66 የሚጠፋው፡ በዙሪያዋ ያለው ድባብ፡ እና በምድር ላይ ያለው ኃጢአት ብቻ ነው። አያችሁ? አሁን፡ **ሰማያት** ማለት "ከላይ ያሉት አትሞስፌሮች" ማለት እንደሆነ እንገነዘባለን። አያችሁ?

67 ምን ያደርጋል? ይህም... ከዚያም እነዚህ አሜከላዎች፡ በሽታዎች፡ ሞት፡ ፖለቲካ፡ ኃጢአተኛ ወንድ፡ ኃጢአተኛ ሴት፡ እንዲሁም እርኩሳን መናፍስት ሁሉ፡ ተወግደው ይጠፋሉ። አያችሁ? ያ በዚያ መንገድ መሆን አለበት፡ ምክንያቱም እኛው እዚሁ ልንኖር ነውና። ያንንም በመጽሐፍ ቅዱስ እናረጋግጠዋለን። የምንኖረው ልክ እዚህ ላይ ነው። አሁን አስተውሉ፡ አሜከላዎች፡ ጀርሞች፡ በሽታዎችና ነገሮች ሁሉ፡ ሙሉ በሙሉ ይወገዳሉ። ይህ ሁሉ፡ አሁን በምድር ላይ ያለው ህልውና፡ የሰው-ሰራሽ ስርዓቶች፡ ፖለቲካ፡ ኃጢአት፡ ዓለም የተበከለበት ልዩ ልዩ እርኩሳን መናፍስት ሁሉ፡ በዚህ ውስጥ ያሉት በላያችን ያሉት ሰማያት ሁሉ፡ በርኩሳን መናፍስት ተበክለዋል። አሁን በዚህ ውስጥ፡ ጠለቅ ብለንና ረዘም ላለ ጊዜ እንሄዳለን፡ አያችሁ።

68 ይህ ሁሉ አሁን ባሉት ሰማያት፡ ወይም አትሞስፌሮች፡ እንዲሁም በምድር ውስጥ ይኖራል። ይህች ምድር እነዚያን ነገሮች ይዛለች፡ ነገር ግን ለዚያ ዓላማ አልተፈጠረችም። እንዲህ እንድትሆን ያደረጋት ኃጢአት ነው። አያችሁ? የተፈጠረችው፡ በፈጣሪ በእግዚአብሔር ነው። ግን ሁሉም...

69 አሁን የምንኖርባቸው፡ *ሥጋዎቻችን* በሙሉ፡ እግዚአብሔር ምድርን ሲፈጥር በምድር ላይ ተቀምጠዋል፡ ምክንያቱም እናንተ ከምድር አፈር ናችሁና። ሁሉም እዚህ ተዘርግቶ ነበር። እግዚአብሔር ራሱ ሲፈጥረው፡

በእርሱ አሳብ ውስጥ ነበራችሁ። በታላቁ ዘላለማዊ፡ በእርሱ ውስጥም፡ ባህርዩ የሆነው፡ አሳብ ነበረ።

70 አሁንም ኃጢአት ይህ ሁሉ እንዲሆን አደረገ። እግዚአብሔርም፡ በዚህ ዘመን ውስጥ፡ የራሱን ንብረት እየሰበሰበ ነው።

71 ሰይጣን አሁንም እዚህ አለ። ይህ ሁሉ ሊሆን የቻለበት ምክንያትም ይኸው ነው። እርሱ አሁንም እዚህ አለ፡ ክፉ ሠራዊቶቹም ሁሉ አሁንም እዚህ አሉ። አስተውሉ፡ ምድር አሁን በጣም የረከሰችው ለዚህ ነው። ለዚህ ነው አሳፋሪና አስቂኝ ነገሮች የሚቀጥሉት፥ ደም መፋሰስ፡ ጦርነት፡ ፖለቲካ፡ ኃጢአት፡ ምንዝርና፡ ሁሉም ዓይነት ርኩሰቶች የሚቀጥሉት፡ ሰይጣን የዚች ምድርና የዚህ አትሞስፌር ገዥ ስለሆነ ነው።

"አትሞሰ-... ፡" ትሉ ይሆናል? አዎ፡ ወዳጄ!

72 ሰማያትም ሆኑ ምድር አሁን በእግዚአብሔር ፊት ሊከሱን በሚችሉ አጋንንቶች ተበክለዋል። ኢየሱስም ስለ እኛ ሊማልድ በዚያ አለ። አያችሁ? ከሳሾቹ ጣታቸውን እየጠቆሙ፡ "**ይህን** አደረጉ፡ **ይህን** አደረጉ፡ **ይህን** አደረጉ" እያሉ ቢቀጥሉም፡ ዳሩ ግን ደሙ አሁንም ይሸፍናል። አስቀድሞ ያያቸውን እነዚያን የተመረጡትን ሊቤዣቸው መጣ። ዛሬ በጣም የረከሰችው ለዚህ ነው።

73 እዚህ፡ ሐዋርያው፡ እዚህ በሁለተኛ ጴጥሮስ፡ በምዕራፍ 2፡ በ5ኛውና በ... በ5ኛውና 6ኛው ቁጥር ላይ ይናገራል። አዎ፡ አገኘቼዋለሁ። እሱም ስለ ምድር ሦስት ደረጃዎችን ይጠቅሳል። አያችሁ፡ ሦ—ሦስት ደረጃዎቿን ይናገራል። እንዴት እንደሚያመጣቸው አስተውሉ።

74 "የቀድሞ ዓለም ከውኃ ውስጥ ወጥታ ቆመች፡" አሁን፡ ያችህ ከጥፋት ውኃ በፊት የነበረችው ዓለም ነበረች።

75 አሁን፡ ያለው፡ አሁን የምንኖርበት የአሁኑ ዓለም፡ "ዓለም" ብሎ ጠራው።

76 "ከውኃ ወጥቶ የቆመው የቀድሞ ዓለም፡" ዘፍጥረት 1፥1 ያለው አለ። ደግሞም አሁን ያለው "ዓለም" አለ። ከዚያም፡ እንደገና፡ "ሊመጣ ስላለው ዓለም፡" አዲሱ ዓለም በማለት፡ ወደ ሌላ ይጠቅሳል። ሦስት ዓለማት፥ ሦስት የዓለም ደረጃዎች አሉ።

77 እግዚአብሔርም የቤዛነት ዕቅዱን ለእኛ እንዴት ግልጽ እንደሚያደርግልን አስተውሉ። ኦህ፡ አሁን እዚህ የቤዛነት ዕቅዱን ለእኛ እንዴት ግልጽ እንደሚያደርግልን፡ ይህን ሳየው ነፍሴን እጅግ አስደስታት። አሁን በገዛ ዓይኖቻችን የምናየውን ነገር አነጻጽሩት። እግዚአብሔር ዓለሙን ለመዋጀት ያደረገውን፡ ሕዝቡን ለመዋጀትም ያንኑ ዕቅድ ተጠቅሟል፡ የማይለወጠው እግዚአብሔር በማንኛውም ዕቅዶቹም ሆነ በምንም ነገር አይለወጥምና። እንዴት ያለ ክቡር ነገር ነው!

78 ወደ ዓለም ለመምጣት፡ ዓለምን በሦስት ደረጃዎች እንደመራት፡ እኛንም በሦስት የጸጋ ደረጃዎች፡ ወደ ራሱ፡ በውስጣችን ወዳለው ማደሪያ፡ እንዴት እንደመራን ተመልከቱ። ዓለም ሦስት የተለያዩ የመንጻት ደረጃዎችን ካለፈች በኋላ እግዚአብሔር ወደ ዓለም እንደሚመጣ፥ በተመሳሳይ ሁኔታ በሦስት የጸጋ

ደረጃዎች ወደ እኛ ይመጣል። ይህን በመጀመሪያ አስተምሬዋለሁ፥ ከዚያን ጊዜ ጀምሮም፡ ፈጽሞ አልለወጥኩም። የእግዚአብሔር ቃል ነው።

79 ሦስቶቻችሁን፡ ሰባቶቻችሁን፡ አሥራ ሁለቶቻችሁን በአንድነት ማቆየት አለባችሁ። የመጽሐፍ ቅዱስ ቁጥሮች ፍጹም ሆነው መሄድ አለባቸው አለበለዚያ ምስላችሁ ሁሉ ይደባለቅባችኋል። ልትረዱት ካልቻላችሁ፡ መጸለይን ብቻ ቀጥሉ። ተመልከቱ፡ በትክክል፡ ይገጠማል። እግዚአብሔር በሦስቶች ፍጹም ሆኗል። አያችሁ?

80 አስተውሉ፡ ከጥፋት ውኃ በፊት የነበረው፡ “የቀድሞ ዓለም”፥ አሁን ያለው “ዓለም”፥ ሊመጣ ያለው...

81 አሁን፡ እርሱ ወደሚያመጣን የመጀመሪያው ደረጃ... አያችሁ፡ የቤዛነት ዕቅዱ በሁሉም ነገር በትክክል አንድ ዓይነት ነው። ያንኑ ዘዴ ይጠቀማል። ፈጽሞ አይለወጥም። በሚልክያስ 3 ላይ፡ “እግዚአብሔር ነኝ፡ አልለወጥም፡” ብሏል። ስለዚህ፡ የሚያደርግበት መንገድ፡ ያዳነውን የመጀመሪያውን ሰው ያዳነው፡ ንጹሕ በሆነው በአንዱ ደም መፍሰስ ከሆነ፡ ቀጣዩንም ማዳን አለበት፡ የሚያድነውንም እያንዳንዱን ሰው በዚያው መንገድ ማዳን ይኖርበታል።

82 በሕይወት ጉዞ ውስጥ በማንኛውም ጊዜ አንድን ሰው ፈውሶ ከሆነ፥ በኢየሱስ፡ በሐዋርያት፡ በነቢያት ዘመን ይሁን፡ መቼም ይሁን መቼ፥ ያው ቅድመ ሁኔታ ሲሟላ፡ እንደገና ማድረግ አለበት። በትክክል። እርሱ አይለወጥም። ሰው ይለወጣል፡ ጊዜ ይለወጣል፡ ዘመን ይለወጣል፡ የዘመን አከፋፈል ይለወጣል፥ ነገር ግን እግዚአብሔር ያው ሆኖ ይኖራል። እርሱ ፍጹም ነው። ይህ ለታመሙ ሰዎች ምንኛ ተስፋን ሊሰጥ ይገባል!

83 ከዚህ በፊት ሰው ፈውሶ ከሆነ፡ ያው ቅድመ ሁኔታ ሲሟላ እንደገና ማድረግ አለበት። ከዚህ በፊት፡ ሰውን አድኖ ከሆነ፡ በመጀመሪያው ጊዜ ባደረገበት በዚያው መሠረት ላይ ማድረግ አለበት። ሰውን በመንፈስ ቅዱስ ሞልቶ ከሆነ፡ በመጀመሪያው ጊዜ ባደረገበት በዚያው መሠረት ላይ ማድረግ አለበት። ሰውን ከመቃብር አስነስቶ ከሆነ፡ በሁለተኛው ጊዜም ሆነ፡ በማንኛውም ሌላ ጊዜ፡ በዚያው መርህ ላይ ማድረግ አለበት።

84 እርሱ አይለወጥም። ኦህ፡ ይህ ምንኛ ተስፋ ይሰጠኛል! ምንድን ነው? የሆነ የሰዎች ቡድኖች በአንድነት በተሰበሰቡበት፡ በሆነ ሰው-ሰራሽ ንድፈ ሀሳብ ላይ አይደለም፥ ነገር ግን በማይለወጠው ቃሉ ላይ ነው።

“ይህ እውነት ነውን፡” ትላላችሁ?

85 እርሱም፡ “የሰው ሁሉ ቃል ውሸት ይሁን፡ የኔ እውነት ይሁን” አለ። “ሰማያትና ምድር ያልፋሉ፡ ቃሌ ግን ፈጽሞ አያልፍም።” “ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ በእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት የተሰጡ ናቸው፡ ስለዚህም ለትምህርት መልካምና ጠቃሚ ናቸው።” እንዲሁም “መጽሐፍ ቅዱስ ሁሉ ይፈጸማል፡” እያንዳንዱ ክፍሉ እንደሚፈጸም አስታውሱ።

86 እግዚአብሔር ለእኛ እንዴት ግልጽ እንደሚያደርግልን አስተውሉ። ይህ— ታላቅ ማረጋገጫ ካልሆነ፡ መልካም... ከእግዚአብሔር የሆነ ታላቅና፡ ፍቅር ያለበት በረከት ካልሆነ ተመልከቱ! ይህን ሳየው፡ ልጅ ከነበርኩበት ጊዜ ጀምሮ፡ ክርስቶስ ለመጀመሪያ ጊዜ ከተገለጠልኝ ጊዜ አንስቶ፡ እነዚያን ሦስት የጸጋ

ደረጃዎች ሁልጊዜ እንዳስተማርኩ አያለሁ። አሁን እውነት መሆን አለመሆኑን አስተውሉ።

87 አሁን፡ የመጀመሪያው እርምጃ “ወደ እግዚአብሔር ንስሐ መግባት” ነው። ከዚያም ቀጥሎ የሚመጣው፡ የውኃ ጥምቀት ነው፡ “የውኃ ጥምቀት፡” “ንስሐ ግቡ፡ በኢየሱስ ክርስቶስም ስም ተጠመቁ።” እያችሁ፡ ንስሐው እውነተኛ እንደነበረ ለማሳየት፡ የውኃ ጥምቀት ይከተላል። ወይም፡ ያለፉት ኃጢአቶቻችንን “ለማስረየት” ይጠቅመናል፡ ከወደፊቱ ኃጢአት ጋር ምንም ግንኙነት የለውም፡ ያስተሰርያል እንጂ። “ንስሐ ግቡ፡ በኢየሱስ ክርስቶስም ስም ተጠመቁ።” ለምን? “ለስርየት።” ያለፈውን ኃጢአት ማስወገድ ከወደፊቱ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም። ብቻ፡ ያደረጋችሁት፡ ኃጢአታችሁ ተቆርጦ ወድቋል።

88 አዳም ላደረገው ነገር ንስሐ መግባት አትችሉም። እናንተ አላደረጋችሁትም፥ አዳም ነው ያደረገው። ይቅርታ የምታገኙት ላደረጋችሁት ነገር ብቻ ነው። አሮጌው ተፈጥሮ አሁንም እዚያው አለ።

89 ለአንድ ደቂቃ ይህን ሰሌዳ ልጠቀም። [ወንድም ብራንሃም በጥቁር ሰሌዳ ላይ ሰዕሎችን ይሰላል—አርታዒ።] አሁን፡ **ይሄ** የሰው ልብ ነው። አሁን፡ አርቲስት ከመሆን... እጅግ የራቅሁ ነኝ። **ይሄ** የሰው ልብ ነው፥ **ይሄም** ደግሞ የሰው ልብ ነው። አሁን፡ **ይሄኛው** እዚህ በውስጡ እባብ አለው፡ ያ ኃጢአት ነው፡ እዚህ የራሱ ሕይወቱ አለው። ይሄኛው **እዚህ** በውስጡ ርግብ አለው፡ እርሱም መንፈስ ቅዱስ ነው፡ እዚህ የራሱ ሕይወት አለው። መልካም፡ **ይሄኛው** እዚህ፡ ክፋት፡ ጥላቻ፡ ቅናት አለው፥ ይሄን የሚያመጣው፡ ይሄ **እዚህ** ያለው አካል ነው። መልካም፡ **ይሄኛው** እዚህ ፍቅር፡ ደስታ፡ ትዕግስት አለው፥ እዚህ ታች ያለው፡ እሱ ነው ያንን የሚያደርገው።

90 አሁን፡ ስትጠየቁ፡ ወይም ኃጢአታችሁ ይቅር ሲባልላችሁ፡ ይህን ብቻ ነው ያደረጋችሁት፡ **ይህንን** አስወገዳችሁት። ነገር ግን እንድታደርጉት ያደረጋችሁ ነገር አሁንም እዚያው አለ። ያ የቀድሞው የክፋት ሥር ነው፥ አሁንም እዚያው አለ። አስተውሉ፡ ከዚያም ንስሐ ገብታችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠምቃችኋል፡ በዚህም ኃጢአታችሁን ይቅር ብሎላችኋል። አስተውሉ።

91 ከዚያም፡ በሁለተኛ ደረጃ፡ አእምሯችንን ለቅድስና በትክክል እንዲያስብ የሚያስተካክለው፡ መቀደስ ይመጣል። ተወ... መቀደስ የተዋቀረ የግሪክ ቃል ሲሆን፡ “የነጻ፡ እንዲሁም ለአገልግሎት የተለየ” ማለት ነው።

92 ከዚያም፡ በመቀጠል፡ እግዚአብሔር በእኛ ውስጥ ያድር ዘንድ፡ የእሳትና የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ይመጣል። የእግዚአብሔርም እሳት ልባችንን ከኃጢአት ያነጻል፡ መንፈስ ቅዱስንም በውስጣችን ያኖራል። ያ በውስጣችን ሰላለ፡ ከዚያም **ይህ** እንዳደረገው ዓይነት ሕይወትን እናፈራለን።

93 በተፈጥሯዊ ልደት፡ አንዲት ሴት ሕፃን ስትወልድ፡ አስተውሉ። ተፈጥሯዊው ሕይወት የመንፈሳዊ ሕይወት ምሳሌ ነው። አንዲት ሴት ሕፃን ስትወልድ፡ በተፈጥሯዊው፡ መጀመሪያ የሚሆነው የውኃ መፍሰስ ነው፡ ከዚያም ደም፥ በመቀጠልም መንፈስ (ሕይወት) ይመጣል። ትንሹን ልጅ ይዛችሁ ቂጡን ስትመቱት፡ እየጮኸ፡ ይሄዳል። [ወንድም ብራንሃም እጆቹን አጨበጨበ—አርታዒ።] ውኃ፡ ደም፡ መንፈስ።

94 አሁንም አንድ ሕፃን በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ሲወለድ፡ ልክ በዚሁ መንገድ ይመጣል፥ ውኃ፡ ደም፡ መንፈስ።

95 አሁን አስተውሉ፡ መቀደስ፡ ሦስተኛው ደረጃው... ሁለተኛው ደረጃው፡ አእምሮን ያነጻል፥ ልብን፡ የልብን አእምሮ፡ በቅድስና ሥርዓት ውስጥ ያስተካክለዋል።

96 አንድ ሰው ከኃጢአቱ ንስሐ ሊገባ ይችላል ሆኖም አሁንም የሚያስበው... እንግዲህ፡ ምናልባት እርሱ ሥነ—ምግባር የጎደለው ሰው ከሆነ፡ የሚያገኛት ሥነ ምግባር የጎደላት ሴት ሁሉ፡ አሁንም በውስጡ አለች። ምናልባት ሰካራም ሊሆን ይችላል፥ የመጠጥ ሽታ ባሸተተ ቁጥር፡ ፍላጎቱ አሁንም በውስጡ አለ። አያችሁ?

97 ነገር ግን ከዚያም ሲቀደስ፡ ያንን ፍላጎት ከውስጡ ጠርጎ ያወጣዋል። አያችሁ? ያንን መሻት ያስወግደዋል። አሁንም ሊፈተን ይችላል፡ ዳሩ ግን እርሱ መሻቱን ያስወግደዋል። አሁንም፡ ገና ትክክል አልሆነም።

98 ከዚያም፡ በመንፈስ ቅዱስና በእሳት ይጠመቃል። የነጻ፡ ተቃጥሎ የወጣ፡ የጸዳ ሆኖ፥ ከዚያም ለእግዚአብሔር አገልግሎት ይውላል።

መቀደስ **ለ**አገልግሎት ለይቶ ማስቀመጥ ብቻ ነው።

99 ያም እንዴት በትክክል እንደመጣ አስተውሉ፡ የመልእክቶቹን መምጣት አስተውሉ። ማርቲን ሉተር፡ መጽደቅ፥ ጆን ዌስሊ፡ መቀደስ፥ ጴንጤቆስጤ፡ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት። መልእክቶቹ፡ ከእነርሱ በላይ ሌሎች ዘመናት ሊኖሩ የማይችሉበት ደረጃ ነው፡ አያችሁ። እኛ በመጨረሻው ዘመን ላይ ነን። ሦስት ደረጃዎች። ጥምቀት በመንፈስ ቅዱስ ልብን ያነጻል።

100 አሁን ምንኛ አስደናቂ ነው፡ እኛ የምንኖርበትንም ስፍራ፡ በተመሳሳይ ሂደት ውስጥ ያሳልፈዋል።

101 አሁን፡ ቤተክርስቲያንን በመጽደቅ ጠርቷታል፡ በመቀደስም ጠርቷታል፡ ከዚያም በመንፈስ ቅዱስና በእሳት ሞልቷታል። እርሱ ራሱ፡ መንፈስ ቅዱስ ራሱ፡ የእግዚአብሔር ልጅ፡ በሰው ልብ ውስጥ ማደር እንዲችል፡ በሂደት ውስጥ አሳልፏታል። አሁን፡ እርሱ ወደ እርሰዋ ከመምጣቱ በፊት በዚያ ውስጥ ማለፍ አለባት።

102 ያቺ ሙሽራ የምትኖርበትን ዓለምም፡ በተመሳሳይ መንገድ፡ በዚያው በድነት ዕ—ዕቅዱ እንዳደረገው፡ አስተውሉ።

103 ከጥፋት ውኃ በፊት የነበረውን ዓለም ልብ በሉ። እርሱ፡ በዚያን ዘመን ሙሽራ በነበረው በኖኅ በኩል፡ ንስሐ ከገባች በኋላ፡ የውኃ ጥምቀትን ሰጣት፡ በውኃም ሸፈናት። ከዚያም፡ ማጽደቅ፡ ይህቺን የወደቀች ዓለም ከኤደን ጀምሮ በመጥራት፡ ዳግም ወደ ቀድሞ ሁኔታዋ ለመመለስ፡ በመንገዱ ላይ እንዳለ ያሳያል።

104 ከዚያም ክርስቶስ መጥቶ ደሙን በእርሰዋ ላይ በማፍሰስ፡ አነጻት የራሱም አደረጋት። አያችሁ፡ አሁን የምንኖርባት ዓለም ይህች ናት።

105 እዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፡ ሰይጣን፡ ወደ ተራራው ይዞት በወጣ ጊዜ፡ ዓለምን ለእርሱ በመስጠት የእግዚአብሔርን ዕቅድ አፍርሶ እንዲቀበል ለማድረግ እንዴት እንደሞከረ፡ ያለ ደም ዋጋ ሊሰጠው እንደሞከረ አያችሁ?

106 አብርሃም፡ መሬቱን ሊሰጡት በሞከሩ ጊዜ፡ በሕዝብ ፊት፡ እንደ ምልክት፡ እንደ ምስክር፡ በብዙ የብር ሰቅሎች እንዴት እንደገዛው አስተዋላችሁን? “ይህንን የመቃብር ሥፍራ መግዛቴ ዛሬ የታወቀ ይሁን።” እያችሁ፡ ገዛው! ሰይጣንም አሁን የራሱ የሆነውን መንግሥት ለእርሱ ሊ—ሊሰጠው ሞከረ። እንደ ስጦታ ሊሰጠው ሞከረ፡ ነገር ግን እርሱ አልተቀበለውም። ምክንያቱም፡ እያችሁ፡ እንደዛ ቢሆን ሰይጣን አሁንም በእርሷ ላይ የይገባኛል ጥያቄ ሊያነሳ ይችል ነበር። ነገር ግን፡ መገዛት ነበረበት። አሜን። እርሱ በሙላቱ ቃል ነበረ። በዚህ ሊያታልሉት አልቻሉም።

ከዚያም፡ አሁን የእሳት ጥምቀት የምታገኝበት ጊዜ ነው።

107 እያችሁ፡ አሁን እሷ... ምን ሆነ? ክርስቶስ መጣና ቤተክርስቲያንን ለንስሐ፡ ለኃጢአት ስርየት፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ወደመጠመቅ ጠራት፥ ቤተክርስቲያንን ቀደሳት፥ በእግዚአብሔርም እሳት ወርዶ ርኩሰቱን ሁሉ አቃጠለ፡ መጥቶም በሰው ልብ ውስጥ ያድራል።

108 አሁን፡ ዓለም፡ ለዚህ ለተዋጀው ሰው እንድትዋጅ፡ ያንኑ የራሱን ዘዴ ይጠቀማል። ከጥፋት ውኃ በኋላ፡ በውኃ አጠመቃት። ሊቀድሳትና የራሱ ሊያደርጋት፡ ደሙን በእርሰዋ ላይ አፈሰሰ። የርሱ ናት።

ሰይጣን፡ “እሰጥሃለሁ” ለማለት ሞክሮ ነበር።

109 እርሱም፡ “አይ፡ ወዳጄ፡ እገዛታለሁ” አለ። ምስክር ይሁን። እንደገዛት፡ ለምልክትነት፡ ከፍ ከፍ አለ። ገዛት።

110 ነገር ግን አሁን ምድርንና በዙሪያዋ ያሉትን ሰማያት በሚያነጻው በእሳት ጥምቀት፡ ከእግዚአብሔር በሆነ ቅዱስ እሳት ውስጥ፡ ማለፍ አለባት። ከዚያም፡ የተዋጁት በእርሰዋ ላይ መኖር እንዲችሉ፡ በሰላምም እንዲኖሩባት ተገዝታለች። አስተውሉ፡ የእሳት ጥምቀት ከኃጢአት፡ ከበሽታ፡ ከበሽታ አምጪ ተህዋስያን፡ ከኃጢአተኞች፡ ከዲያብሎስና ከጭፍራው ሁሉ እርሰዋን ለማንጻት ነው። እርሱም ወደ እሳት ባሕር ውስጥ፡ ይጣላል። ከእግዚአብሔር የሆነ ቅዱስ እሳት፡ ከእግዚአብሔር ዘንድ፡ ከሰማይ ይወርዳል፡ አስተውሉ፡ እግዚአብሔር ሊያድርባት ዝግጁ ለማድረግ፡ ያቃጥላታል። ምክንያቱም፡ እግዚአብሔር፡ ሊመጣ ባለው አዲስ ዓለም፡ በምድር ላይ ያድራልና። ምክንያቱም፡ እናንተ፡ “እግዚአብሔር፡ በሰው ልብ ውስጥ ያድራል” ትላላችሁ። ነገር ግን፡ እርሱና ሙሽራይቱ አንድ ይሆናሉ፡ ወደ አዲሱ ዓለም ቤታቸውም ይሄዳሉ። ያም ተመሳሳይ የቤዛነት ዕቅድ፡ ሁለቱንም፡ ዓለምንና በእርሰዋ ውስጥ የሚኖሩትን ሰዎች ለመዋጀት ጥቅም ላይ ይውላል።

111 እያችሁ፡ ልብ እንደዚያው መንጻት አለበት። እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ አካል ሆኖ ከመውረዱ በፊት፡ ይህም ክርስቶስ ወርዶ በሰው ልብ ውስጥ ማደሩ ነው፡ መጀመሪያ ንስሐ መግባት አለበት። የማን እንደሆነ ለማሳየት፡ በስሙ፡ በውኃ መጠመቅ አለበት።

ከዚያም በኢየሱስ ደም መንጻት አለበት።

112 ከዚያም ከእግዚአብሔር የሆነው፡ ቅዱስ እሳትና መንፈስ ቅዱስ፡ ወርዶ የኃጢአትን ፍላጎት ሁሉ፡ የዓለምንም ተፈጥሮ ሁሉ ያቃጥላል። “እና፡ ስለዚህ፡ የእውነትን እውቀት ከተቀበለ በኋላ ሆን ብሎ ኃጢአት የሚሠራ... ” ከዚያም፡

መጽሐፍ ቅዱስ እንደገና እንዲህ አለ፡ “የማይቻል ነው… ” “ከእግዚአብሔር የተወለደ ሰ—ሰው ኃጢአት ሊሠራ አይችልምና፥ ኃጢአትን አያደርግም” አለ። ኃጢአት የሚሠራበት ምንም መንገድ የለም። በተመሳሳይ ጊዜ ኃጢአተኛና፡ የተዋጀ፡ እንዴት ሊሆን ይችላል? በተመሳሳይ ጊዜ፡ ዕቃ ማሰያዣ ሱቅ ውስጥና፡ ዕቃ ማስያዣ ሱቅ ውጭ እንዴት ልሆን እችላለሁ? አያችሁ? ኦህ፡ በደሙ ዋጀን፥ በመንፈሱ አነጻን፥ ከዚያም በእኛ፡ በቤተክርስቲያን ውስጥ ሊያድር ይመጣል። አሁን፡ የሐይማኖት ተቋም አይደለም፥ ቤተክርስቲያን ነው!

113 አሁን የ—የምንኖርባቸውን ማደርያዎችን ስንመለከት፡ በጥሞና አስተውሉ። አሁን፡ አሁን፡ ከጥፋት ውኃ በፊት የ—የነበረው ንስሐ፡ ከዚያም፡ የውኃ ጥምቀትን አመጣ። ከዚያም ክርስቶስ መጥቶ ሊያነጻትና የራሱ ሊያደርጋት፡ ደሙን በእርሰዋ ላይ አፈሰሰ። ከዚያም ቀጥሎ፡ የሚመጣው፡ አሁን እንዳለችው ዓለምን ማጥፋት ነው።

114 ከላይ በሰማያት ያለው ኃጢአት ሁሉ፡ “እርሱ በአየር ላይ ሥልጣን ያለው አለቃ ነው፡” ከእግዚአብሔር የሚመጣውን በረከት ይከለክላል (ይዋጋል)። በዚያ የመብረቅ ነጎድጓድ መጥቶ ምድርን ይመታል፡ ሁሉም ነገር፡ ከሰማያት፡ ዶፍ ዝናብ፡ አውሎ ነፋሶች፡ አው-… ማዕበሎችና ሁሉም ነገር፡ “ከላይ ይመጣል፡” እርሱም ሰይጣን፡ “በአየር ላይ ሥልጣን ያለው አለቃ” ነው።

115 አስተውሉ፡ ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት እንዳልኩት፡ ሰይጣን ሳይገዛው ለኢየሱስ በመስጠት፡ እንዴት ሊወስደው እንደሞከረ አያችሁ። እንደዛ ቢሆን፡ አሁንም ሰይጣን የኔ ነው ይል ነበር፡ ምክንያቱም ምልክት ተደርጎበታልና፡ አያችሁ። ነገር ግን ኢየሱስ በፈሰሰው ደሙ ይገዛዋል ወደ ትክክለኛው ባለቤቱም ይመልሰዋል። አያችሁ? እርሱ ቤተክርስቲያንን እንዴት እንደገዛ፡ እኛን በደሙ የገዛን፡ እንደዚሁ ነው።

116 አሁንም የእሳት ጥምቀቱ ከጀርሞች ሁሉ፡ ከበሽታዎቹ ሁሉ፡ ከህመሞች ሁሉ፡ እንዲያውም ከመንፈሳዊ ነገሮች ሁሉ ያነጻታል፥ ይህም፡ በእኛም ላይ፡ በተመሳሳይ መንገድ ያደርገዋል፥ ሊመጣ ባለው በዚህ ታላቅ ዘመን፡ በአዲሲቱ ምድር፡ እግዚአብሔር ሊያድርባት ዝግጁ ያደርጋታል። አያችሁ፡ የራሱን ሕዝብ በሚዋጅበት በተመሳሳይ መንገድ ይዋጃታል። የቤዛነት ዕቅዱን፡ ሁሉንም ልክ አንድ ዓይነት ያደርገዋል። እርሱ፡ የማይለወጥ አምላክ ነውና፡ በዕቅዶቹም ዘወትር ያው ነው።

117 እግዚአብሔር ሊለወጥ እንደማይችል፡ ቀደም ብዬ፡ እንደነገርኳችሁ፡ እንዳሳወቅኋችሁ፡ በዘመናትም ሁሉ እንዳሳወቀ፥ በሁሉም መንገድ፡ በተመሳሳይ ሁኔታ፡ ግልጥ ያደርገዋል።

118 የመጀመሪያውን መልእክቱን፡ ከጥፋት ውኃ በፊት በነበረው ዓለም፡ በነቢዩ በኖኅ በኩል፡ ግልጥ አደረገው።

119 አሁን አብሮኝ ከተቀመጠ ውድ ወንድም ጋር ስነጋገር ነበር። ትናንት፡ “ወንድም ብራንሐም፡ አንድ የተናገርከው ነገር፡ ሁልጊዜ የሚያናውጠኝ ነገር አለ፡” አለኝ።

እኔም፡ “ምንድነው፡ ወንድሜ” አልኩት?

120 እርሱም፡ “እነሆ ያልከው ይህንን ነው” አለ፡ እውነትም ነው፡ “‘ጥቂቶቹ፡ በመምጣቱ ዘመን ትንሽዬ ቡድን እንዴት እንደሚድን ነው።’ ኢየሱስ፡ ‘ደጁ የጠበበ መንገዱም የቀጠነ ነው፡ የሚያገኙትም ጥቂቶች ናቸው’ ብሎ እንዴት እንደተናገረ ተነጋገርን። አሁን አስተውል፡ መጽሐፍ ቅዱስ፡ ‘በኖኅ ዘመን ስምንት ነፍሳት በውኃ እንደዳኑ፡ በመምጣቱም እንዲሁ ይሆናል’ አለ።”

እንዲህ አልኩት፡ “ወንድሜ፡ አንተ የተረዳኸው... ”

“አስታውስ፡ በዚያ የነበሩት ስምንት ነፍሳት ብቻ ናቸው፡” አለኝ።

እኔም፡ “አንተ ያገኘኸው ግማሹን ምሰል ብቻ ነው” አልኩት።

121 ሆኖም፡ ኖኅ የተሻገሩት ቅሬታዎች ምሳሌ እንጂ፡ ወደ ሰማይ የተነጠቀው ህዝብ ምሳሌ አልነበረም። ሄኖክ፡ አንድ ሰው፡ የጥፋት ውኃ ከመምጣቱ በፊት በንጥቀት ሄዷል፡ በዚህም ቤተክርስቲያን ወደ መከራውም ሆነ በዚያ ዙሪያ ወዳለ ወደ ማናቸውም ነገር እንደማትገባ ያሳያል። ሄኖክ አንድ ሰው፡ ተነጠቀ። ኦህ፡ ቤተ ክርስቲያን በቁጥር ብዙ ልትሆን ትችላለች፥ ነገር ግን ሙሽራይቱ ሙሽራይቱን የሚያዋቅራት እጅግ በጣም ትንሽ ቡድን ይሆናል። አሁን፡ ቤተክርስቲያን ትልቅ ቁጥር ልትሆን ትችላለች፥ ነገር ግን፡ ሙሽራይቱ፡ እያችሁ፡ ስምንትን ከአንድ ጋር አወዳድሩት። ሙሽራይቱ፡ ከቤተክርስቲያኒቱ፡ ስምንት እጥፍ ታንሳለች።

122 “ጻድቅም በጭንቅ የሚድን ከሆነ፡ ዓመፀኛውና ኃጢአተኛው ወዴት ይታይ ዘንድ አለው፡” ለማድረግ፡ የተሻለውን እያወቁ፡ ሄደው እንዴትም የሚያደርጉትስ? ከቃሉ ይልቅ የየሐይማኖት ተቋሙን ሕግጋት የሚከተሉት፡ ሆኖም ክርስቲያን ተብለው የሚጠሩ፡ የክርስቶስን ስም የሚወስዱትስ፡ የት ይታያሉ?

123 አሁን፡ በፍጹም ሁኔታ፡ ኖኅ የተሻገሩት ሰዎች ምሳሌ ነበር። አስታውሱ፡ ኖኅ ሲወጣ፡ ካም ከእርሱ ጋር ነበረ። ኃጢአት አሁንም በዚያ ውስጥ ነበረ። ኃጢአት በመርከቧ ውስጥ፡ ተሻግሮ ሄደ። አለማመን፡ ጥርጣሬ፡ በፍርድ ላይ ተጠርገው፡ በመርከቧ ውስጥ ተሻግረው ሄዱ። ነገር ግን ሄኖክ ከመርከቧ በላይ ከፍ ብሎ ሄደ፡ ወደ እግዚአብሔር መገኘት ውስጥ ገባ። ዳሩ ግን ኖኅ በዚያ ውስጥ አልፎ ወጣ፡ አሁንም ኃጢአት ነበረ፥ ይህም የሺህ ዓመት ግዛት፡ የዓለም ሁኔታ ምሳሌ ነው።

124 የሺህ ዓመት ግዛት መጨረሻው አይደለም። ከሺህ ዓመት ግዛት በኋላ አሁንም ጊዜ ይኖራል። የሺህ ዓመት ግዛት የሆነ ያህል ጊዜ ነው፥ ነገር ግን፡ አዲሲቱ ምድር አይደለም። በፍጹም፡ አይደለም። አስተውሉ፡ በዚያ ውስጥ፡ ከጥቂት ጊዜ በኋላ እንደርሳለን።

125 እያችሁ፡ ምድር፡ ተዋጅታ፡ እንደገና ወደ የቀድሞ ባለቤቷ ትመለሳለች። ወስደው... ከሰይጣን ወሰዳት። እናንተን ከሰይጣን እንደወሰዳችሁ፡ በውኃ ጉድጓዱ አጠገብ የነበረችውን ምስኪን ሴት፡ ከሰይጣን እንደወሰዳት ሁሉ፡ ምድርን ከሰይጣን እየወሰደ፡ ጎተታት። ካህኑ በዚያ ቆሞ ነበር፡ ከእግዚአብሔር ጋር እንዳለ አሰቦ ነበር፡ ሆኖም ምንም አልነበረውም። እያችሁ?

126 ለጥቂት ጊዜ ይህንን ልስላላችሁ እወዳለሁ። አሁን፡ ይህንን በጣም ግልጽ ማድረግ እንፈልጋለን፡ ስለዚህ አሁን ይህንን ትምህርት በደንብ ተከታተሉ።

[ወንድም ብራንሃም በሚቀጥሉት ጥቂት አንቀጾች ውስጥ በሰሌዳ ላይ ማብራሪያዎችን ይሰላል—አርታዒ።]

127 አሁን፡ ይህ **እዚህ** ያለው፡ እዚህ ያለው እግዚአብሔር ነው። ዘላለማዊ የሆነው፡ እግዚአብሔር፡ ያለ… ከእርሱ በቀር ማንም የለም። ነገር ግን፡ በእግዚአብሔር ውስጥ፡ ባህርያት ነበሩት። አሁን፡ ይህ **እዚህ** ያለው ቃልን ይወክላል፡ ሥጋ የሆነውንና በኢየሱስ ማንነት በእኛ መካከል ያደረውን፡ የእግዚአብሔርን ቃል ይወክላል።

128 አሁን ይህ **እዚህ** ያለው፡ እዚህ ያለው ሰው፡ እሱን ልክ **እንደዚህ** እናደርገዋለን። አሁን፡ **ይህች** በውኃ ጉድጓዱ አጠገብ የነበረችው ሴት ናት። **ይህኛው** ካህኑ፡ ፈሪሳዊው ነው። **ይህን፡** ባዶ ሰሌዳ የምታዩበት፡ ይህ ማለት ጸጋና ድነት ማለት ነው።

129 አሁን፡ "በመጀመሪያ ቃል ነበረ። ቃልም ሥጋ ሆነ በእኛም ዘንድ አደረ።" ሦስቱ ደረጃዎች። እርሱ በመጀመሪያ ባህርይ ነበረ፥ ራሱን እንደ ሰው አድርጎ በማሰብ፡ በእግዚአብሔር ውስጥ ነበረ፥ ያም አስተላልፎት ኢየሱስ እንዲሆን አደረገው፥ አሁንም፡ እዚያ ከሆናችሁ፡ ያኔ ከእርሱ ጋር ነበራችሁ። ምክንያቱም፡ አንድ ዓይነት የዘላለም ሕይወት ብቻ ነው ያለው፡ እርሱም እግዚአብሔር ነው፥ እዚህ ታች የመረጣችሁትን ሳይሆን፡ በመጀመሪያ የእግዚአብሔር አካል መሆን ነበረባችሁ። እርሱ መረጣችሁ። "አብ የሰጠኝ ሁሉ ወደ እኔ ይመጣል።"

130 አሁን እዚህ ያለውን ይህንን ካህን ተመልከቱት። የእርሱን ታችኛውን ክፍል፡ **እዚህ፡** የኋላ ሕይወቱን፡ ከእርሱ በስተኋላ ያለውን፡ እዚህ ኋላ ያለው አስቀድሞ መወሰኑን፡ ኃጢአተኛ እንደሆነ እናገኛለን።

እዚህ ጋር ሲኦል አለ፡ **እዚህ** ታች።

131 አሁን፡ ሰሌዳ የሚመስለው፡ **እዚህ** ያለው ይህ ትንሽ ክፍል፡ ንጽህናውን ይወክላል። እርሱ ካህን ነበረ። የተከበረ ሰው ነበረ። ያም **ይህንን** ወክሏል። እንዲሁም፡ ጥሩ ሰው፡ መሆን ነበረበት፡ አለበለዚያ ካህን መሆን አይችልም ነበር። ነገር ግን እንዴት እንዳገኘው እያችሁ፡ ምሁራዊ ትምህርት ነበረ።

132 አሁን፡ የዚህች ምስኪን ሴት፡ የመጀመሪያ ሕይወቷ፡ **እዚህ** ላይ ያለው፡ ሴተኛ አዳሪ ነበረች፥ ፈጽሞ የተበላሸች ነበረች። ዳሩ ግን በውስጧ ጥልቅ ሰፍራ፡ **እዚህ፡** ጥቂት ማስተዋል ነበረ። "መሲሕ ሲመጣ አውቃለሁ… " እያችሁ? እያችሁ፡ ያ እዚያ ነበረ።

133 አስተውሉ፡ ኢየሱስ መጥቶ ቃሉን በገለጠ ጊዜ፡ ቃሉ በልብ ውስጥ ያለውን አሳብ፥ በዕብራውያን 4 ላይ፡ 4፥12፡ እንደሚያደርገው እንደሚናገረው የሚለይ ነበር። "ቃሉ የልብን አሳብ የሚለይ ነበረ፥" እርሱም እንደ ሰው ልጅ፡ እንደ ነቢይ መጣ። ምን ተፈጠረ? ይህ ካህን፡ ምሁራዊ ትምህርት ብቻ ኖሮት፡ "ይህ አጋንንት ነው፡" አለ፡ ምክንያቱም የሐይማኖት ተቋሙ የሚጠራው በዚህ መንገድ ነበርና። ያ ምን አደረገ? ምንም ውክልና አልነበረውም፥ ስለዚህ አጨለመበት።

134 ነገር ግን ይህች ምስኪን ሴት የምታቀርበው ምንም ነገር አልነበራትም፥ ልትሆን የምትችለውን ያህል የረከሰችና የቆሸሸች ነበረች። ነገር ግን፡ አስተውሉ፡

ጥልቅ በሆነው ውስጧ፡ ውክልና አላት፡ እያችሁ። ከዚያም፡ ይህ ሥጋ ሆኖ እንዲገለጥ፡ ትጠባበቅ ነበረ።

እርሱም፡ “ሂጂና ባልሽን ጠርተሽ ወደዚህ ነይ” ባላት ጊዜ።

እርሰዋም፡ “ጌታዬ፡ ባል የለኝም” አለች።

135 እንዲህ አላት፡ “እውነት ተናግረሻል፡ ምክንያቱም አምስት ነበሩሽ፥ አሁን አብሮሽ ያለው ባልሽ አይደለም። አምስት ነበሩሽ። ያም ስድስት እንደነበሩሽ ያደርገዋል” አላት።

136 እሷም፡ “ጌታ ሆይ” አለች! (“አንተ፡” አላለችም፡ “ብዔልዜቡል፡” አላለችም።) “አንተ ነቢይ እንደሆንክ እያለሁ። አሁን፡ ክርስቶስ የሚባል፡ መሲሕ እንደሚመጣ፡ እናውቃለን። ሲመጣም፡ ይህን ያደርጋል” አለችው።

እርሱም፡ “እርሱ እኔ ነኝ” አላት።

137 ከእንግዲህ ምንም ጥርጥር አልነበረም። ማብራራት አላስፈለገም። አየችው። አመነችበት። ጥላ ሄደች! ለምን? ምን አደረገላት? ዋጃት።

138 አሁን ተመልከቱ፡ ቤዛ ሊሆን መጣ። ልክ ነው? **መዋጀት** ማለት ምን ማለት ነው? “ወደነበረበት መመለስ።” ለምን ካህኑን አላገኘውም? ፈጽሞ እዚያ አልነበረም። እያችሁ? እያችሁ፡ ምንም ውክልና አልነበረውም።

139 የወደቀውን ሊዋጅ መጣ። በውድቀቱ ጊዜ፡ **ይህ** ነገር፡ በዚያች ሴት ተበላሽቶ ነበር፥ ሆኖም እግዚአብሔር ዓለም ከመፈጠሩ በፊት በአሳቡ ውስጥ ነበረችው፡ ሊያነጻትም መጣ። እያችሁ? ከዚያም እርሱ... የዘላለም ሕይወት ነበራት። እያችሁ?

140 ታዲያ፡ ካህኑን፡ ምን አደረገው? ቀጥታ ወደ መድረሻው መልሶ ላከው። ሲጀመር፡ ምንም አልነበረውም፡ አእምሯዊ ዕውቀት ብቻ እንጂ።

141 አሁን ስሙኝ፡ ወዳጆቼ፡ ያላችሁ ብቸኛ ነገር አእምሯዊ ዕውቀት ብቻ ከሆነ፥ ከዚያ የተለየ ነገር ታገኛላችሁ። ውክልና ካላገኛችሁ በስተቀር በፍጹም ልታገኙት አትችሉም። ሕያው የሆነው፡ ቃል፡ ስለተገለጠ፥ ከምሥራቅና ከምዕራብ፡ ከሰሜንና ከደቡብ እንደመጣችሁ የማምነውም ለዚህ ነው።

142 አሁን በመጀመሪያ፡ መንገዱን በነቢያቱ በኩል እንዴት እንደሚያሳውቅ አስተውሉ። ፈጽሞ አልለወጠውም።

143 [ቴፕ ላይ ባዶ ቦታ አለ—አርታዒ።]... ድነት። ሰውን አጸደቀ፥ ቀደሰው፥ መንፈስ ቅዱስንና እሳትን ላከ፥ ኃጢአቱንም እቃጥሎ አወጣለት፡ እራሱም፡ በውስጡ አደረ።

144 በቤዛነት እቅድ ሊጠቀምባት ያሰባትን ምድርንም፡ በተመሳሳይ መንገድ፡ ያደርጋታል። ንስሐ ገባች በውኃም ተጠመቀች፡ በ... በኖኅ። ኢየሱስ መጥቶ ደሙን በላዩዋ ላይ በማንጠባጠብ፡ ቀደሳት፡ የራሱም አደረጋት። በምትመጣው አዲስ ምድርም፡ ከእያንዳንዱ አጋንንት፡ ከእያንዳንዱ ጀርም፡ ከእያንዳንዱ በሽታ፡ ካለባትም ነገር ሁሉ ሊያጸዳትና፡ አዲስ ሊያደርጋት፡ የቅዱስ እሳት ጥምቀት ይኖራታል። “አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር አየሁ።”

145 አዲስ ሰው ትሆናላችሁ። አሜን! ቤተክርስቲያንን በመቀላቀል ወይም አዲስ ገጽ ለመክፈት በመሞከር፡ የተጠገነ አሮጌ ሰው ብቻ ሳትሆኑ፥ ነገር

ግን ሙሉ በሙሉ-አዲስ ፍጥረት ናችሁ። እግዚአብሔር አሮጌውን ሰው ወሰደ፡ በመንፈስ ቅዱስና በእሳት ሙሉ በሙሉ ያቃጥለዋል፡ ራሱም መጥቶ፡ ውክልናችሁን ወደ ታች ይልካል። "አባቴ ከሳበው በቀር ማንም ወደ እኔ ሊመጣ አይችልም። አብ የሰጠኝም ሁሉ ወደ እኔ ይመጣል።" አያችሁ? ተመሳሳይ እቅድ፥ ተመሳሳይ መንገድ።

146 ሰይጣን... ሰይጣን ከእናንተ እንደተወሰደው ሁሉ፡ ልክ እንደዚሁ ሰይጣን ከምድር ይወሰዳል። ሰይጣን ሊያሰቸግር አይችልም፥ ወይም፡ ሊፈትን ይችላል፡ ሆኖም ግን ዳግም-የተወለደውን ክርስቲያን ሊያገኘው አይችልም። ምክንያቱም፡ እግዚአብሔር፡ ዓለም ከመፈጠሩ በፊት አስቀድሞ፡ ስላየው፡ ሊዋጀውም ኢየሱስን ስለላከ፡ ደሙም ስለ እርሱ ይናገራል። በእግዚአብሔር ዘንድ፡ እንኳን፡ መታየት ካልቻለ እንዴት ኃጢአት ሊሠራ ይችላል? እርሱ እንዲያውም... እርሱ የሚሰማው ብቸኛ ነገር ድምፃችሁን ብቻ ነው። የሚያየውም ውክልናችሁን ነው። አሜን! ያ እውነት ነው። አያችሁ?

147 በተመሳሳይ ሁኔታ፡ እናንተ ከባሕርያቱ አንዱ እንደሆናችሁ ሁሉ ዓለምም ከባሕርያቱ አንዷ ናትና። በመጀመሪያ፡ በእግዚአብሔር አሳብ ውስጥ ስለነበረች፡ ዓለም ከባሕርያቱ አንዷ ትሆናለች። ዓለም እንዲኖረው፡ በዙፋን ላይ ሊሆን፡ ንጉሥ ሊሆን፡ ቤዛ ሊሆን፡ ፈዋሽ ሊሆን፡ ያ ባሕርያቱ ነው።

148 ልክ እንደ እናንተ ባሕርይ ነው። ስለ ምስሶ ካላሰብኩ በ—በስተቀር "ምስሶ" ብዬ መናገር አልችልም። ስለ ሰው ካላሰብኩ በስተቀር "ሰው" ብዬ መናገር አልችልም። ስለ ሰው ሳስብ፡ ከዚያም "ሰው" ስል፡ ማሰቡ የኔ ባሕርይ ሲሆን መግለጹ ደግሞ ቃሉ ነው። አያችሁ?

149 እንደ ኢሳይያስ፡ እርሱ፡ "ድንግል ትፀንሳለች" ብሎ፡ እንዴት ሊናገር ቻለ? አሳብ ምንድን ነው?

150 አሁን፡ ብዙዎቻችሁ ያ በመንፈስ መለየት፡ እንዴት እንደሚመጣ፡ ትደነቃላችሁ። ልነግራችሁ ነው። አያችሁ፡ የምናገረው ቃል ነው። የኔም አሳብ አይደለም፡ ምክንያቱም አላውቀውምና። ስለማሰቡ አላውቅም። ሳላውቃችሁ፡ ማን እንደሆናችሁና ከየት እንደመጣችሁ እንዴት ልነግራችሁ ቻልኩ? በሕይወቴ አይቻችሁ ሳላውቅ፡ ከአሰር ዓመት በፊት ምን እንዳደረጋችሁ እንዴት ልነግራችሁ ቻልኩ? ከአሰር ዓመት በኋላ የት እንደምትሆኑና ምን እንደምታደርጉ እንዴት ልነግራችሁ ቻልኩ? ስለ ወደፊቱ እንዴት አወቅሁ? ሆኖም ይህ የሆነ አካል ሀሳብ ነው።

151 "በክርስቶስ የነበረ ይህ አሳብ በእናንተ ዘንድ ደግሞ ይሁን። በክርስቶስ የነበረ ይህ አሳብ በእናንተ ዘንድ ደግሞ ይሁን።" አያችሁ፡ እንደዛ ከሆነ የናንተ አሳብ አይደለም። በእናንተ በኩል፡ የእርሱ አሳብ ነው። የራሳችሁንም ቃላት እየገለጻችሁ አይደለም፥ የእርሱን ቃላት እየገለጻችሁ ነው።

152 ወንድሞች በልሳን ትርጉምና፡ በሌሎችም ነገሮች ላይ፡ ብዙ ጊዜ ግራ የሚጋቡት በዚህ ነው። አያችሁ፡ ትክክል ያልሆኑ ነገሮችን ይናገራሉ፡ ያም ሰይጣን መሆኑን አይገነዘቡም። እናንተም፡ "በእግዚአብሔር ገነት ውስጥ" ትላላችሁ? እስክንጨርስ ድረስ ብቻ ጠብቁ፡ እንደዛ መሆኑን፡ ወይም አለመሆኑን እናያለን። እንክርዳዱና ስንዴው በአንድ ማሳ ውስጥ ያድጋሉ። ሁለቱም በተመሳሳይ ፀሐይና በተመሳሳይ ዝናብ ይኖራሉ። አያችሁ?

153 “ነገር ግን በመካከላችሁ ነቢይ ቢኖር፡ እኔ እግዚአብሔር እናገረዋለሁ። የተናገረውም ቢፈጸም፡ እንደዛ ከሆነ የተናገርኩት እኔው ነኝ፡ አያችሁ፡ ምክንያቱም የራሱን እየገለጸ አይደለምና። አሳቤን፡ ሊመጡ ያሉትን የነገሮች ባሕርያቴን እየገለጸ ነው፡ እነርሱንም ለመግለጽ አፉን እጠቀማለሁ። ከተናገራቸውም በኋላ፡ መፈጸም አለባቸው። ሰማይና ምድር ያልፋሉ፡ ቃሌ ግን ፈጽሞ አያልፍም።”

154 ኢሳይያስ፡ “ድንግል ትፀንሳለች” አለ። በቃ ያ እልባት ይሰጠዋል። ትፀንሳለች። እግዚአብሔር የተናገረውን፡ ያደርገዋል።

155 ኦህ፡ በነቢያቱ በኩል፡ ሁሉንም መገለጦቹን፡ ያሳውቃል፡ ምክንያቱም የተገለጹት የአሳቦቹ ባሕርያት ናቸውና።

156 አሁን፡ **በዚህች** ምስኪን ሴት ውስጥ የነበረው፡ ይህ ነው። እሷ ከባሕርያቱ አንዷ ነበረች። አያችሁ?

157 ብርሃኑን የሚወክለው፡ ካህኑም እዚያ ነበር፡ ያንንም ከመጽሐፍ ቅዱስ ተምሮት ነበር። እግዚአብሔር አምላክ እንደሆነ ተምሮ ነበር። ቅድስና ትክክል እንደሆነ ተምሮ ነበር። የእግዚአብሔር ሕግ እንዳለ ተምሮ ነበር። ይህንንም የተማረው በአእምሯዊ ግንዛቤ ነው። በትክክለኛው የትውልድ ሐረግም ተወልዶ ነበር፥ ሌዋዊ ነበር። ሆኖም የሚያውቀው በአእምሯዊ ግንዛቤ ብቻ ነበር። የዘመኑም ብርሃን ሲ... አያችሁ፡ የተማረው **በሆነው** ነገር እንጂ፡ እየሆነ ባለው አልነበረም፥ ከዚህ በፊት በሆነው ነገር! እየሆነ ያለውንም ባገኘ ጊዜ፡ የሐይማኖት ተቋሙ ስለዚያ ምንም አላለም፡ ስለዚህም እርሱ ምንም ውክልና አልነበረውም።

158 ሆኖም እነዚያን የእግዚአብሔር ባሕርያት ለመዋጀት፡ በዚያን ጊዜ ቤዛው በምድር ላይ ነበር፡ እሷም ተቀበለችው። ፈጽሞ አልጠየቀችውም። እሷም፡ “መሲሑ ሲመጣ፡ ይህን ያደርጋል” አለች፡ ያም እልባት ሰጠው። ሲደረግም አየችው፡ ስለዚህ... እርሱም፡ “እኔ መሲሑ ነኝ” አላት፡ ስለዚህ ያ እልባት ሰጠው። ተጨማሪ ጥያቄ የለም። እሷም ሄዳ፡ ለሌሎች ሁሉ፡ “ኑና፡ ያገኘሁትን ሰው ተመልከቱ” ማለት ጀመረች።

159 እነዚህ ሂደቶች ንጹሕ ያደርጉናል፡ ለመኖሪያ ስፍራው የሚሆን ቤተመቅደስ ያደርጉናል፥ ጽድቅ፡ መቀደስ፡ በመንፈስ ቅዱስና በእሳት መጠመቅ። ያ የዚህን (የኛን) ቤተመቅደስ መንጻት ያከናውናል።

160 ስለዚህ፡ የቀድሞ የዓለም ማዕቀፍ፡ በውኃ በታጠበች ጊዜ እንዳልጠፋ ሁሉ፥ የፕላኔቷ ማዕቀፍ፡ የቀድሞ ማዕቀፍ፡ ያ... ቆሻሻው ሁሉ፡ እግዚአብሔር በምድር ላይ ያስቀመጠው ነገር ሁሉ፡ የመጀመሪያዋ ዓለም በጠፋች ጊዜ አልጠፋም። መጽሐፍ ቅዱስ “ጠፍቷል” አለ፡ ነገር ግን ማዕቀፍ ፈጽሞ አላጠፋውም ነበር። በላዩ ላይ የነበረውን ኃጢአትና ኃጢአተኞችን ብቻ አጠፋ። ማዕቀፉ ግን ቀረ።

161 ነገር ግን፡ አያችሁ፡ ማጽደቅ፡ እናንተ ባፕቲስቶችና ሜቶዲስቶች ማሰብ እንደምትፈልጉት፡ ጽድቅ ብቻ፡ ማመንና መጠመቅ፡ ያ በቂ አይደለም። ወዲያውኑ ወደ ዓለም ነገሮች ትመለሳላችሁ፡ ጸጉራችሁንም ትቆርጣላችሁ አጫጭር ልብስም ትለብሳላችሁ፡ ሌላውንም ሁሉ ታደርጋላችሁ። አያችሁ፡ ገና ምንም

የሆነ ነገር የለም። ወደ ኋላ ተመልክታችሁ ስህተት እንደሰራችሁ ብቻ አያችሁ እንጂ።

162 ጽድቅ ለዓለም ምን አደረገላት? ምንም አላደረገላትም፥ እንደነበረው ባለ ብዙ ኃጢአት ሆኖ፡ ወዲያውኑ እንደገና ጀመረ። ሰው የሚያደርገውም እንደዚሁ ነው፡ የሚሄድበትም ርቀት ይህ ነው።

163 ታላቁ ወንጌላዊ፡ ቢሊ ግራሃም፡ ሊያየው የሚገባው በዚህ መንገድ ነው። እሱም፡ "ሄጄ ሠላሳ ሺህ ሰዎችን ጌታን እንድቀበሉ አደርጋቸዋለሁ፥ በአንድ ዓመት ጊዜ ተመልሼ ስመጣ ግን ሠላሳም አላገኝም" አለ። የሄዱበት ርቀት ያው ነው። አያችሁ? በእርግጥም፡ ንስሐ፡ ይገባሉ። አብዛኛዎቹ፥ ወይም ቢያንስ የተወሰኑት፥ ንስሐ እንደሚገቡ አምናለሁ። ነገር ግን የሚያስፈልገው ያ አይደለም። ይህ እዚህ ጋር ያረጋግጠዋል።

164 አሁን፡ ስለዚህ የቀድሞው ዓለም ማዕቀፍ በውኃ አልጠፋም። ዓለም ታጠበች ብቻ እንጂ። ጥምቀቷን አገኘች። ተጠመቀች።

165 ስለዚህ በእሳት ብትቃጠልም፡ ማዕቀፉ ይቀራል። ምድርን አያጠፏትም፡ አያችሁ፡ በእርሰዋ ላይ ያለውን ኃጢአት ብቻ ያጠፏዋል።

166 እንዳንዶቻችሁ፡ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች፡ በተለይም እኔን የምትመለከተው ዶክተር ቬይል፡ እዚህ ላይ አስተውል። በጴጥሮስ፡ በጴጥሮስ 2ኛ ምዕራፍ ላይ፡ ማለትም በ3ኛ ምዕራፍ ላይ ያለውን፡ አስተውሉ፡ "ዓለም" የሚለውን ቃል፡ **ኮስሞስ** በሚል የግሪክ ቃል ይጠቀመዋል፡ ትርጉሙም፡ "የዓለም ሥርዓት" ማለት ነው። "ምድር ታልፋለች፥ የፍጥረትም መሠረት በትልቅ ትኩሳት ይቀልጣል።" አያችሁ? ይህ ማለት ምድር፡ ፕላኔቷ፡ ታልፋለች ማለት አይደለም። ነገር ግን ዓለም፡ **ኮስሞስ፡** ፖለቲካው፡ ኃጢአተኞች፡ መዋቅሮች፡ ኃጢአት፡ በሽታ፡ ጀርሞች፡ ስህተት የሆነው ነገር ሁሉ፡ ያልፋል። በአንድ ወቅት የነበረ ሁሉም ነገር...

167 እግዚአብሔር በአንድ ወቅት ሰማያትን አናወጠ፡ ነገር ግን በዚህ ጊዜ ምድርን፥ ሰማያትንና ምድርን እንደሚያናውጥ ተናገረ... "ምድርን አናወጠ፡" ማለቴ፡ "በዚህ ጊዜ ደግሞ ሰማያትን ያናውጣል።" አያችሁ? "የማይናወጥ መንግሥት እንቀበላለንና።" ዘላለማዊ መንግሥት ነው። ወደዚያ እንዴት እንደሚሄድ ተመልከቱ።

168 እዚህ ጋር አስተውሉ፡ ጴጥሮስ፡ "በትልቅ ትኩሳትም ይቀልጣል፡ በእርሰዋም ላይ ያለው ሥራ ይቃጠላል" አለ እንጂ፡ ፕላኔቷን አላለም። "በእርሰዋም ላይ ያለው ሥራ፡" የሰው ሥራ፡ ፖለቲከኞቻቸውና ሴራዎቻቸው ሁሉ፥ የሐይማኖት ተቋሞቻቸውና ሰው-ሠራሽ ሴራዎቻቸው ሁሉ፡ በምትቃጠልበት ጊዜ አብረው ያልፋሉ።

169 "ሰ—ሰማያትም በታላቅ ድምፅ ያልፋሉ።" እዚህ ጋር አስተዋላችሁን? "ሰማያት በታላቅ ድምፅ ያልፋሉ።" አዳምጡ! መላዋ ምድር በእሳት ትሆናለች፡ በምድር ውስጥ ያሉት ጋዞች ይቀጣጠላሉ ይፈነዳሉም። በትክክል። ሲናገር... መጽሐፍ ቅዱስ እዚህ፡ ጴጥሮስ፡ "ሰማያትም ምድርም፡ በታላቅ ድምፅ፡ ያልፋሉ" አለ። እንዲህ ያለው ፍንዳታ ያናውጣታል፡ ኦህ፡ ማይ፡ ምክንያቱም እያንዳንዱን በሽታ፡ እያንዳንዱን እሜከላን፡ እያንዳንዱን እሾህን መግደል አለበትና። መደረግ ያለበትን ሁሉ፡ እሳቱ ያቃጥለዋል። ደግሞም፡ አስታውሱ፡

ዝም ብሎ ተራ እሳት የሚባል አይነት እሳት አይደለም፡ ቅዱስ እሳትም ጭምር ነው፡ አያችሁ፡ ሰይጣንንና የርሱ የሆኑትን ሁሉ፡ አጋንንትን ሁሉ የሚያስወግድ ነው። “ሰማይም ምድርም፡” አሜን፡ “ያልፋሉ፡” ጀርሞችን ሁሉ፡ ነፍሳትን ሁሉ፡ በላዩዋና በዙሪያዋ ያለውን ተፈጥሯዊ ሕይወት ሁሉ ይገድላል፡ $H_2O$ (ውኃው) እንኳን ይፈነዳል። አሰቡት እስቲ። ስለ ድምፅ ከተነሳ!

170 ሰድሰቱን ማኅተሞች በፊታ ጊዜ፡ በዙሪያው ያለውን አገር ያናወጠውና መነጋገሪያ የሆነው፡ እዚህ ቱክሰን ውስጥ የነበረው ያ ትንሽ ድምፅ፡ የሆነ ነገር እንደሆነ ይመስላችኋል። ይህቺ ምድር ጥምቀቷን እስክትቀበል ድረስ ጠብቁ!

171 ታውቃላችሁ፡ አንድ ሰው የእሳት ጥምቀትን ሲቀበል፡ በዚያ አካባቢ ብዙ ጫጫታ ይኖራል። ሰዎች እንደዚያ ሲጮሁና እልል ሲሉ መሰማት፡ ያ ነውር እንደሆነ ያስባሉ። ይህቺ ምድር ጥምቀቷን እስክታገኝ ድረስ ብቻ ጠብቁ!

172 አዎን፡ ያብራራላችኋል... H2O፡ ውኃውን፡ ያፈነዳዋል፡ ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ እዚህ ራዕይ 21 ላይ፡ “ባሕርም ወደ ፊት የለም” ብሏልና፡ ያፈነዳዋል። ይህ የመላዋን ምድር ገጽታ በሙሉ ይለውጠዋል። እርሰዋ ትፈነዳለች ወደ ሰብርባሪዎችም ትበተናለች። ውጫዊው አካል በሙሉ፡ ቅርፊቱ፡ እንዲሁም ከእርሱ በታች ለመቶዎች ጫማዎች ያህል፡ በቀላሉ ሙሉ በሙሉ ይደመሰሳል። አሁን በምድር ላይ ያሉት አትሞስፌሮች፡ ጋዞቹ፡ እነዚህ ሚሳኤሎች ሰንጥቀው ሊያልፋት የማይችሉ ሆነው ያገኙበት፡ እዚያ ላይ ያለ ትልቅ ሉል አለ፡ በጣም ከፍ ብሎ እነሱ እንደሚሉት፡ ልዩ ልዩ ዓይነት ጋዞች ባሉበት በአንድ ዓይነት ሉል ውስጥ ነው፥ ያም ይፈነዳል። የእግዚአብሔር ቅዱስ ቁጣ በእርሰዋ ላይ ይመጣል፡ አያችሁ፥ ያነጻታልም፡ መላውንም ገጽታ ይለውጠዋል።

173 አሁን፡ ይህንን ቃል ለመጻፍ ለምትፈልጉት ለብዙዎቻችሁ፡ የግሪኩ ቃል፡ “ማለፍ” የሚለው ልነገራችሁ። ቃሉ የመጣው... ፈልጌ ማግኘት ነበረብኝ። “ይህቺ ዓለም እንዴት ታልፋለች፡ ሆኖም ግን በእርሰዋ ላይ ልንኖር ነውን፡” ብዬ አሰብኩ? ነገር ግን ካሰተዋላችሁ፡ ለመጻፍ ለምትፈልጉ አንዳንዶቻችሁ፡ ፊደላቱን እዘረዝርላችኋለሁ። ላነበው አልቻልኩም፡ p-a-r-e-r-e-c-h-o-m-i-a። እንዴት እንደምለው አላውቅም።

174 አሁን፡ በዚያ መንገድ፡ እንዳልኩት፡ ሳገኝ... መንፈሳዊ መነሳሳት ለሆነ ነገር ይነካኛል፡ ከዚያም ቃሉን ለማግኘት ወደ ኋላ እመለሳለሁ። አሁን፡ እዚህ፡ የቃሉን ፊደላት መዘርዘር አልችልም፡ ወይም ላ––ላነበው አልችልም። ሆኖም፡ በዚያ ውስጥ፡ ጌታ አሁንም መንገድ ሰጥቶኛል። እሄድና የዚያን ቃል ትርጉም ምን እንደሆነ አገኛለሁ፡ ከዚያም አገኘዋለሁ። አያችሁ? ከዚያም ዳግመኛ፡ አገኘዋለሁ። አያችሁ?

175 ሰማያትና ምድር **ያልፋሉ**፡ አሁን፡ ይህ ቃል፡ “ከአንድ ቅርጽ ወደ ሌላ ማለፍ” ማለት ነው። የእንግሊዝኛው ቃል እንደሚያመለክተው፡ **ያልፋል**፡ ሙሉ በሙሉ ይጠፋል እንደሚለው፡ “መደምሰስን” አያመለክትም። ሆኖም የዕብራይስጡ ቃል፡ ወይም እዚህ ያለው የግሪኩ ቃል፡ **ያልፋል** ማለት አይደለም፥ ትርጉሙም፡ “ከአንድ ነገር ወደ ሌላ ማለፍ” ማለት ነው። ተመልከቱ፡ ነገር ግን፡ “ከአንድ ሁኔታ፡” እንዲህ ይላል፡ “ወደ ሌላ ማለፍ” ማለት ነው።

176 አሁን አስተውሉ፡ አሁን ማንበብ ከፈለጋችሁ፡ ጳውሎስ ተጠቅሞበታል። ጳፉት፡ በኋላ ልታነቡት ትችላላችሁ። በቲቶ 3፡5 ላይ፡ ጳውሎስ ይሄንኑ ቃል ይጠቀማል፡ የሰውን ዳግም ልደት ያመለክታል፡ ሰው ከኃጢአተኛነት ወደ ቅዱስነት ማለፉን እንጂ፡ ሙሉ በሙሉ መደምሰሱን አያመለክትም። ሰው ሲለወጥ፡ መሉ በሙሉ አይጠፋም፥ ነገር ግን የተለወጠ ሰው ይሆናል። ከነበረው ወደ ሆነው ተለውጧል እንጂ፡ ሙሉ በሙሉ አልጠፋም።

177 ኢየሱስ በማቴዎስ 19፡28 ላይ ይሄንኑ ቃል ተጠቅሟል፥ አሁን፡ 28፡19 አይደለም። አሁን፡ በ19፡28፡ እንዲህ አላቸው፡ “ሲታደሱ፡ በአባቴ መንግሥት ከእኔ ጋር ትቀመጣላችሁ፡” አያችሁ፡ “ስትለወጡ፡” በተለወጣችሁ ጊዜ። ይሄንኑ ቃል ተጠቅሟል።

178 ለውርንጫውም፡ “ውርንጫውን ፍቱትና ይሂድ፡” ባለ ጊዜም፡ ይሄንኑ ቃል ተጠቅሟል።

179 በአልዓዛር ትንሣኤ ጊዜም፡ “ፍቱት! ለውጡት! ታሰሯል፥ ይሂድ” በማለት ያንኑ ተናግሯል!

180 ምን ማለት ነው? ምድር ከሰይጣን ቁጥጥር ትፈታለች። ትፈታለች። ከፖለቲካ ትፈታለች፡ ከሐይማኖት ተቋም ሥርዓቶች ትፈታለች፥ ለእግዚአብሔር መንግሥት ልትውል፡ እዚህ በምድር ላይ ልትመሠረት ትፈታለች። ነገር ግን በሰይጣን፡ በፖለቲካ... የምድር ገዥ በሆነው በሰይጣን እጅ እስካለች ድረስ፡ የርሱ ናት፥ የእርሱ ነበረች፡ አሁን ግን ክርስቶስ ዋጅቷታል።

181 በአንድ ወቅት፡ የእርሱ ንብረት ነበርኩ፡ ነገር ግን አሁን አይደለሁም። በአንድ ወቅት፡ ያቺ ምስኪን ሴት የእርሱ ንብረት ነበረች፡ ነገር ግን አሁን አይደለችም። አያችሁ፡ እርሱ እስራቱን ሊፈታ መጣ። እርሱ በሕይወቴ ላይ፡ በሕይወታችሁ ላይ የነበረውን፡ የኃጢአትን፡ የሰይጣንን እስራት ፈትቷል፡ አሁን የእርሱ አይደለንም።

182 ብዙ ጊዜ ሲጸልይ፡ “ከእግዚአብሔር ንብረት ላይ እጅህን አንሳ” ሲል፡ ሰምታችሁኛልን? አያችሁ? አሜን! የራሳችሁ የሆነውን ለማግኘት እምነት ይኑራችሁ። ያ መብታችሁ ነው። “ከእርሰዋ ላይ እጅህን አንሳ! ከእርሱ ላይ እጅህን አንሳ!” አያችሁ፡ እምነት ያደርገዋል። ኡህ፡ ማይ! መሉ በሙሉ ማጥፋት አይደለም፡ ነገር ግን፡ እንዲሁ፡ “ከእርሷ ላይ እጅህን አንሳ፡” ማስፈታት፡ ማስለቀቅ፡ ማሳለፍ ነው። ይለወጣል።

183 ምድር ትለወጣለች። ፖለቲካ ይለወጣል። ሐይማኖቶች ይለወጣሉ። የሐይማኖት ተቋሞች ያልፋሉ። ፖለቲካ ያልፋል። የእግዚአብሔር መንግሥት ትመሠረታለች።

184 በዮሐንስ ላይ እናነባለን፡ ዮሐንስን በራዕይ 6፡14 አንብቡ፡ አያችሁ፡ “እንደ መጽሐፍ ተጠቅልሎ አለፈ” ይላል። መጽሐፍ ቅዱስ የተናገረው... ያ... ዮሐንስ፡ “ሰማይና ምድር እንደ መጽሐፍ ተጠቅልለው ሲያልፉ አየሁ” አለ። ዮሐንስ፡ ራዕይ 6፥14 ላይ።

185 ኢየሱስ፡ “ሰማያትና ምድር ያልፋሉ” አለ፡ ወይም፡ በሌላ አነጋገር፡ “ሰማያትና ምድር ይለወጣሉ” ማለት ነው። አያችሁ፡ እዚያው እንደገና ያንኑ ቃል ተጠቅሟል።

186 አይ፡ ሙሉ በሙሉ መጥፋት አይደለም። ምክንያቱም፡ በኋላ፡ በራዕይ 21፡ 2 እስከ 24 ባለው፡ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ከእግዚአብሔር ዘንድ ከሰማይ ስትወርድና፡ በዚህች ምድር ላይ ስትቀመጥ እየ። ትጠፋለች ማለት አይደለም። ሥርዓቶቹ ይለወጣሉ።

187 ዳንኤል ተመሳሳይ ነገር አይቷል። አለት ዓለምን መታው፡ ያለ እጅም የተፈነቀለ ነበረ፥ የሥርዓቶቹም ምስል ሁሉ ፈራርሶ በበጋ አውድማ ላይ እንዳለ እብቅ ሆነ፡ ነፋሱም ጠረገው። ያም ዓለት፡ ራሱ፡ ምድርን ለመሸፈን ወደ ታላቅ ተራራ አደገ። አሁን ያንን ተራራ፡ ከትንሽ ቆይታ በኋላ ተመልከቱት። ያ ተራራ ምድርን ሸፈነ።

188 እንዲሁም ይህንን፡ እዚህ፡ በዚያ፡ በራዕይ ውስጥ፡ እንደገና፡ እናገኛለን፡ "የአዲሲቱ ምድር ነገሥታት ክብራቸውንና ሞገሳቸውን ወደ እርስዋ ያመጣሉ፡" አለ። በምድር ላይ፡ ተቀምጣለች... አዲሲቱ ኢየሩሳሌም በዚህች ምድር ላይ ተቀምጣለች። እያችሁ፡ ተለወጠች ብቻ።

189 እግዚአብሔር ሲጠራችሁ፡ በቁመናችሁ፡ ያው ከዚህ በፊት የነበርክ ሰው ነህ፡ አንቺም ያችው ሴት ነሽ። ሆኖም፡ እያችሁ፡ ያደረገው ነገር፡ ዳግም ልደት ነበረ። አሮጌው ሕይወት አለፈ። አሮጌው ፍላጎት አልፏል። መጠጣትና፡ መሳደብና፡ መነጫነጭና፡ መጨነቅና፡ መንከራተትና፡ ሥነ ምግባር የጎደለው ድርጊት ትወዱ በነበረበት፡ ጊዜ፡ ያ ነገር እንዲሁ ሞተ። እያችሁ? ነገር ግን አሁን እናንተ... ያኔ የሰይጣን መሣሪያ ነበራችሁ፥ አሁን ቤዛነትን አግኝታችኋል።

190 ዓለምም እንደዚሁ ትሆናለች፡ በተመሳሳይ መንገድ፡ ትዋጃለች፡ አዲስ ሰማያትና አዲስ ምድር።

191 ልክ እንደ እናንተ፡ "እናንተ አዲስ ፍጥረት ናችሁ።" ማንም እንደሚያውቀው፡ እዚያ ያለው የግሪኩም ቃል፡ "እናንተ አዲስ ፍጥረት ናችሁ፡" ይላል። አሜን! በዚያው ባረጀው ቤተ መቅደስ ውስጥ አዲስ ፍጥረት። ሃሌሉያ። አሁን እዚህ የሚሆነውን ተመልከቱ። የከበረ! መልካም።

192 አሁን ይህቺ ምድር የምድር ነገሥታትን እንደምትይዝ እናገኛለን።

193 እንዲሁም፡ እንደገና፡ በማቴዎስ 5፡5 ላይ፡ ኢየሱስ፡ "የዋሆች ምድርን ይወርሳሉ" አለ። ሌላ ምድር፡ ሊኖረን አይደለም። ያው ምድር ሊሆን ነው። ሌላ ምንም ነገር ማስተላለፍ ባልችል እንኳ፡ እያችሁ፡ ከምንም በፊት፡ የ— የቤዛነትን ዕቅድ ላስረዳችሁ እየሞከርኩ ነው። በእርስዋ ላይ የሚሆነው፡ የእሳት ጥምቀት፡ እርስዋን ለማንጻትና የዋሆቹ እንዲኖሩባት ተስማሚ ስፍራ ለማድረግ ብቻ ነው። እያችሁ? ኦህ!

194 እኛን፡ ፍጥረቶቹን፡ እንድንኖርበት እንዳደረገን ነው። ሊኖርበት ከመምጣቱ በፊት፡ የእሳት ጥምቀትን መስጠት ነበረበት፥ ከዚያም መንፈስ ቅዱስ መጥቶ ይኖራል፥ የእሳት ጥምቀት። ከዚያም፡ ያንን የእሳት ጥምቀት ስታገኙ፡ ያኔ መንፈስ ቅዱስ ሊገባ ይችላል። ምን? እንደሚያደርገው፡ ከቃሉ ጋር የሚቃረነውን ነገር ሁሉ፡ ከውስጣችሁ ያቃጥላል። እያችሁ? እርሱ ቃል ስለሆነ፡ ከቃሉ በቀር ሌላ ምንም አያምንም። እያችሁ? እያችሁ? እያችሁ?

195 አሁን፡ በቀደም ስንነጋገርበት የነበረው ያንን ነው፡ ስለ መንፈስ ቅዱስ ማረጋገጫ። እያችሁ? የመንፈስ ቅዱስ ማረጋገጫ ቃሉን መቀበል ስትችሉ ነው፥

ሌላ ሥርዓትን ሳይሆን፡ ግልጽ የሆነ መረዳት ሲኖራችሁ ነው። ቃሉ ግልጽ መሆኑን፡ መረዳታችሁን እንዴት ታውቃላችሁ? ራሱን ሲያጸና ተመልከቱት።

196 "መልካም፡" እናንተም፡ "**ይህ** ሲያደርገው እያለሁ፡ **ያኛውም**" ትላላችሁ። ኡህ፡ አዎ፡ አረሞችም በተመሳሳይ መንገድ ይኖራሉ። አያችሁ?

197 ነገር ግን ሙሉው ቃል መሆን አለበት። ሙሽራይቱ ለመሆን፡ የእርሱ አካል መሆን አለባችሁ። እርሱ ቃል ነው። አያችሁ? የእርሱ አካል የሆነውስ የትኛው ነው? እርሱ ሙሽራይቱን በሚጠራበት በዚህ ዘመን የተሰፋው ቃል የሆነው ቃል ነው። የዚያ አካል ሁኑ። ገባችሁን? አሁን፡ አ—አሁን ያንን አትሰቱ። አስተውሉ።

ዘላለምን ለመኖር ተሰማሚ ሰፍራ ያደርጋታል።

198 አስተውሉ፡ ይህ አሁንም የተጠቀሰው አይደለም... ይህ የሺህ ዓመቱ መንግሥት ግዛት፡ ሺህ ዓመት፡ አዲሲቱ ምድር አይደለም። አያችሁ፡ የሺህ ዓመቱ መንግሥት ግዛት የተለየ ግዛት ነው። እኛ የምንገባበት ያ ነው፥ የሺህ ዓመቱ መንግሥት፡ ነገር ግን ያ አዲሲቱ ምድር አይደለም፡ አዲሱ ሰማይ አይደለም። በፍጹም፡ አይደለም። ያ የማረፊያ ሥፍራ ብቻ ነው፡ አያችሁ፡ የእረፍት ጊዜ ነው እንጂ፥ በፍጹም አዲሱ ሰማያትና አዲሲቱ ምድር አይደለም፥ ምክንያቱም፡ አያችሁ፡ በሺህ ዓመቱ መንግሥት ውስጥ ወደዚያ የማይገቡ ነገሮች አሉን። ያ ኤደን ውስጥ የነበረው፡ የቀድሞው ሰባተኛው ቀን ምሳሌ ነው፥ ዓለምን ከፈጠረ በኋላ የነበረው፡ ሰባተኛው ቀን። በሰባተኛው ቀን፡ በኤደንና፡ በሺህ ዓመቱ መንግሥት ውስጥ አረፈ።

199 አያችሁ፡ ዓለም አሁን ወደ ሰድሰት ሺህ ዓመታት ገደማ፡ እድሜ ሆኗታል። አያችሁ? በእያንዳንዱ ሁለት ሺህ ዓመት ውስጥ አ—አንድ ጥፋት ነበራት። አያችሁ?

200 በመጀመሪያው ሁለት ሺህ፡ የጥፋት ውኃ መጣ፡ በ (ምን) አጠመቃት? በውኃ።

201 በሚቀጥለው ሁለት ሺህ፡ ኢየሱስ ሊቀድሳትና የራሱ ሊያደርጋት መጣ፡ ደሙን በእርሰዋ ላይ አንጠበጠበ፡ የራሱ ብሎ ጠራት። መልካም።

202 "እንደገና እመጣለሁ፡" ኡህ-ሃህ፡ አሁን እንደ ንጉሥ ከንግሥቲቱ ጋር፡ በሁለተኛው ሁለት ሺህ ዓመታት (ምን ያደርጋል? ) መጥቶ የእረፍት ጊዜውን ይሰጣታል።

203 ከዚያም ያቃጥላታል፡ የራሱም አድርጎ ይወስዳታል፥ የራሱ የሆኑቱን ወደ እርሰዋ ይመልሳል።

204 አስተውሉም፡ ይህ የሺህ ዓመቱ መንግሥት፡ ፍጹም ዓለም ሳይሆን፡ የሰባተኛው ቀን ምሳሌ ነው። ከዚያም ታላቁ ነጭ ዙፋን ፍርድ ይመጣል። አያችሁ፡ አሁንም ፍርድ አለን። በሺህ ዓመቱ መንግሥት ውስጥ፡ አሁንም በጊዜ ውስጥ ነን። አንድ ቀን ነው፥ አንድ ሺህ ዓመታት። የጊዜ አካል ነው። አሁን፡ ያንን ከአዲሲቱ ምድር ጋር አታደባልቁት፡ አይሁን፡ ምክንያቱም እንደዚያ አይደለም።

205 እንዲህ ልትሉኝ ትችላላችሁ። አሁን አንድ ሰው ይህንን እንደሚለኝ ይሰማኛል፡ ይህም፡ "አሁን፡ ወንድም ብራንሐም፡ አሁን ምን ልታደርግ ነው? ሙሉ የሆኑት ሰባቶች አልቀውብሃል። ታዲያ አሁን ምን ልታደርግ ነው? አሁን፡

የዘመናት ክፍፍል አማኝ ነህ” ትላላችሁ። እንዲሁ፡ ነኝና። እግዚአብሔርም፡ እንደዚያው እንደሆነ አምናለሁ። አስተውሉ፡ ልብ በሉ። “የዘመናት ክፍፍል ምሳሌዎች አልቀውብሃል። ምክንያቱም፡ ከዚያ ከሰባተኛው ቀን ባሻገር የሆነ ነገር ልታደርግ ከሆነ፡ እንዴት ልታገኘው ነው? አሁን ወዴት ልትሄድ ነው? ”

206 መልካም፡ ትኩረታችሁን ወደ አንድ ነገር እጠራለሁ፡ እያችሁ። ኧ-ህ። እያችሁ? ስለዚህ፡ ገና ነኝ—አሁንም፡ የዘመናት ሙላት አላጠናቀቅሁም። እዚህ ሌላ ጥቅስ አለኝ። አስታውሱም፡ ሁሉም፡ መፈጸም አለበት፡ እያንዳንዱ ክፍል። እያችሁ?

207 አሁን እናንተ እንዲህ ብላችኋል፡ “ወንድም ብራንሐም፡ ከሰባተኛው ቀን ባሻገር ሌላ ነገር ለማስቀመጥ፡ ከሰባተኛ-ቀን ሰንበት ሌላ እየፈለግክ ነው።”

208 እግዚአብሔር ምድርን ሰርቶ ስድስት ቀን እንደ ደከመ፡ በሰባተኛውም ማረፉ፥ የጊዜ፡ የጊዜ ምሳሌ ብቻ ነበረ። ሆኖም እኔ እዚህ የተናገርኩት፡ ዘላለማዊ እንሆናለን ነው።

209 “ስለዚህ አሁን ምሳሌህ የት አለ? በምሳሌዎች እንደምታምን ተናግረሃል። ስለዚህ፡ አንተ፡ አሁን ምሳሌዎች አልቀውብሃል።” አይ፡ ገና አልጨረስኩም። እንደጨረስኩ እስኪ እናረጋግጥ።

210 ወደ ዘሌዋውያን እንሂድ፡ ወደ ኋላ ወደ ዘሌዋውያን 23ኛ ምዕራፍ እንሂድ። አሁን ባለፈው እሑድ በነበርንበት በዘሌዋውያን ላይ፡ እንድታስተውሉ እፈልጋለሁ፡ ወይም ባለፈው… ሀሳቡን የሰጠኝ ይህ ነው፡ ልክ እዚህ ያለው። ዘሌዋውያን 23ኛ ምዕራፍና፡ 26ኛ ቁጥር።

211 አሁን አስታውሱ፡ ሰባት የበዓል ቀናት አሉ። የመለከት በዓል፥ የ—የዳስ በዓል፥ የነዶ-ማወዝወዝ በዓል፡ የ… ይህ ሁሉ፡ ሰባት ታላላቅ የበዓል ቀናት አሉ፡ እነዚያ የሰባቱ የቤተክርስቲያን ዘመናት ምሳሌዎች ብቻ ነበሩ። ከአንዱ እስከ ሌላው ድረስ ሰንት ሰንበቶች እንደነበሩ ታስታውሳላችሁን? እያችሁ፡ ከጴንጤቆስጤ እስከ መለከቶች ድረስ ሰባት ሰንበቶች ነበሩ፥ እነርሱም የሰባቱ ቤተክርስቲያን ዘመናት ናቸው። የሰባቱን የቤተክርስቲያን ዘመናት የሚወክሉ፡ ሰባት የበዓል ቀናትም ነበሩ። ቁጥሮቻችሁን አስኬዱ።

212 “መልካም፡ አሁን፡ ወንድም ብራንሐም፡ አልቆብሃል። ሰባቱን አግኝተሃል፡” ትላላችሁ።

213 መልካም፡ የመጨረሻውን በዓል እንውሰድ፡ እርሱም የዳስ በዓል ነው። አሁን እዚህ 36ኛውን ቁጥር አስተውሉ።

> **ሰባት ቀን ለእግዚአብሔር** **የእሳት** ቍርባንን አቅርቡ፥ **በስምንተኛውም ቀን የ—የተቀደሰ ጉባኤ ይሁንላችሁ** (ሌላ የሚመጣ የተቀደሰ ጊዜ አለ)… **የተቀደሰ ጉባኤ ይሁንላችሁ፥ ለእግዚአብሔርም የሚቃጠለውን ቍርባን አቅርቡ፥ ዋና ጉባኤ ነው፥ የተግባር ሥራ ሁሉ አታድርጉበት።**

214 ከዚያም “ስምንተኛ ቀን” ይኖረናል። አሁን፡ ሰባት ቀናት ብቻ አሉ፡ እዚህ ግን “ስምንተኛው ቀን፡” የተቀደሰ ጉባኤ፡ ጉባኤ ብለን እንናገራለን። አስተውሉ፡ “ሥራ አትሥሩበት።” ስምንተኛው ቀን፡ (ምንድነው? ) ወደ መጀመሪያው ቀን

መመለስ ነው። ለምን፡ የትም ሳታቆም ስትሽከረከር፡ ስለ ዘላለም ይናገራል። አሜን። አያችሁ?

215 አስተውሉ፡ ይህም የሆነው በዚህ በስምንተኛው ቀን ላይ ነበረ። የመጨረሻው ቀን፡ የዳስ በዓል ቀን፥ አስተውሉ ከዚያ በኋላ፡ ከመጨረሻው የበዓል ቀን በኋላ፡ ከመጨረሻው የቤተክርስቲያን ዘመን በኋላ፡ በምድር ላይ ካሉት የመጨረሻዎቹ ከፍጹም ሰባት ቀናት በኋላ፡ ከሺህ ዓመቱ መንግሥት በኋላ፡ ይህ የተቀደሰ ጉባኤ ይመጣል።

216 አስታውሱ፡ ይህ የዳስ በዓል ነው፥ **ዳሶች**፡ "የመሰብሰቢያ ሥፍራዎች።" አሜን! የት፡ "በሺህ ዓመቱ መንግሥት፡" መጽሐፍ ቅዱስ፡ "ቤቶችን ይሠራሉ፥ ይቀመጡባቸዋልም" ይላል።

217 ነገር ግን በአዲሲቱ ምድር፡ እርሱ ቀደም ብሎ ሄዶ ሥፍራ አዘጋጅቷል። ተገንብታለች። ከግንባታው ጋር ምንም የምናደርገው ነገር የለም። አሜን። ዘላለማዊ! ኦህ፡ ያንን ቃል እወደዋለሁ! ማይ! የተቀደሰ ጉባኤ፡ ስምንተኛው ቀን። ይኸውም፡ ሰባት ቀናት ብቻ ናቸው። ከዚያም ወደ መጀመሪያው ቀን ዳግም በሚመለሰው፡ ልክ ወደ መጀመሪያው ቀን በሚመለሰው፡ በስምንተኛው ቀን ላይ፡ ስምንተኛው ቀን የተቀደሰ ጉባ-... ጉባኤ ነው።

218 አስተውሉ፡ ሰባት ቀናት፡ ከቀድሞው ፍጥረት፡ ከዓለም ጊዜ ጋር ብቻ የተያያዘ ነው። ሰባት ቀናት፡ ያ የሺህ ዓመቱ መንግሥት ነው፡ የእረፍት ቀን። እግዚአብሔር ስድስት ቀን ደክሞ፡ በሰባተኛው እንዳረፈ፥ ቤተክርስቲያንም ስድስት ቀን ትደክማለች፡ በሰባተኛውም ታርፋለች፡ ነገር ግን እናንተ አሁንም በጊዜ አካል ውስጥ ናችሁ። ስለ ዘላለማዊ እየተናገርኩ አይደለም።

219 ነገር ግን፡ አያችሁ፡ ስምንት ቀናት የሚባል ነገር የለም፥ ዳግመኛ ወደ መጀመሪያው ቀን ትመለሳላችሁ፡ አያችሁ፡ ወደ መጀመሪያው ቀን።

220 ሰንበት ሊያልፍ ስለነበረው፡ ስለ አሮጌው ሕግ ይናገራል። ሰንበትን ማክበር፡ እርሱም "ያለፈ፡" ወይም፡ "ወደ ሌላ ተለውጧል፡" ብያቸዋለሁ። የሳምንቱን የሆነ ቀን ከመጠበቅ፡ ከአሮጌው ሕግ ተለወጠ እንጂ፥ አላለፈም።

221 እንዲህ ያለው፡ ኢሳይያስ፡ 19ኛው ምዕራፍ፡ 28፡19 ይመስለኛል፡ "ትዕዛዝ በትዕዛዝ ላይ፥ ጥቂት በዚህ፡ ጥቂት በዚያ መሆን አለበትና፡" አለ። "መልካም የሆነውን አጥብቃችሁ ያዙ።" "በሚንተባተብ ከንፈርና በሌላ ልሳን ለዚህ ሕዝብ እናገራለሁና። እረፍትም ይህች ናት።" አያችሁ?

222 ቀንን ወይም ጥላን ወደ መጠበቅ ሳይሆን፡ ወደ ሕይወት ትገባላችሁ። ጳውሎስ፡ እዚያ በዕብራውያን 4ኛ ምዕራፍ ላይ፡ "ቀናትንና ጥላዎችን፡ እንደዚያም ያሉ ነገሮችን ትጠብቃላችሁ፥ ስለ ልምምዳችሁ እፈራለሁ" አለ። አያችሁ፡ ወደ የሆነ አይነት ቀናትና ሥርዓቶች አናልፍም። "ከሞት ወደ ዘላለም ሕይወት ተሻግራችኋል፡" ወደ ቀናትና ጊዜያት አይደለም። ወደ ዘላለም ተሻግራችኋል። የተቀደሰ ጉባ-... ጉባኤ፡ ማለትም፡ ጉባኤ ያ ነው።

223 **ሰባት ቀናት፡** ተመልከቱ፡ "ያልፋል፡" ወይም፡ "ወደ ሌላ ይለወጣል፡" ብያቸዋለሁ። ስምንት ቀናት ከአዲሱ ፍጥረት ጋር ይያያዛል፡ አያችሁ፡ ከቀድሞው ፍጥረት ጋር አይደለም። ስምንት ቀናት አዲሱ ፍጥረት ነው።

224 ምክንያቱም፡ ጌታችን ከሙታን የተነሳው በሰምንተኛው ቀን ነበረና። ሌላኛው ጉባኤያችሁ ይሄውና፡ ቅድስና፥ ሰንበቶችን፡ በጭራሽ፡ ወይም የዳሰ በዓልን፥ **የዚህን** በዓልና፡ የጴንጤቆስጤን በዓል አያካትትም። ኢየሱስ ለጽድቃችን ሲል፡ በሰምንተኛው ቀን፡ ከሙታን ተነሳ። ከሰባቱ ሰንበቶች፡ ወይም ከሰባቱ ቀናት፡ ከሰባቱ የቤተክርስቲያን ዘመናት በኋላ፡ ኢየሱስ ከሙታን ተነሳ። ሰምንተኛው ቀን፡ የተቀደሰ ጉባኤ የሆነው፡ አያችሁ፡ እርሱም የመጀመሪያው ቀን ነው።

225 አያችሁ፡ እናንተ፡ አሁን በጊዜ ውስጥ አልፋችኋል፥ እንደገና ወደ ዘላለም ገብታችኋል፥ ቀናትን በመጠበቅና፡ ሰንበቶችን በመጠበቅ፥ አዲስ ጨረቃዎችንና፡ እንደዚያ ያሉ ነገሮችን በመጠበቅ አይደለም። "ነገር ግን **አልፏል**፡" መልካችሁን ቀይሯል እንጂ፥ ሙሉ በሙሉ አልጠፋም። ክብር! "ነገር ግን ከሞት ወደ ዘላለም ሕይወት ተሻግሯል።" ኦህ፡ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረን ይህንኑ ነው! አያችሁ፡ ከአንዱ ወደ ሌላው ማለፍ።

226 መልካም፡ "አልፏል፡" የቀድሞው ሰንበት አልፏል። ኢየሱስ በሰምንተኛው ቀን ተነሳ። ያ የተከበረ ቀን፡ የተቀደሰ ነበረ። ቀን አልነበረም፥ ምክንያቱም ቀን፡ ጊዜ፡ አሁን አብቅቷልና። ወደ ዘላለም አልፏል። አያችሁ፡ በቀጥታ ዳግመኛ ወደ መጀመሪያው ቀን ተመለሰ። አያችሁ?

227 ዘላለም እ—እንደ ቀለበት ነው። ማዕዘን ልታገኙለት አትችሉም። ፍጹም በሆነ ክብ ውስጥ የማቆሚያ ሰፍራ ልታገኙ አትችሉም። ዝም ብላችሁ ትቀጥላላችሁ። ምንም ያህል ሪቃችሁ ብትሄዱ ግድ አይሰጠኝም፡ አሁንም እየሄዳችሁ ነው። **እንደዚህ** መዞር መጀመር ትችላላችሁ፥ ወለሉን አልፋችሁ ሂዱ፡ ምድርን አልፋችሁ ሂዱ፡ ከምድር ባሻገር ሂዱ፡ አሁንም እየሄ-... [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ አለ—አርታዒ።]

228 **እዚህ** የተፈጠሩት ነገሮች ሁሉ፡ የተዛቡ እንጂ፡ በሰይጣን፡ የተፈጠሩ አይደሉም፡ ታላቁ የወርቅ ደወል ሲደወልና መለከት ሲነፋ ይጠፋሉ።

229 ያኔ ጥንት በመጀመሪያ፡ ኤደን ውስጥ የመሰረት ምሰሶ በተጣለ ጊዜ፡ ሰው ወደ ምድር መጥቶ በወደቀ ጊዜ፡ አንድ ትንሽ በግ ደሙን አፈሰሰ፡ ያም ታላቁ በግ ደሙን ሊያፈሰሰ እንደሚመጣ የሚናገር ነበረ። ቀራንዮ መሰቀሉን አነሳ፥ ይህም፡ ላጸደቃቸው፡ እርሱን ለተጠባበቁት፡ ለብሉይ ኪዳን ማሰሪያ ነበር። በዚህም አዲስ ዘመን፡ በጌታ መምጣት፡ በአዲሲቷ ምድር፡ የድነት ገመድ (ስለ እርሱ የምናገረው የቤዛነት ኃይል የሆነው፡ ደም፡ ሰውንም ምድርንም በዋጀው በዚያው መዋቅር አማካይነት) እንደገና በቀጥታ ወደ ዘላለም ከፍ ይላል። የእሳት ባሕርም ኃጢአተኛ የሆነውን ለእርሱም አስቀድሞ ያልተወሰነውን ሁሉ ያጠፋል። አያችሁ?

230 ልብ በሉ፡ በሰምንተኛው ቀን፡ ኢየሱስ እኛን ለማጽደቅ ተነሳ። ዘላለማዊው ንጉሥ፡ ተጠምቀን ወደምንገባበት፡ ዘላለማዊ መንግሥት፡ ለዘላለም ሕይወት። ሰባት ቀናት አይደለም፥ ከየትኛውም ቀናት ጋር ምንም ግንኙነት አልነበረውም። ስለ ሌላው፡ ስለ ዘላለማዊው፡ ስለመምጣቱ ይናገራል፥ እያወራሁት ስላለሁ፡ ስለ ዘላለማዊ ጊዜ ይናገራል።

231 እስተውሉም፡ ከአምሳ ቀናት በኋላ፡ ወይም፡ ከዚያ ጀምሮ ከሰባት ሰንበታት በኋላ፡ እንደገና ሌላ የተቀደሰ ጉባኤ ይመጣል። ምን ተፈጠረ? መንፈስ

ቅዱስ በጴንጤቆስጤ ቀን ወረደ፡ በሰባተኛው ቀን... ወይም፡ በስምንተኛው ቀን፡ ማለቴ፡ በስምንተኛው ቀን፡ የወረደው በስምንተኛው ቀን ነበር። ከትንሣኤው በኋላ፡ በትክክል፡ ከሰባት ሰንበታት በኋላ ነበር፡ አያችሁ፥ ስለዚህ ያ እንደገና ሰባት ጊዜ ይሆናል ማለት ነው፡ በትክክል፡ እንደገና ወደ መጀመሪያው የሳምንቱ ቀን መልሶ ያመጣዋል። አያችሁ?

232 የተቀደሰው ጉባኤያችሁ ያ ነው፡ ከቁሳዊ ነገሮች ጋር ምንም የሚያገናኘው ነገር የለም። ከዚያ ያለፈ ነው። ይህም ከዘላለም ሕይወት ጋር፡ እንዲሁም መቼም ቢሆን ጅማሬ ከሌላቸው፡ አስቀድመው ከተወሰኑት ጋር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት ነው። በምንም ቀን አልተጀመረም። በምንም ቀን አልዳናችሁም። ሁልጊዜም የዳናችሁ ነበራችሁ። አሜን። ኢየሱስ ያንን ለመዋጀት መጣ፥ ነገር ግን ከመጀመሪያው፡ የዳናችሁ ነበራችሁ፡ ምክንያቱም ገና ከመጀመሪያው፡ የዘላለም ሕይወት ነበራችሁ።

233 አንድ የትራውት ዓሣ መቼም ቢሆን ጋር ወይም ታድፖል ሊሆን አይችልም። አብሮት በአንድ ውኃ ውስጥ ሊኖር ይችላል፡ ነገር ግን እርሱ፡ ከመጀመሪያውም፡ ትራውት ነበረ። መረቡ ብቻ ነው ያጠመደው፡ አያችሁ፡ እርሱ ግን ከመጀመሪያውም እንደዚያ ነበረ። ይሄውና...

234 አሁን፡ ከዘመናት ክፍፍል አልወጣንም። ወጥተናል እንዴ? በትክክል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ነን። ከአምሳ ቀናት በኋላ፡ መጣ።

235 አያችሁ፡ ስምንት ከሳምንት ጋር ሊቆጠር አይችልም። አያችሁ፡ በሳምንት ውስጥ ስምንት ቀናት ተብሎ፡ ሊቆጠር አይችልም። ልታደርጉት አትችሉም፡ አያችሁ፡ ምክንያቱም በሳምንት ውስጥ ሰባት ቀናት ብቻ አሉ። በፈለጋችሁት መንገድ ቁጠሩት። እሁድ የሳምንቱ የመጀመሪያ ቀን ነው። አያችሁ፡ ሰባት ትቆጥራላችሁ፡ ከዚያም ተመልሳችሁ እንደገና መጀመር አለባችሁ። ሰባት ቁጠሩ፡ ተመልሳችሁ እንደገና ጀምሩ። አያችሁ?

236 በእነዚህ ሁሉ ምሳሌዎች ውስጥ አልፈናል፡ ነገር ግን፡ ስምንተኛው ላይ ስትደርሱ፡ ወደ ዘላለም ትገባላችሁ። የምትመጡት በሕግጋት፡ በሥርዓቶችና፡ በትእዛዛት አይደለም። የምትመጡት አስቀድሞ በመወሰን ነው። አሜን! እውነተኛና፡ ቅዱስ የሆነ ጉባኤ አለ! አያችሁ? እኛም ሰባተኛውን የቤተ ክርስቲያን ዘመን፡ የቤተ ክርስቲያን ዘመን የሆነውን፡ የጴንጤቆስጤን ዘመን እየጨረስን ነው። ይታያችኋልን? ወደዚያ ቅዱስ ጉባኤ እየገባን ነው። ቤተ ክርስቲያን ወደ ተጠራችበት፡ ወደዚያ እውነተኛ፡ ትክክለኛ ወደሆነው፡ ዘላለም እየገባን ነው፥ ጥሪዋም ወደ አንድ ሥፍራ፡ ወደ አንድ የሃይማኖት ተቋም ሳይሆን፡ ከዘላለማዊ ንጉሣቸው ጋር ወደ ዘላለም የሚደረግ ነው። አያችሁ? ያኔ፡ ነገሮችና፡ ጊዜያት የሚባሉ ነገሮች፡ ፈጽሞ የሉም። መጀመሪያ ወደ መጣችሁበት፡ ወደ ዘላለም፡ አልፋችሁ ገብታችኋል። ገና ከመጀመሪያውም እዚያው ነበራችሁ። አያችሁ?

237 የዘላለም ሕይወት ካላችሁ፡ ያለው አንድ መልክ ብቻ ነው፡ እርሱም እግዚአብሔር ነው፡ እናንተም የተገለጠው የእርሱ ባሕርይ ናችሁ። አያችሁ? ካል... ካልሆናችሁ፡ ምንም ቢሆን፡ እዚያ አትሆኑም። "አባቴ ከሳበው በቀር ማንም ወደ እኔ ሊመጣ አይችልም።" አያችሁ? እነዚህ፡ የቀድሞ ነገሮች ሁሉ፡ "ያልፋሉ፡" ነገር ግን እነዚህ ነገሮች አያልፉም፡ ስለዚህ ስለ ዘላለም ይናገራል።

መንፈስ ቅዱስ ዘላለማዊ ነው። ስለዚህ፡ ሁልጊዜም በነበራችሁበት፡ ዘላለም ውስጥ ናችሁ፡ ነገር ግን አሁን ምን እንደሆነ ተገነዘባችሁ።

238 አያችሁ፡ ለዘላለማዊ ዓላማ ነው የተፈጠራችሁት፡ ምክንያቱም ስ— ስለ እናንተ ባሰበውና በገለጣችሁ፡ በእግዚአብሔር ውስጥ የነበረው ባሕርይ መገለጫ ነበራችሁ፥ እናንተን ከዚያ አውጥቶ፡ የሰው ልጅ ሊያደርጋችሁ ምድርን ፈጠረ። ኃጢአትም መጣና መንገዱን አጣመመው። ምንም ቢሆን ግን፡ መጣችሁ፡ ነገር ግን ከዓለም ጋር ጠፍታችሁ ነበር። ስለዚህ እርሱ መጣና የተገለጠውን ባሕርይ፡ እናንተን ዋጃችሁ፡ እንዲሁም ይህችን ምድር በተመሳሳይ መንገድ ይዋጃታል። ከዚያም፡ ዓላማው ይቀጥላል። አያችሁ? ኦህ! ሃሌሉያ! ኦህ፡ ከፊት ለፊታችን ስላለው ነገር ማሰብ ብቻ፡ ታላቅ ደስታ ይሰጠኛል!

239 አሁን፡ በኤፌሶን 1፥10 ላይ፡ እንዲህ ተብሎ... አሁን፡ እየጻፋችሁት ከሆነ፡ ኤፌሶን 1፥10፡ የሚጠራው፡ የዘመን ክፍፍል ተብሎ አይደለም፡ ሰባተኛው ቀንም ተብሎ አይደለም። የሚጠራው፡ "የዘመን ፍጻሜ" ተብሎ ነው። "የዘመን ፍጻሜ" ሲደርስ፡ ጊዜ የተፈጸመው ያኔ ነው። ጊዜ ከእንግዲህ በማይኖርበት ጊዜ፡ ሰባተኛው የቤተክርስቲያን ዘመን ካለቀ በኋላ፡ ወደ ዘላለም ትገባላችሁ፡ አልቋልም፥ የሉተር ዘመን አልቋል፡ የሜቶዲስት ዘመን አልቋል፡ የጴንጤቆስጤ ዘመን አልቋል። አሁንም ወደ (ምን?) ዘላለም ትገባላችሁ፥ ከእንግዲህ ሰባቶች የሉም፡ ከእንግዲህ ሦስቶች የሉም፡ ከእንግዲህ ሌላ የለም። እነርሱ ቁጥሮች፡ ጊዜያት፡ እንዲሁም ነገሮች በሚባሉበት ጊዜ በሌለበት ሰፍራ፡ በዘላለም ውስጥ ናቸው። አሜን! ኦህ፡ ማይ! አሁን አያችሁት?

240 ወይም፡ ጊዜ ከተፈጸመ በኋላ፡ ኃጢአት ሁሉ አልፎ፡ በሺህ ዓመቱ መንግሥት፡ በታላቁ ነጭ ዙፋን ፍርድ ላይ፡ ተወግዷል። (በመንፈስ ቅዱስ የተደረገ፡ ምሳሌ ነው።) ዓለም በእሳት ከተያያዘችና ከተጠመቀች በኋላ፡ ከሰማይ በሚመጣው በተቀደሰ እሳት ጥምቀቷ፥ ኃጢአት ሁሉ ጠፍቷል፡ ጀርሞች ሁሉ ጠፍተዋል፡ አጋንንት ሁሉ ጠፍተዋል፡ ፈተናዎች ሁሉ ጠፍተዋል፡ ክፋት ሁሉ ጠፍቷል። (አሁን ጥላውን እዩ።) ከዚያ እግዚአብሔር ምን ያደርጋል? በምድር ላይ ሊቀመጥ ይችላል፡ አያችሁ፡ ምክንያቱም ኃጢአት ሁሉ ጠፍቷል።

241 የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት በእሳት ሲሰጣችሁ እርሱ የሚያደርገው ያንኑ ነው። መጥቶ ከእናንተ ጋር ሊኖር ይችላል፡ እኛም በክርስቶስ ኢየሱስ በሰማያዊ ሰፍራዎች ልንቀመጥ እንችላለን፡ ምክንያቱም አስቀድመን በእርሱ ውስጥ ነንና። ወደፊት "እንሆናለን" አይደልም። አሁን በክርስቶስ ኢየሱስ ውስጥ ተቀምጠናል። ወደዚህ እንዴት እንገባለን? በአንድ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት። "በአንድ መንፈስ ሁላችን ወደ ክርስቶስ ተጠምቀናል፡" ማለት፡ አሁን በውስጡ ነን። በክርስቶስ ውስጥ፥ "እንሆናለን" ሳይሆን፡ አሁን ነን! እርሱ በእኛ ውስጥ ላለው መንፈስ ታላቅ መንፈሳዊ ንጉሥ ነው፡ ምክንያቱም በመጀመሪያ በእርሱ ውስጥ ነበርንና።

242 አያችሁ፡ እግዚአብሔር፡ በመጀመሪያ፡ ስለ እናንተ ሲያስብና እንደዚያ ስላሉት ሌሎች ሲያስብ፡ ራሱ የሚዳሰስ ስለመሆን አሰበ። ሃሳቦቹ ያ ነበሩ።

እያችሁ? ስለዚህ፡ ሃሳቦቹን በቃል ገለጠ። እርሱ "ይሁን፡" አለ። "ይሁን፡" ሆነም። "ይሁን፡" ሆነም።

243 ከዚያም፡ ከጥቂት ጊዜ በኋላ፡ ሕዝቡ፡ አንድ ቀን፡ "እግዚአብሔር አይናገረን፡" እስኪሉ ድረስ "ይሁን" ማለቱን ቀጠለ!

244 እርሱም፡ "አሁን በነቢይ በኩል እናግራቸዋለሁ" አለ። እያችሁ? "ከእንግዲህ ወዲህ፡ በነቢይ በኩል እናግራቸዋለሁ።"

245 ነቢዩም እንዲህ አለ፡ "ይመጣል፥ ይሆናል፡" ሆነ፡ ሆነ። ሆነ፡ ሆነ፡ እያችሁ፡ ልክ እንደዚያው ሆነ። አሁን ገባችሁ?

246 "የዘመን ፍጻሜ" የመጣው ጊዜ ከተፈጸመ በኋላ ነው። ከዓለም ጥምቀት በኋላ፡ የዓለም ጥምቀት ተስማሚ ሰፍራ ካደረጋት በኋላ፡ ኃጢአት ጠፍቷል፥ በሽታ የለም፡ ጀርሞች የሉም፥ እሾህ የለም፡ አሜኬላ የለም፥ ሞት የለም፡ ሐዘን የለም፡ የልብ ስብራት የለም፥ እርጅና የለም፡ ሞትን የሚወክል ምንም ነገር የለም፥ ምንም የተሳሳተ ነገር የለም፥ ሁሉም ትክክል ነው፥ ምንም ተፈጥሯዊ ነገር የለም። ዘላለማዊ!

247 ከዚያም፡ የእርሱ ባሕርይ ይገለጣል ምክንያቱም ገና፡ ከመጀመሪያው፡ እዚያው ነበር። ያ እሱ ያሰበው ነበር። [ወንድም ብራንሐም በሰሌዳ ላይ ያሳያል—እርታዒ።]

248 ከዚያስ ምን ተፈጠረ? አዳምንና ሔዋንን እዚህ ምድር ላይ አስቀመጣቸውና፡ "አሁን ተባዙ፡ ምድርንም ሙሉአት" አላቸው። ሥጋቸው እዚህ ተቀምጦ ነበር፡ ይህም እንድትበሉና ሰውነታችሁን እንድትገነቡ ነበር። ያደረገው እንደዚያ ነበር።

249 ነገር ግን ኃጢአት መጣና ዕቅዱን አበላሸው። እሷም በተመሳሳይ መንገድ፡ ትቀጥላለች፡ ጊዜም እንደዛው።

250 ነገር ግን ኢየሱስ ምን አደረገ? እግዚአብሔር ወረደና ራሱን በሰው መልክ፡ በሰው ልጅ መልክ ገለጠ፥ እዚህ ከመቆየት ይልቅ፡ ሕይወቱን አሳልፎ ሰጠ። እርሱም፡ ንጉሥ ነበረ፡ ነገር ግን ሌሎቹን ለመዋጀት ራሱን አሳልፎ ሰጠ። ገባችሁ?

251 ሁሉም ነገር ሲጠነቀቅ፡ ከዚያም በትክክል ወደ ቦታው ይመለሳል፡ የእግዚአብሔርም ዓላማ ይፈጸማል። ዘላለማዊው ንጉሥ ከዘላለማዊ ተገዢዎቹ ጋር፡ በሰው ሥጋ ተገልጦ፡ ልክ እርሱ ባደረገው መንገድ እንደገና በዚያ ይሆናል፥ ኃጢአት ተወግዷል፥ ዲያብሎስ ጠፍቷል፥ አሁን ሁሉም ተፈጽሟል።

252 ያንን የሚያደርገው ምንድን ነው? ይህች ምድር አሁን ሰማይ ሊቀመጥባት የምትችል ሰፍራ መሆን አትችልም። ተመልከቱት፡ ኃጢአቱን። መነጻት ይኖርበታል።

253 ማንም ሰው፡ የትኛውም ወንድ፡ ሴት፡ ወንድ ልጅ፡ ሴት ልጅ፡ ማንም ቢሆን ግድ የለኝም፡ በመንፈስ ቅዱስ ሳይሞላ፥ ወደ መድረክ መውጣት፡ ወይም ክርስቲያን ነኝ ብሎ ለመናገር እንኳ የሚገባው የለም። በእግዚአብሔር ቅዱስ እሳት እስካላነጻችሁ ድረስ፡ ለጌታ እራት፡ ወይም ለማንኛውም ኅብረት፡ እግር-መተጣጠብ፡ ወይም ለማንኛውም ነገር መብት የላችሁም።

254 ማንም ሰው፡ ልክ እንደ ሙሴ፡ በዚያ በተቀደሰው ሥፍራ ላይ፡ ያ የእሳት ዓምድ በዚያ ተንጠልጥሎ ባለበትና፡ የት እንደቆመ በእርግጠኝነት በሚያውቅበት ሁኔታ ከእርሱ ጋር ካልተገናኘ በቀር የመሰበክ መብት የለውም። አያችሁ?

255 እንዴት፡ እንዴት እንደምንጓዝ አስተውሉ። ከዓለም የእሳት ጥምቀት በኋላ፡ ጀርሞች በሙሉ ይጠፋሉ፡ ከዚያም ሰማይ እዚህ ምድር ላይ እንዲኖር የተገባ ስፍራ ያደርገዋል።

256 አሁን ይህ፡ ያቺ ምስኪን ሴት እንደነበረችው፡ ቆሻሻ ከሆነው ከዚህ ሁኔታ አልፎ፡ ወደ ተገለጠው የእግዚአብሔር ባሕርይ ውስጥ በመግባት፡ በክርስቶስ ኢየሱስ በሰማያዊ ሥፍራዎች የመቀመጥ፡ ምሳሌ ነው። "አሁን የእግዚአብሔር ልጆች ነን፡" እንጂ ወደፊት **እንሆናለን** አይደለም። የእግዚአብሔር አሳብ ባህርያት ነን። አያችሁ?

257 አሁን እናንተ፡ "መልካም፡ ይህን ካህን ተመልከት። እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ አልነበረምን" ትሉ ይሆናል? እንዳይደለ አረጋግጧል። ምንን ነበር ማስተዋል ያልቻለው? "መጽሐፍ ቅዱስን አምናለሁ፡" ብሎ ነበር እንዴ? አዎን። ነገር ግን የዘመኑን የተገለጠ ቃል ማወቅ አልቻለም። ከእርሱ በፊት ከነበረ አንድ ቡድን ያገኘው ምሁራዊ ትምህርት ብቻ ነበር የነበረው።

258 ዛሬም ያው ተመሳሳይ ነገር ነው! አያችሁ? ይህ ከባድ እንደሆነ አውቃለሁ፡ ነገር ግን እውነት ነው።

259 ለዚያ ዘመን በትክክል እንደተነገረው፡ ቃሉ በዚያ ነበረ፥ እርሱም፡ ምሁር ቢሆንም፡ ታዋቂ ሰው ቢሆንም፡ ሆኖም፡ ሊያውቀው አልቻለም። ለምን? ምንም ያህል ምሁር ቢሆንም፡ ወይም እንደዛ ያለ ሌላ ነገር ቢሆንም፡ ሆኖም የአስቀድሞ የመወሰን ውክልና አልነበረውም። አያችሁ?

260 አስቀድመው የተወሰኑት ብቻ ናቸው ያንን የሚያደርጉ የሚሆኑት፥ እነርሱ ብቻ ናቸው የሚችሉት። ልታደርጉት የምትችሉት እናንተ ብቻ... ምክንያቱም፡ ተመልከቱ፡ ይህ አስቀድሞ መወሰንን ያረጋግጣል። ምክንያቱም፡ የዘላለም ሕይወት ካላችሁ፡ ሁል ጊዜ የእግዚአብሔር አካል መሆን ነበረባችሁ፥ ምክንያቱም ዘላለማዊ የሆነው እርሱ ብቻ ነውና። አያችሁ? ኡህ፡ ማይ! እስቲ አስቡት።

261 አሁን በታላቁ የሺህ ዓመት ግዛት ውስጥ ምን እንደሚሆን አስተውሉ። ኃጢአት በሙሉ ጠፍቷል፡ የሺህ ዓመት ግዛት አሁን ገብቷል፡ አሁን መንፈስ ቅዱስ ስፍራውን የሚይዝበት ጊዜ ነው።

262 ልክ በእኛ ውስጥ እንደሚያደርገው፡ "ከሞት ወደ ሕይወት ተሻግሮ፡" በክቡር ሕልውናው ውስጥ፡ በክርስቶስ በሰማያዊ ሥፍራዎች መኖር ነው። ልክ አሁን መንፈሳዊ ሞት እንዳለፈ ሁሉ፥ በዚያን ጊዜ የስጋ ሞትም እንኳ ያልፋል።

263 እንግዲህ ለተጠመቀው የ—የ—የእግዚአብሔር ቅዱስ፡ መንፈሳዊ ሞት የሚባል ነገር ፈጽሞ የለም። "ቢሞት እንኳ፡ ሕያው ይሆናል። ሕያው የሆነውና የሚያምንብኝ ሁሉ ለዘላለም አይሞትም።" ቅዱስ ቃሉ ሁሉ፡ ሊፈጸም ይገባዋል። አያችሁ? ልትሞቱ አትችሉም። የዘላለም ሕይወት አላችሁ። ብቸኛው ነገር ቢኖር፡ ቤዛው ይህንን እንድታስተውሉ ማድረጉ

ነው። እናንተም ሁልጊዜ እንደዚያው ነበራችሁ፡ የምትኖሩበትንም ዘመን የምታስተውሉበት ምክንያትም ይኸው ነው። ስንቶቻችሁ ይታያችኋል? እጃችሁን አውጡ። አያችሁ? አመሰግናለሁ። አያችሁ? እየኖርንበት ያለውን ዘመን ታስተውሉታላችሁ።

264 አሁን፡ ሜቶዲስት፡ “ስትጮኹ፡ አግኝታችሁታል” አለች። ብዙዎቹ ጮኹ ሆኖም አላገኙትም ነበር።

265 ጴንጤቆስጤ፡ “በልሳን ስትናገሩ፡ አግኝታችሁታል” አለች። ብዙዎች በልሳን ይናገራሉ፡ ሆኖም አላገኙትም ነበር።

266 እነዚያ ፈሪሳውያን እንዴት ሁሉም አይነት ሥርዓቶች እንደነበሯቸው፡ ተመልከቱ፡ ነገር ግን ቃሉ በተገለጠ ጊዜ፡ አላስተዋሉትም ነበር። አያችሁ? አያችሁ?

267 እናንተም ሙሽራይቱ ከሆናችሁ፡ ሙሽራይቱ የባሏ አካል ናት። እናም... ያንን ልታስተውሉት የምትችሉበት ብቸኛ ሰፍራ፡ የዚያ ባል (የዚያ ቃል) የትኛው አካል እንደ ሆናችሁ ማወቅ ነው፡ አለበለዚያ ሙሽራይቱ መሆናችሁን ልታስተውሉ አትችሉም። ስንቶቻችሁ ይህንን ታያላችሁ? አያችሁ? አያችሁ? ቦታችሁን ማወቅ አለባችሁ።

268 የሌላውን ሰው ሰፍራ ልታውቁ አትችሉም። ሙሴ በኖኅ መልእክት መጥቶ ቢሆን ኖሮስ ም—ምን ይሆን ነበር? ኖኅም የዚያ አካል ነበረ፡ ነገር ግን አይሰራም ነበር። ኢ—ኢ—ኢ—ኢየሱስ በሙሴ መልእክት መጥቶ ቢሆን ኖሮስ ምን ይሆን ነበር? አይሰራም ነበር። አያችሁ፡ የተለየ ዘመን ነበረ፡ የተለየ ትንቢት ነበረ፡ የተለየ የቃሉ ክፍል በዚያ መፈጸም ነበረበት። በሌላ የሳምንቱ ቀን ውስጥ ነበሩ። አይ፡ የማክሰኞ ሥራ በረቡዕ ሊሠራ አይችልም። የረቡዕም በረቡዕ መሠራት አለበት። አያችሁ? ቅዳሜ የቅዳሜ ሥራ መሆን አለበት። አያችሁ?

እነርሱም፡ “ኦህ፡ ሙሴ፡ እኛ ሙሴ አለን፡” ብለው፡ ተገንዝበው ነበር።

269 እርሱም፡ “ሙሴንስ ብታውቁት ኖሮ፡ እኔን ባወቃችሁኝ ነበር፡ ስለ እኔ የተናገረው እርሱ ራሱ ነበረና። ‘ጌታ አምላካችሁ እንደ እኔ ያለ ነቢይ ያስነሳላችኋል’” አለ። ሀሳቡን ተረድታችኋልን? ኦህ፡ ማይ! አያችሁ?

270 ከዚያም ኢየሱስ፡ በዮሐንስ 14 ላይ፡ “እርሱ፡ መንፈስ ቅዱስ፡ በመጣ ጊዜ፡ እነዚህን ነገሮች ያሳስባችኋል” አለ። አያችሁ? በየትኛው ዘመን ውስጥ እየኖራችሁ እንደሆነ ያሳያችኋል። ከዚያም፡ እርሱን የምታውቁበት ሌላው ነገር፥ “ሊመጡ ያሉትን ነገሮች ያሳያችኋል” አለ። አያችሁ? አያችሁ? እንደገና በቀጥታ ወደ ትንቢታዊው ስንመለስ፡ “እርሱ ሲመጣ” ይላል። አያችሁ?

271 ይህች አዲሲቱ ምድር ስትመጣ፡ በአዲሱ ሰማይና በአዲሲቱ ምድር ውስጥ፡ ዳግመኛ መቼም አይጠቁርም። ዲያብሎስ ይታሰራል... ሰይጣን፡ አሁንም ተፈትቶ ነው ያለው፥ እርሱ ከሳሽ ነው። ነገር ግን በአዲሲቱ ምድር፡ ታስሮ በዚህ ቅዱስ እሳት ውስጥ፡ ወደ እሳት ባሕር ይጣላል።

272 ከዚያም፡ በዚህች አዲሲቱ ምድር፡ እስቲ አሁን ለጥቂት ደቂቃዎች እንመልከተው። በዚህች አዲሲቱ ምድር፡ ሰማያት ዳግመኛ ፈጽሞ አይጠቁሩም፥ አይ፡ ያ ከእርግማኑ የተነሳ ነው፡ አያችሁ። በቁጡ ደመናዎች

ዳግመኛ ፈጽሞ አይጠቁሩም። ነፋሳትም እንደዚያ በእርሰዋ ላይ ዳግመኛ ፈጽሞ አይነፍሱም። አይ። ዛፎችን ፈጽሞ አትነቅልም፡ ቤቶችንም አታፈርሰም፡ ነገሮችንም አትገለብጥም። መብረቅና ቁጣ ከሰይጣን ዘንድ ተፈናጥረው በዚያ ላይ በመውረድ፡ በመንገድ ላይ የሚሄድን ሰው መቼም አይገድሉም፡ ወይም ሕጻንን አያቃጥሉም። አያችሁ? አይ፡ ከእንግዲህ አይኖርም። ከእንግዲህ ወዲህ ታይፎኖች ጠራርገው የሚወርዱበት፡ ወይም ማዕበሎችና ቶርኔዶዎች፡ መጥተው ቤቶችን የሚያፈርሱበት፡ ትንንሽ ልጆችን የሚገድሉበትና፡ የመሳሰሉት ነገሮች ፈጽሞ አይኖሩም። ሃሀ-ኡሀ፡ ከእንግዲህ አይኖርም። ለማጥፋት መሞከር፡ እዚያ አይኖርም። ሰይጣን ወደ ውጭ ተጥሏል።

273 አሁን ጊዜ በኖረን ብዬ እመኛለሁ። በጣም እንዳንረፍድ ብዬ፡ አሁን፡ የቅዱስ ቃሉን ጥቅሶች እንዲሁ እያለፍኳቸው ነው። ለታመሙት መጸለይ አለብኝ።

274 ሰማያትና ምድር ተገናኝተዋል፥ እግዚአብሔርና ሰው ታርቀዋል። ወደ ቀድሞ ሁኔታዋ የተመለሰችው ኤደን ጀምራለች፥ አያችሁ፡ እርግማኑ በሙሉ ጠፍቷል።

275 ልክ፡ መንፈሰ ቅዱስ ሲቀበላችሁ የኃጢአት እርግማን በሙሉ እንደሚጠፋው ነው። አያችሁ፡ እናንተ አትቀበሉትም፥ እርሱ ይቀበላችኋል፡ አያችሁ፡ ምክንያቱም እርሱ የእግዚአብሔር ባህርይ ነውና። አያችሁ፡ መንፈሰ ቅዱስ ከሆነ፡ ትርጉሙም፡ የእግዚአብሔር መንፈሰ ማለት ነው፥ እንዲሁም ለዚያ ዓላማ ስለተሾማችሁ የተቀበላችሁ፡ የእግዚአብሔር ባህርይ፡ የእግዚአብሔር አሳብ ነው። አያችሁ? ሆኖም፡ በኃጢአት ተወለዳችሁ፥ ነገር ግን እግዚአብሔር ያ ባህርይ ነበረው፡ እዚህ ምድር ላይም ራሳችሁን ገለጣችሁ፡ እርሱም ወርዶ ይወሰዳችኋል። አያችሁ፡ **እዚህ** ተመልሳችኋል፥ መሆን ያለባችሁ **እዚህ** ነው። አያችሁ? አያችሁ፡ ኃጢአት ኃይሉን አጥቷል። በትክክል። መንፈሰ ቅዱስ ሲገባ፡ የኃጢአት መሻት ከልባችሁ ፈጽሞ ጠፍቷል። የተቃና ሰው ናችሁ።

276 ከዚያም ምድር በተመሳሳይ ሁኔታ፡ ወደ ቀድሞ ሁኔታዋ ስትመለስ፡ ከእንግዲህ እርግማን፡ ከእንግዲህ ማዕበሎች፡ ከእንግዲህ ነፋሳት፡ ማ— ማለትም፡ ታይፉኖች ሊኖሩ አይችሉም። ታርቃችኋል፥ ሰውና እግዚአብሔር ተገናኝተዋል። አዲሲቱ ምድር የኤደን ውበቷን እንደገና ትላበሳለች። አዲሲቱ ምድር፡ ከእሳት ጥምቀቷ በኋላ፡ ወደ ፊት ትሰፋፋለች።

277 ብቻ አሰቡት፡ በእሳት ተያይዛ ትቃጠላለች። የሰማይም ፍጥረት በ— በትልቅ ትኩሳት ይቃጠላል። በምድር ላይ ያሉ ሥራዎች ሁሉ ይቃጠላሉ። ውኃ ሁሉ ይፈነዳል፥ ይነድዳል ሁሉንም ያፈነዳዋል። ሁሉም ነገር ይፈነዳል። እሳተ ገሞራዎች ይፈነዳሉ፡ የሚያቃጥል ላቫም ወደ አየር፡ በሺዎች ለሚቆጠሩ ማይሎች ይፈናጠራል። ጀርሞች በሙሉ... የእግዚአብሔር መንፈሰ ቅዱስ የኃጢአትንና ሁሉንም ነገር ጠራርጎ ያነጻል። ዲያብሎስ ሁሉ ይታሰራል በሚባላው እሳት፡ በእግዚአብሔር የቁጣ እሳት፡ ወደ እሳት ባሕርም ይጣላል።

278 እንደገና ሊያጠፋችሁ የሚችል አውሬ በዚያ አይኖርም። በመንገድ ላይ ስትራመዱ፡ በአትክልት ሰፍራ አበባዎች መካከል፡ በመርዙ ሊነድፋችሁና፡ ሊያሾፍባችሁ የሚችል ምንም ዓይነት እባብ በዚያ አይኖርም። ኑ፡ ማይ! አሰደናቂ

አይሆንምን? አዳምጡ። ለመቃብር ተብሎ፡ የተከመረ ትንሽ ቢጫ የአፈር ክምር ከእንግዲህ በዚያች አዲሲቱ ምድር ፈጽሞ አይኖርም፥ አንዳቸውም በዚያ አይኖሩም።

279 ሰውና እግዚአብሔር ተገናኝተዋል፥ ሙሽራይቱና ሙሽራው። ሰማያትና ምድር እርስ በርስ ተቃቅፈዋል፥ እግዚአብሔር በሰዎች መካከል ሊያድር ወርዷል። ማደሪያው ከእነርሱ ጋር ነው።

280 ከእንግዲህ ኃጢአት አይኖርም፡ ከእንግዲህ ሐዘን አይኖርም። በእናት ጉንጭ ላይ፡ በልጅዋ ምክንያት የእንባ ዘለላ ፈጽሞ አይወርድም። አሜን። በዚያ አዲስ ምድር ላይ፡ ያ አይሆንም። አይ። ተዋጅታለች። የእርሱ ናት፥ እንዲሁም ከእርሰዋ ለተዋጁት የእርሱ ለሆኑት ናት። አያችሁ?

281 እንዲሁም፡ ተመልከቱ፡ እናንተ የዚያች ምድር አካል ናችሁ። ልክ ነውን? ሲቤዣችሁ፡ ምድርንም በተመሳሳይ ነገር ተቤዣት፡ እንደገና አንድላይ ሆናችኋል። ኦህ፡ ከዚህ የበለጠ እንዴት ግልጽ ሊሆን ይችላል? አያችሁ? የእርሰዋ አካል ስለሆናችሁ መዋጀት አለባችሁ። ደሙ በላያችሁ ላይ ካልፈሰሰ፡ ገና አልተዋጃችሁም፥ አልተጠራችሁም። ከዚያም ያነጻዋል፥ ያም በእሳት የሚያደርገው ተመሳሳይ ነገር ነው። ደሙ ቢፈስም፡ እንኳ፡ ለእግዚአብሔር ማደሪያ ስፍራ እንዲሆን፡ ገና በእሳት መነጻት አለበት፡ በትክክል።

282 እግዚአብሔር በተዘዋዋሪ እንደ ቀብድ፡ ማደሪያውን እዚህ አድርጓል፥ የእግዚአብሔር መንግሥት አሁን በምድር ላይ፡ በቅዱሳኑ ልብ ውስጥ ትገኛለች። ይህም በመጀመሪያ የጀመረው የእርሱ ባህርያት ነው። አሁንም ባህርያቱ ተዋጅተዋል። ምን እየጠበቀ ነው? ምድርን ለመዋጀት፡ ባህርያቱን በላዩዋ ላይ ለማኖር፡ አስቀድሞ የወሰነውን ዕቅድ በትክክል ለመፈጸም ነው። አያችሁ?

283 አስተውሉ፡ ከእንግዲህ መቃብሮች፡ የእንባ ዘለላዎች፡ ፈጽሞ፡ የደም መፋሰስም አይኖሩም። በእንባ ዘለላ ወይም በደም ዳግመኛ ፈጽሞ አትርሰም። አይ። ከእንግዲህ ጦርነቶች አይኖሩም። አይ። የክረምት ደመናዎች አይኖሩም። በጡቶቿ ላይ ምንም ዓይነት ቀዝቃዛ በረዶ አይኖርም፥ ከእንግዲህ ወዲህ በዚያ ላይ አያርፍም። ትኩሱ ፀሐይ ሳሩዋን ፈጽሞ፡ አያቃጥለውም። ሃሌሉያ! በረሃውም እንኳ ጽጌረዳዎችን ያበቅላል። “ያ የቀድሞ፡ እሾሃማ በረሃ፡ አንድ ቀን፡ እንደ ጽጌረዳ ያብባል፡” እግዚአብሔር እንደዛ ብሏልና፥ ስትዋጅ፡ የእሳት ጥምቀቷን ስትወስድ እንደዛ ትሆናለች። አሁን በዚያ ሁሉም ዓይነት ቁልቋሎችና እሾሆች ሁሉም ነገሮች አሉ፡ ነገር ግን የእሳት ጥምቀት እየመጣላት ነው።

284 ልክ አንድ ሰው በውስጡ ገና ጥላቻ፡ ክፋትና ጠብ በነበረበት ጊዜ እንደነበረው ማለት ነው፥ የእሳት ጥምቀት ሲመጣ፡ ያንን ጠራርጎ አነጻው። ከእንግዲህ ቅናት፡ ምንም ነገር የለም፥ ፍጹም ለእግዚአብሔር ማደሪያ ስፍራ ሆኗል። አስታውሱም፡ እዚያ ማዶ፡ እርሱን የሚያገኙት የእርሱ ልዑካን ናቸው። አሜን! ኦህ፡ እንዴት ያለ...

285 ያ ዝም ብሎ ታርክ አይደለም፥ ያ እውነት ነው። እግዚአብሔርም ያለው ያንን ነው። እርሱ ቃል የገባው ያንን ነው። ሙሽራይቱም የምትሄደው ወደዚያው ነው። “በረሃውም እንኳ፡” እርሱም፡ “ያብባል፡ ጽጌረዳ ይሆናል” አለ።

286 ሰይጣን፡ ኃጢአትና፡ ኃጢአተኞች፡ ለዘላለም፡ ጠፍተዋል። ሁሉም ተፈጽሟል፥ ወደ ዘላለም ተዋህዷል። እንዲሁም የተዛባው ሁሉ፡ አንድ ቀን በዚያ የተቀመጠው ያ ታላቅ የመላእክት አለቃ፡ ይህን ሁሉ ክፋት ያደረገው፡ ሰይጣን፡ ይጠፋል። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ እንዳለ፡ ታስታውሳላችሁ፡ "ያች ነፍስ፡ እርሱ አድርጉ ያለውን ባታደርግ፡ እርሱ ያችን ነፍስ እንኳ ያጠፋታል።"

287 ነገር ግን፡ እያችሁ፡ ራሱን አጥፍቶ አምላክ ሆኖ ሊቀጥል አይችልም። ስለዚህ፡ ያቺ ነፍስ የዓለም ከሆነች፡ መጥፋት አለባት። ነገር ግን ከእግዚአብሔር ጋር፡ ዘላለማዊ ከሆነች፡ መቼም አልጀመረችም፡ ምክንያቱም የእግዚአብሔር አካል ስለሆነችና ፈጽሞ ልትጠፋ ስለማትችል። አሜን! እንዴት ውብ ነው! ቤተክርስቲያን ይህን ማየት መቻሏ፡ እ—እንዴት የሚያስመሰግን ነው!

288 ሰዎች፡ ያደረጋችሁት ነገር ሁሉ የሚያርፈው እዚሁ ላይ ነው። እኔም ለመናገር እየሞከርኩ ያለሁት ይህንን ነው። ወደዚያው እንደገና መመለስ ስለምፈልግ የተወሰነውን እየዘለልኩት ነው።

289 እነዚህ ነገሮችም፡ ሰይጣን፡ ኃጢአተኞች፡ ለዘላለም፡ ይጠፋሉ፥ ዳግመኛ ፈጽሞ አይኖሩም። ሁሉም... እያችሁ፡ ሰይጣን መፍጠር አይችልም። ከቻለማ፡ እርሱ አምላክ ነው። እያችሁ? የተፈጠረውን ማዛባት ብቻ ነው የሚችለው። እያችሁ? መዛባት ሁሉ፡ ማዛባትም ጭምር፡ ሙሉ በሙሉ ይወገዳል። ሞት የሕይወት መዛባት ነው፥ መዛባቱም ሲወገድ፡ ከእንግዲህ ሞት ሊኖር አይችልም። እርጅና የሞት ምልክት ነው፥ እርጅናም ሲወገድ፡ ሕይወት ይገባል። የመዛባት ምልክቶች ሁሉና ሌላውም ነገር ሁሉ ይጠፋል። እሾህና አሜከላ የኃጢአት ምልክቶች ናቸው፡ "ምድር በእነርሱ ትረገማለች" ተብሏል፡ እነርሱም ይወገዳሉ። በዚያም፡ በሽታ ይመጣል፥ እርሱም ይወገዳል። ሞት ይወገዳል። የደም መፋሰስ ይወገዳል።

290 ያንን አፈር ከቅድስና ማለትም ከተዋጁት በቀር፡ ሌላ ምንም ነገር መቼም አይነካውም። ኦህ፡ ማይ! አዎን። ኦህ፡ በጣም ደስ የምል ስሜት ይሰማኛል። እግዚአብሔር፡ የእርሱ ፍጥረት፥ የዚህ ፍጥረት ፍጡራኑም በገዛ ደሙ ተዋጅተዋል። በገዛ ራሱ የማንጻት ሂደት ነጽተዋል፥ በጀርም-ገዳይ፡ በኃጢአት-ገዳይ ሂደቱ!

291 ልክ ማንኛውም ነገር ስተራላይዝ ቢደረግ፡ እስካሁን ካየናቸው ምርጥ የጀርም ማጥፊያ መንገዶች እሳት አንዱ ነው። ማንኛውንም ነገር ወስዳችሁ በሳሙና አረፋና በእነዚህ በሚወራው ኬሚካሎች ሁሉ ልታጥቡት ትችላላችሁ፡ ሆኖም ግን ነጻ አይሆንም። አንድ ጊዜ ብታቃጥሉት ግን!

292 የእግዚአብሔር ቅዱስ እሳት ምድርን በኬሚካሎች ስተርላይዝ ሲያደርግ፥ ሙሽራይቱን አውጥቷል፡ ይህ እየሆነ ባለበት ጊዜ፡ እርሷ ከእርሱ ጋር ወደ ሰማይ ልትገባ ትችላለች። እንደገናም አዲስ ሰማያትና አዲስ ምድር ሆና፡ ወደ ምድር ትመለሳለች። ብርዳማው ክረምት ሊጎዳት አይችልም። ሞቃታማው በጋ ሊጎዳት አይችልም። በረሃዎቹ እንደ ጽጌረዳ ያብባሉ። ኃጢአትና ኃጢአተኞች ይጠፋሉ።

293 እግዚአብሔር፡ ፍጡራኑና ፍጥረቱ፡ በፍጹም ስምምነት አብረው ይኖራሉ። ሰማያትና ምድር ባልና ሚስት እንደሆኑት፡ ክርስቶስና ቤተክርስቲያንም እንዲሁ

ናቸው፡ ሁሉምም በአንድ ታላቅ የክብር የቤዛነት እቅድ ተገናኝተው እንደገና በቀጥታ ወደ እግዚአብሔር እቅፍ ይመጣሉ። አያችሁት?

294 እንዲሁም፡ በአዲሲቷ ምድር ውስጥ፡ አዲስ ከተማ አለች። ኦህ፡ ማይ! አሁን በደንብ አዳምጡ። ይህንን አትርሱ። ያንን፡ ኢየሱስ፡ በዮሐንስ 14 ላይ፡ ሊያዘጋጅ እንደሚሄድ ተናግሯል። “ልባችሁ አይታወክ።” ሲሄድ፡ “የምሄድበት ምክንያት አለኝ። በእግዚአብሔር አምናችኋል፥” እንዲህ አለ፡ “በእኔም ደግሞ እመኑ” አለ። እርሱ እግዚአብሔር መሆኑን ሊያዩ አልቻሉምም። እንዲህ አለ፡ “በእግዚአብሔር አምናችኋል፡ አሁን በእኔም እመኑ። ስፍራ ላዘጋጅላችሁ እሄዳለሁና። በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ፥ በአባቴ መንግሰት ብዙ ቤተ መንግሰቶች አሉ።” ክርስቶስ እዚያ ነው፡ አሁን በዚህች አዲሲቷ ኢየሩሳሌም ግንባታ ሰር ነው። አሁን በደንብ አዳምጡ። አትንቀሳቀሱ። አይ፡ ይህ እንዳያመልጣችሁ። ክርስቶስ ዛሬ፡ አዲሲቷን ኢየሩሳሌም እያዘጋጀ፡ በሰማይ ነው።

295 ልክ እግዚአብሔር ምድርን በስድስት ቀናት እንደፈጠረ፡ ምድርን በስድስት ቀናት፡ ወይም በስድሰት ሺህ ዓመታት እንደሠራው ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፡ “አንድ ሺህ ዓመት እንደ አንድ ቀን ነው፡” ብለን እንደምናነበው፡ እርሱ “አላዋቂዎች አትሁኑ” እንዳለው ነው።

296 ክርስቶስም ሄዷል ስፍራንም እያዘጋጀ ነው፡ ለብዙ፡ ለብዙ ሺህ ዓመታት፡ በግንባታ ላይ የነበረውን ስፍራ እያዘጋጀ ነው። “ሄጄም ስፍራ ባዘጋጅላችሁ፡ እኔ ባለሁበት፡ እናንተ ደግሞ እንድትሆኑ፡ ዳግመኛ እመጣለሁ፥ ወደ እኔም እወስዳችኋለሁ።” አስተውሉ ቤዛውንና የተዋጁትን!

297 አሁን ጊዜ በኖረን ብዬ እመኛለሁ፡ “ሰሎሞን ይህችን ልጃገረድ ሲያግባባት፥ ሙሽራይቱን፡” እዚህ ጋር ምልክት አድርጌበታለሁ። ኦህ፡ ዝም ብለን መተው አለብን፥ ጊዜው እየረፈደ ነው፡ አያችሁ። ዳግመኛ፡ እመለሰበታለሁ። “እርሷን ለማግኘት ሲሞክር፡ ነገር ግን ለእረኛ ልጅ ታጭታ ነበር።” አንዳንዶች ምናልባት የዘፈነው ዘፈን እንደሆነ ያስቡ ይሆናል። ኦህ፡ አይደለም። ሰሎሞን በምድር ላይ፡ የዳዊት ዙፋን ወራሽ ነበረ፡ ሆኖም ያ መንግሥት ማለፍ እንደነበረበት አሳይቷል። ይህ ከሙሽራይቱ ጋር በፍቅር የወደቀው የክርስቶስ ጥላ ነበረ። አያችሁ?

298 ኢየሱስ፡ በዮሐንስ 14 ላይ፡ “ስፍራ ላዘጋጅላችሁ እሄዳለሁ” ማለቱን አስተውሉ።

299 ኦህ፡ ምን ይመስል ይሆን? አሁን አሰባችሁት ታውቃላችሁን፡ ሙሽራይቱ ሆይ፡ ምን ይመስል ይሆን? በመለኮታዊው መሀንዲስ የተዘጋጀችና የተነደፈች ናት። ያቺ ከተማ ምን ትመሰል ይሆን? አሁን፡ ሰለ እርሱ ለጥቂት ደቂቃዎች ልንነጋገር ነው። መለኮታዊው መሀንዲሰ አዘጋጅቶታል፡ ነድፎታል። እና፡ ተመልከቱ፡ ለተወደደችው ሙሽራው፡ በርህራሄ እጆች ነድፎታል። ምን ሊመስል ነው?

300 አንድ ሰው አቅም ኖሮት፡ ሚሰት ሲያገባ፡ እያንዳንዷን ነገር እርሰዋ እንደምትፈልገው፡ እና እንደምትወደው አድርጎ እንደሚሠራና እንደሚያሰቀምጥ ታውቃላችሁ? አሜን።

301 አሁን፡ መለኮታዊው መሐንዲስ፡ ከሙሽራይቱ ጋር የሚኖርባትን አዲሲቱን ከተማ፡ ልክ ለእርሷ በሚስማማና እርሷን በሚያስደስት መልኩ ነድፏታል። ሐዋርያው፡ “ዓይን ያላየው፡ ጆሮም ያልሰማው፡ በሰውም ልብ ያልታሰበው” ማለቱ ምንም አያስገርምም። እስቲ ምን ልትመስል እንደምትችል ለማየት፡ ለአፍታ ያህል ጠለቅ ብለን ለመመልከት እንሞክር።

302 መለኮታዊው መሐንዲስ ይህችን የነደፋት ለፍቅረኛው ነው። አያችሁ? ኦህ፡ መለኮታዊ ባሕርይ ያለው፡ መለኮታዊ መሐንዲስ፡ የመለኮታዊ ሕይወት ደራሲ በሆነው መለኮታዊ አምላክ፡ በመለኮታዊ መንገድ አስቀድሞ ለተወሰነች መለኮታዊ መገለጫ ሲነድፋት ያ—ያ ሰፍራ ምን ዓይነት ድንቅ ሰፍራ መሆን አለበት! ያቺ ከተማ ምን ትመስል ይሆን? እስቲ አስቡት።

303 አስታውሱ፡ መንግሥተ ሰማያት አይደለችም። ዮሐንስ፡ “ከሰማይ ስትወርድ አየኋት” ነው ያለው። የምትሆነው በምድር ላይ ነው። አያችሁ?

304 ይህች ምድር የምትጠፋ አይደለችም፥ ይልቁንም የተዋጀች ምድር ናት። እግዚአብሔር አዲስ ትውልድን እንደሚያስነሳ አልተናገረም፥ ይልቁንም እዚህ ያለውን ነው የሚዋጀው። አዲስ ትውልድን አያስነሳም፥ እዚሁ ያለውን ነው የሚዋጀው። እርሱ አዲስ ዓለምን አይፈጥርም፥ ይኸው እዚሁ ያለውን ነው የሚያድሰው። ልክ እናንተን እንዳነጻችሁ ሁሉ፡ እርሷንም በእሳት አቃጥሎ፡ ያነጻታል። የእርሱ ዕቅድ ለዘላለም ጸንቶ መቆየት አለበት። አሁን፡ ተመልከቱ፡ ነገሩ እንዲህ ነው የሚሆነው።

305 አስታውሱ፡ መንግሥተ ሰማያት አትሆንም። “ከሰማይ ነው የምትወርደው።” መኖሪያ ሰፍራ ነች፡ ማደሪያውን የሚያደርግባት፡ መኖሪያ። ልክ ዮሐንስ፡ በፍጥሞ ደሴት ሆኖ፡ እዚህ በራእይ ምዕራፍ 21 ላይ፡ “ስትወርድ፡” እንዳያት ማለት ነው። ዮሐንስ ከተማይቱን አያት፡ ልክ እንደ እርግብ፡ “ከሰማይ ስትወርድ” አያት፡ እርሱ እንዳየው ናት።

306 እግዚአብሔር፡ በምድራዊ ማደሪያው፡ በኢየሱስ፡ ላይ… “ከሰማይ ወርዶ” ወደ ታች መጣ። ኢየሱስ ተጠመቀ፡ ወዲያውም ወጣ…

307 ነቢዩን ባገኘው ጊዜ! “ቃል ወደ ነቢይ ይመጣል።” እርሱም ቃል ነበረ። ነቢዩም የሐይማኖት ተቋማቸውንና፡ ሁሉንም ነገር እየካደ፡ በዚያ ቆሞ ነበር። ቃሉንም፡ ባየ ጊዜ፡ ቃሉ ቀጥታ ወደ እርሱ መጣ።

308 ነቢዩም በጣም ስለደነገጠ፡ “በአንተ ልጠመቅ ያስፈልገኛል። አንተ ወደ እኔ ትመጣለህን፡” አለው?

309 እርሱም፡ “ጽድቅን ሁሉ መፈጸም እንዲህ ይገባናልና (መልእክቱን እናውቀዋለን)፡ አሁንስ ፍቀድልኝ። መሥዋዕቱ እኔ ነኝ፥ መታጠብም አለበት” አለው። ከዚያም ፈቀደለት።

310 ከውኃው በወጣ ጊዜ፡ “ሰማያት ሲከፈቱ አየሁ፡” አለ። ነቢዩ አየው። ሰማያት ሲከፈቱ አየ።

311 እነሆም፡ ከሰማይ ሲወርድ፡ በርግብ አምሳል መጣ፥ ድምፅም፡ እንዲህ አለ፡ “ይህ እኔ የተቤዠሁት የእኔ የሆነው የምድር ክፍል ነው፡ ከዚህም የምድር አካል የቀረውን እቤዠዋለሁ፡ እርሱ የተገለጠው ቃሌ ነውና” አለ። “ዓለምን በሙሉ፡ በቃሌ ወደ መኖር አምጥቼዋለሁ፡” ዕብራውያን 11። “ሰይጣንም

ይህን ሁሉ ጊዜ ይዟት ነበር፡ ነገር ግን ልቤዣት መጥቻለሁ። አካሉም በብዙ ከእሷ የተገነባ ነው፡ በእርሱም ውስጥ ላድር እመጣለሁ።”

312 ዮሐንስ፡ “ቅድስቲቱን ከተማ፡ አዲሲቱን ኢየሩሳሌምን ለባልዋ እንደተሸለመች ሙሽራ፡ ከሰማይ ስትወርድ አየሁ” አለ። የት ላይ አረፈች? ልክ በዚያ ላይ እንዳደረገችው፥ በምድር ላይ።

313 ኢየሱስ መንፈስ ቅዱስ የወረደበት የዚያች ምድር አካል ነበረ፡ (ልክ ነው? ) ለዘላለምም በእርሱ ላይ ኖረ። ከቶ ሊለየው አይችልም። ሁልጊዜ እዚያ አለ። እርሱና እግዚአብሔር አንድ ናቸው። ሁልጊዜ መኖር አለበት!

314 ስለዚህም ዮሐንስ ቅድስቲቱን ከተማ፡ አዲሲቱን ኢየሩሳሌምን፡ እንደ ኮሜት፡ ወይም እ—እንደ ርግብ፡ ከሰማይ ስትወርድና በተዋጀችው፡ በመላዋ ምድር ላይ ስታርፍ አያት፡ (ምን ለማድረግ? ) ምድርን የፈጠረበትን እያንዳንዱን ባህርይ የራሱ ለማድረግ። በዘላለም ውስጥ የተወከለው እያንዳንዱ ወንድ፡ እንዲሁም እያንዳንዷ ሴት፡ ያኔ ይዋጃሉ። ተፈትጋለች፣ በእሳትም ተቃጥላለች።

315 ኢየሱስ፡ በምድረ በዳ ውስጥ በነበረው የእሳት ፈተናው፡ ለአርባ ቀናት ቆየ። ከዚያ በኋላ፡ አሰተውሉ፡ ያኔ ለአገልግሎቱ ዝግጁ ነበረ።

316 አሰቡት እስቲ፡ መንፈስ ቅዱስ በምድር፡ በኢየሱስና፡ በዚያ ቅዱስ ደም ላይ ሲወርድ! አሁን ተመልከቱ፡ በጣም ወደ ጥልቀት አልገባሁም ብዬ ተሰፋ አደርጋለሁ፡ እያችሁ። በእግዚአብሔር የተፈጠረው ቅዱስ ደም፥ ደሙ፡ ሕይወቱ፡ የእግዚአብሔር ፍጥረት። “ኢየሱስ የእግዚአብሔር ፍጥረት መጀመሪያ ነበር።” ኦህ! እያችሁ? እግዚአብሔር፡ በፍጥረት ውስጥ የተሰራ። እርሱ መንፈስ ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ፡ “እርሱ የእግዚአብሔር ፍጥረት መጀመሪያ ነው” አለ። እንዴት ጀመረ? በአንዲት ሴት ማኅፀን ውስጥ። ይኸውም ምንድን ነው? ሴቲቱ አይደለችም...

317 እነዚያ ዕውር ሰዎች የእባብን “ዘር” ልክ እዚህ ጋር ሊያዩት እንዳልቻሉት ነው። እያችሁ? ሔዋን እዚህ ምድር ላይ ተቀምጣ ነበር፡ እና፡ ሰይጣን ፈጽሞ ሳይነካት፡ ወይም ሌላ ምንም ሳይሆን፡ እግዚአብሔርም እነርሱን፡ “ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሉአት” አላቸው። በትክክል፡ ነገር ግን ሰይጣን እዚህ ላይ ጠልቃ ገባ። ታዲያ፡ ያ የአዳም ልጅ ከነበረ፡ ታዲያ የት...

318 አዳም በቀጥታ ከእግዚአብሔር የተገኘ ነበር። የወላጆችሁንም ባህሪ ብቻ ነው የምትወሰዱት።

319 ዳግመኛም ስትወለዱ፡ የሰማያዊውን፡ ወላጆችሁን ባህሪ ትወሰዳላችሁ። ሰማያዊ ወላጆችሁም የቃሉ ባህሪ ነው... ወይም፡ ቃሉ የወላጆችሁ ባህሪ ነው። ታዲያ፡ ስለ አንድ የሐይማኖት ተቋም ብላችሁ፡ እርሱን እንዴት ትክዱታላችሁ? ኦህ፡ ማይ!

ይህ እንደማያመልጣችሁ ተሰፋ አደርጋለሁ። ይህ ከእግዚአብሔር እንደሆነ አውቃለሁ።

320 ኢየሱስ። እነሆ ይሄው፡ ከሰማይ ወረደ፥ የእግዚአብሔር ባህሪ የሆነው፡ ኢየሱስም እዚያ ነበር።

321 አሁን፡ “ሴቲቱ፡” እርሷ። ተመልከቱ። እግዚአብሔር፡ “ይህን ስላደረጉ፡” እንዲህ አለ፡ “በዘሪሽና በእባቡ ዘር መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ” አለ። ልክ ነው? ሴቲቱም ምንም ዓይነት ዘር የላትም። ይህንን አስባችሁበት ታውቃላችሁ? እርሷ ማሳ እንጂ፡ ዘር የላትም። አያችሁ፡ እባቡ “ዘሩን” ቀድሞውኑ እዚያ አስቀምጦ ነበር።

322 እንደዚያ ከሆነ፡ ሴቲቱ ዘር ከሌላት፡ ዘር እንዲኖራት መቆየት አለባት።

323 አያችሁ፡ እዚህ በተፈጸመው የግብረ ሥጋ ግንኙነት አማካይነት፡ ከሰይጣን የመጣ ነበር፡ እርሱም በደረቱ የሚሳብ ያልነበረ፡ እባብ ነበር፥ እግሮች ነበሩት፡ ምክንያቱም እግሮቹ ከእርሱ ላይ ተወግደዋልና። እርሱ ከሁሉ ይልቅ ተንኮለኛ ነበር፡ ከ—ከሴቲቱ ጋር ሊጣመር-የሚችል ብቸኛ እንሰሳ ነበር።

324 የአውሬ ዘር አሁን ይህን አያደርገውም፡ ሌላም ምንም አያደርገውም። ሞክረዋል። አይሰራም። አያችሁ፡ ከተባዕት የሚወጣ የዘር ሕይወት ወደ ሴት አይገባም። ይህን አያደርገውም።

325 ነገር ግን ያ በጣም የቀተቃረበ ነገር ነበር። አያችሁ፡ በቺምፓንዚና በሰው መካከል ያለውን ያን ዝርያ ሊያገኙት አይችሉም። አያችሁ፡ እያንዳንዱ፡ ከወፎች ጀምሮ፡ ወደ ጦጣዎች፡ ወዘተ፡ እስከ ቺምፓንዚ ድረስ በዝግመተ ለውጥ ከፍ እያለ ሲመጣ፡ የሆነ “የጠፋ” አለ። ያ እባብ ነበር፡ ተራ እባብ አይደለም፥ የተረገመ ስለነበረ፡ እያንዳንዱ ቅርጽ ከእርሱ ጠፋ።

326 አሁን፡ እግዚአብሔር አዳምን አልረገመውም፥ እርሱም ያንኑ ነገር አድርጎ ሊሆን ይችላል፡ ነገር ግን ምድርን፡ “እሾህንና አሜከላን” ታብቅል ብሎ ረገማት።

327 ሔዋንን አልረገማትም፡ ነገር ግን አዳም “ገዥዋ” እንደሚሆን ተናገረ። ከአሁን ጀምሮ፡ ማንኛውንም ሰብከት ወይም ሌላ ነገር አትሞክርም፡ አዳም ገዥዋ ነው። “በሕይወትሽም ዘመን ሁሉ፡ በሀዘንም፡ የአንቺ... ህይወትን ወደ ምድር ታመጫለሽ።” ነገር ግን እንዲህ አለ፡ “በዘሪሽና በ... ጠላትነትን አደርጋለሁ”

328 አሁን፡ እርሷ ምንም ዘር አልነበራትም፡ ከቶም ኖሯት አያውቅም፡ ስለዚህ፡ በሆነ መንገድ ዘርን መቀበል ነበረባት። እግዚአብሔር ዘርን ሰጣት፡ በግብረ ሥጋ ግንኙነት አይደለም፡ ነገር ግን በፍጥረት።

329 ያ የእባቡ “ዘር” መሆኑን እናንተ እውሮች ማየት አትችሉምን? ኦህ፡ ማይ! ሰይጣን ከአዳም በፊት እዚያ ደረሰ፥ ያ “ዘሩ” ነበር።

330 ነገር ግን እርሷ ዘርን ተቀበለች። እርሱም ምን ነበር? እግዚአብሔር ራሱ። “እርሱ የእግዚአብሔር ፍጥረት መጀመሪያ ነበር።”

331 አሁን ሴት ሲወለድ ተመልከቱ፡ ወይም አቤል፡ ከአባቱ የሆነ፡ ጻድቅ ሰው ነበረ። ሴትም በተመሳሳይ መንገድ።

332 ያ ክፉ ሰው፥ ነፍስ ገዳይ፡ ውሸታም ከየት መጣ? አያችሁ፡ ከየት እንደመጣ አያችሁ? እርሱ ዘር ስለነበረ፡ “ዘር” መሆን ነበረበት፥ ቃየን ሰው ነበረ።

333 ኦህ፡ እነዚያ ዕውር የሆኑ ሰዎች የት አሉ? “የዚህ ዓለም አምላክ አሳውሯቸዋል።” እንግዲህ፡ ምንም አያስገርምም፡ ኢየሱስ ማንም ሊያየው እንደማይችል ተናገሯል። አያችሁ?

እናንተም፡ “ለምን አያዩትም” ትላላችሁ?

334 ኢየሱስ በአንድ ወቅት፡ ለደቀ መዝሙሩ፡ “የእግዚአብሔርን መንግሥት ማወቅ ለእናንተ ተሰጥቷል፡ ነገር ግን ለእነርሱ አልተሰጠም” አለ።

335 ከሺህ አምስት መቶ ስኩዌር ማይልስ ርቀት የመጣችሁበት ምክንያትም ይኸው ነው፡ አያችሁ፥ “መንግሥቱን ማወቅ ለእናንተ ተሰጥቷል።” ተመልከቱ፡ ሙሽራይቱ በዚህ በመጨረሻ ዘመን ወደ መንግሥቱ ለመግባት ስትዘጋጅ፡ ሰዎች ከደቡብ አፍሪካና ከአካባቢውም ጭምር መጥተዋል።

በቃ በቂ ጊዜ የለኝም። አስተውሉ። አሁን ተመልከቱ፡ አያችሁ።

336 አሁን የእባቡን “ዘር” እንዴት እንዳደረገ፡ በዚያ ውስጥ አያችሁት? ፍጹም ነው፡ አያችሁ። አሁን አንዳንዶች…

337 አሁን፡ በቀደም በቱክሰን የነበረው ሰውዬ፡ ሲሞክር እንደነበረው… እህ፡ ይህን ቴፕ ይሰማ ይሆናል። ነገር ግን፡ እንደዚያ ከሆነ፡ አንተ ሰው፡ አንድ ነገር ልነግርህ እፈልጋለሁ።

338 እርሱም፡ “ሔዋን እንዲህ አለች” ብሎ ሲናገር፡ ወደዚህ ነው የሚሄዱት፡ “‘ከጌታ ዘንድ ወንድ ልጅን፡ ወይም ሰው አግኝቻለሁ’ አለች።” ለምን፡ እርግጥ ነው። እግዚአብሔር ሕግ አለው።

339 ይኸውላችሁ፡ ዘር ወሰዳችሁ ስንዴ ባለበት ማሳ ውስጥ ብትተክሉትና፡ እዚያም አሜከላን ብትተክሉ። ምንም አይገደኝም፡ ያው ፀሐይና ያው ዝናብ ያንን ዘር ወደ ሕይወት ያመጣዋል። እግዚአብሔር ሕግ አለው፡ ያም ሕግ ሊጣስ አይችልም።

340 ግድ አይሰጠኝም እ—አንድ… በከተማዋ ውስጥ በጣም መጥፎ የሆነች ሴት በጣም መጥፎ የሆነ ወንድም፡ ያላገቡም ቢሆኑ ሌላም ነገር ቢኖር፡ የጾታ ግ—ግንኙነት ቢያደርጉ፡ አብረውም ቢኖሩ ልጅም ቢወልዱ፥ ያ ልጅ በእግዚአብሔር ህግ መምጣት አለበት፡ ምክንያቱም ሌላ መንገድ የለምና። ያ ካልሆነ፡ ሰይጣንን ፈጣሪ ታደርጋላችሁ፡ ያኔም እርሱ አምላክ ይሆናል። ኦህ፡ እንዴት እንዲህ እውር መሆን ትችላላችሁ! አያችሁ፡ የእግዚአብሔር ህግ፡ በእርግጠኝነት።

341 መቼም ቢሆን ልጅ ቢኖራችሁ፡ እሱ ኤሳው፡ ያዕቆብ፡ ማንኛውም ሰው፡ ወይም ማንኛውም መጥፎ-ስም ያለው ሰው ቢሆን፡ ይሁዳም ቢሆን፡ ከእግዚአብሔር ዘንድ መምጣት ነበረበት። እግዚአብሔር ሕግ አለው።

342 መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡ “እሱ በጻድቃንና በኃጢአተኞች ላይ ፀሐይን ያወጣል፥ በጻድቃንና በኃጢአተኞች ላይ ዝናቡን ያዘንባል-… ” ዕብራውያን ምዕራፍ 6 ላይም፡ እንዲህ ይላል፡ “ዝ—ዝናብ ምድርን ለማጠጣትና፡ ሕይወት ይሆን ዘንድ፡ ለተዘጋጀችለት ነገር፡ ለማዘጋጀት ብዙ ጊዜ ይመጣልና፡ ታውቃላችሁ፥ ነገር ግን እሾህና አሜከላ በአንድ ውሃና፡ በአንድ የፀሐይ ብርሃን ይኖራሉ።” ምክንያቱም፡ እያንዳንዱን ዘር ለማብሰልና፡ እያንዳንዱ ዘር ራሱን እንዲያባዛ ማድረግ፡ የእግዚአብሔር ህግ ነውና።

343 ስለዚህ፡ የእባቡን “ዘር” ማባዛት ነበረበት። ይህም እግዚአብሔርን ፈ—ፈጽሞ አላደናቀፈውም፥ ይልቁንም የእርሱን ፍጹም ዕቅድ ፈጸመ እንጂ፡ አዳኝም አደረገው። የተሰወረበት ካልሆነ በቀር፡ ማንኛውም እውር ያንን ማየት

ይገባዋል። “የዚህ ዓለም አምላክ” ከእናንተ ሸሽጎታል። ማየት እንደምትችሉት ማንኛውም ነገር ግልጽ ነው። ይሄውና አያችሁ። እባቡ “ዘር” ይኸውና። አሁን አስተውሉ።

ነገር ግን፡ “ኢየሱስ የእግዚአብሔር ፍጥረት መጀመሪያ ነበር።”

344 አሁን ሴቷ ምን ታደርጋለች? የሕይወት ዘሩ የሚመጣው፡ ከወንዱ ጾታ ነው። አሁን ይህንን ትክዳላችሁ? ሴቷ በውስጧ ምንም ዓይነት፡ ሕይወት የላትም። እሷ ያላት ትንሽ እንቁላል ብቻ ነው፡ እርሱም ልክ እዚህ ውጭ እንዳለ ማሳ ነው።

345 ልክ አንድን ማሳ ወስዳችሁ በደንብ እንዳረሳችሁት፡ ከ—ከዚያም መድሃኒት ረጭታችሁበት፡ ጀርሞችንም ሁሉ ጠራርጋችሁ እንዳስወገዳችሁት ነው። በውስጡ ም—ምንም ዓይነት ሳርም ሆነ ሌላ ነገር ማደግ አይችልም፥ ከዚያም እንደገና ማዳበሪያ አድርጋችሁበት፡ መልካም ዘርን በውስጡ ትዘሩበታላችሁ። ጠላት መጥቶ ሌላ ዘር ቢዘራበት፡ ያው የእግዚአብሔር ሕግ ሁለቱንም ዘሮች ያበስላል።

346 እንግዲህ፡ እግዚአብሔር ያ እንዲሆን አላሰበም ነበር፡ አያችሁ። ነገር ግን ምን ተፈጠረ?

347 አያችሁ፡ ከወንዱ የሚመጣው ስፐርም ደም የሆነውን፡ ሄሞግሎቢን ይሸከማል። በደም ውስጥ ሕይወት አለ። መቼም ቢሆን… በከብቶች ዝርያ ማዳቀልና በመሳሰሉት ነገሮች ላይ፡ ተመልክቼዋለሁ። ወንድም ሻካሪያንና እኔ፡ ሐኪሞችና የመሳሰሉት፡ ኬሚስቶች፡ እንዴት እንደሚያደርጉ ስንከታተል ነበር። አያችሁ? ከዚያም የእንቁላል ሰብሰብ የሆነው፡ ከሴቷ የሚወጣው ስፐርም ይመጣል። የዘሮች ሰብሰብ የሆነው፡ ከወንዱ የሚመጣው ስፐርም ይመጣል።

348 **ይሄኛው** በውስጡ ቅንጣት ታክል ዘር የለውም። የወንዱ ተረፈ-ምርት ብቻ ነው። በመጀመሪያ ደረጃ፡ እሷ እዚህ የመጣችው በዚህ መንገድ ነው፡ እሷም ማሳ ብቻ ነች። እንቁላል አለ፥ ለዚህ ሕይወት ለም መሬት አለው። ይህም ሕይወት ወደ ውስጥ ገብቶ ይሳባል። አንድ ምስጢር አለ፡ እንዴት ያ…

349 “ምናልባት፡” እንዲህ ትሉ ይሆናል፡ “እንግዲህ፡ የመጀመሪያው ይገናኛል። የቀሩት ይሞታሉ።” እንግዲህ፡ እንዴት፡ ማን ይወስነዋል? “እንግዲህ፡ የመጀመሪያው ነዋ።” ከፊት ያለው ይሆናልን፥ ከፊት ያለው የመጀመሪያው እንቁላልና፡ የመጀመሪያው ዘር? አይ፡ አይደለም።

350 አንድ እንቁላል ሊሆን ይችላል፥ ፈጽሞ ከኋላ፡ በስተጀርባ፡ በስፐርሙ መካከል፡ አንድ ዘር ወጥቶ ሄዶ ይገናኘዋል። ይህ የሚያሳየው የሆነ እውቀት ቀይ-ጠጉር፡ ጥቁር-ጠጉር፥ ትንሽ፡ ትልቅ እንደሚሆን፥ ወንድ ወይም ሴት እንደሚሆን እንደሚወስነው ነው። አያችሁ? ምንም፡ በዚህ ላይ ሌላ ምንም ልታደርጉ አትችሉም፥ አይሰራም። አንድ ላይ ልትቀላቅሏቸውና፡ ሁሉንም ነገር ልታደርጉ ትችላላችሁ፡ ምንም ዓይነት ልዩነት አያመጣም። እግዚአብሔር ይወስነዋል። ከተወሰነ ጊዜም በኋላ፡ አንድ ትንሽ ዘር ወደዚያ ማሳ፡ ወደ እንቁላሉ ይሳባል። በላዩ ላይ፡ እንደ፡ ትንሽ ጅራት ያለው ነገር፡ ሲዋኝ ቆይቶ፥ ይወድቅና፡ ከዚያም የሕፃኑ አከርካሪ አጥንት መፈጠር ይጀምራል።

351 ታዲያ እሷ ምንድናት? እሷ ዘር የላትም። ዘሩን የምትቀበልበት ማሳ አላት። ስለዚህ...

352 አያችሁ፡ ጠላት ወጣ። መልካሙ ዘሪ፡ መልካም ዘርን እየዘራ ሲወጣ፥ ጠላት ከኋላው ወጥቶ፡ የተበላሸ ዘርን ዘራ። “ነገር ግን ዝናቡ በጻድቃንና በኃጢአተኞች ላይ ይዘንባል፥ ፀሐይም።” ሁሉም ማደግ አለበት።

353 ኢየሱስ፡ “አብረው ይደጉ። በዚያ ቀን፡ እንክርዳዶቹ ይታሰራሉ” አለ። አሁንም በትላልቅ ድርጅቶች ውስጥ፡ እየታሰሩ ነው፥ ወደ ትልቁ እሰር፡ ወደ ዓለም አብያተ ክርስቲያናት ካውንስል እየሄዱ ነው። መጨረሻውም ምን ነበር? መቃጠል ነው። ነገር ግን ስንዴው ወደ ጎተራ ይወሰዳል። አያችሁ? ይህም፡ ሁለቱም በአንድ ዓይነት ነገር፡ በአንድ ዓይነት ውኃ፡ በተመሳሳይ ዝናብ ይኖራሉ።

354 የሲትረስ ዛፍ፡ ማ—ማለትም የብርቱካን ዛፍ፡ ያፈራል፡ ግድ ነው፥ ሮማን፡ በላዩ ላይ ለማዳቀል ከተተከለበት፡ ያፈራል። ሎሚን ያፈራል። የወይን ፍሬን ያፈራል። አያችሁ? ነገር ግን ብርቱካን አይሆንም፡ ነገር ግን የብርቱካኑ ዛፍ ከሚያመነጨው ከተመሳሳይ ሕይወት እየተመገበ ይኖራል።

355 የሐይማኖት ተቋማት በወይኑ ግንድ ላይ ተተክለዋል። ምክንያቱም፡ “ክርስቲያኖች” ነን ካሉ፡ በእርሱ ይኖራሉ። ቀያፋም እንደዚያ ነበር፥ ማን እንደነበረ ታውቃላችሁ፥ ሆኖም ግን ትንቢት እንኳ ተናግሮ ነበር። አያችሁ? አያችሁ፡ በእርሱ ይኖራሉ።

356 ኦህ፡ ይህንን ነገር በሚገባ አጥንተን፡ ሳታዩት እንዳታልፉ፡ ግልጽ ለ—ለማድረግ አንድ ሳምንት ቢኖረን እመኛለሁ። አሁን ከእነዚህ ነገሮች መካከል አንዳንዶቹን እተዋቸዋለሁ።

357 አሁን ተመልከቱ። ተመልከቱ፡ እነዚያ እጆች ይህንን ያዘጋጁት ለተወደደችው ሙሽሪት ነው፡ ለሙሽሪት ባለው በላቀ ፍቅር ነው ያዘጋጁት።

358 መንፈስ ቅዱስ በኢየሱስ ላይ እንደወረደ አስታውሱ፡ ይህም፡ ኢየሱስ የምድር አካል ነበረ። ለምን? የእግዚአብሔር ዘር፡ የእግዚአብሔር ሕይወት፡ የተፈጠረው በሴት ማህፀን ውስጥ ነው (ልክ ነው?)፡ እርሷም ምድር ነበረች። መልካም። ከዚያም የእግዚአብሔር ሕይወት ወደ ውስጥ ገባ፡ ስለዚህ፡ “እርሱ የእግዚአብሔር ፍጥረት መጀመሪያ ነበረ።” አያችሁ? ከዚያም በዚያ ዘር ምክንያት፡ በዚያ የነበረው ያ የእግዚአብሔር ደም፥ በቀራንዮ ሲፈስ፥ ተመልሶ በምድር ላይ ጠብታው ወደቀ። ለምን? ምድርን ለመዋጀት። አሁን፡ ጸድቃለች፥ ተቀድሳለች፥ ተጠርታለች፡ የእርሱ ሆናለችም፥ አሁንም የእሳትን ጥምቀት ልትቀበል፡ ለኢየሱስና ለሙሽራይቱ ንጹ ትሆናለች።

359 እናንተም ከዚች ምድር የተወጣጣችሁ ሌሎች አካሎች ናችሁ። ምድር፡ እናንተ የምድር አካል ናችሁ፥ ሰጋችሁ። ነፍሳችሁ የእግዚአብሔር አካል ናት፡ እዚህ ምድር ላይ በአካል የታየች፡ የእግዚአብሔር ባህርይ ናት። አካሉ መዋጀት አለበት።

360 አሁን፡ ነፍስ ተዋጅታለች፡ ምክንያቱም በኃጢአት ውስጥ ነበረችና። ስለዚህ እግዚአብሔር ወረደ፡ በማጽደቅ፡ በመቀደስ፡ በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ሂደት ውስጥ አልፎ፡ ነፍሳችሁን ዋጃት።

361 እናንተም፡ የምድር አካል እንደመሆናችሁ መጠን፡ በእርሱ ይቤዣል። አሁን በሂደቱ ውስጥ ናችሁ። ሂደቱም እየቀጠለ ነው። አካላችሁ በኖኅ ጥምቀት ጸድቋል። አሜን! እንዲሁም፡ በስጋችሁም፡ ወረደ። እናንተ የምትኖሩበት ስፍራ የሆነችው ምድርም፡ በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት፡ በእሳት ልትነጻ ነው፥ ለክርስቶስና ለሙሽራው መኖሪያ ስፍራ የሚትሆን፡ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም።

362 ይህችን ከተማ ተመልከቱ፥ ምድር፡ በምድር ላይ ማደሪያዋን ታደርጋለች። አሁን እንደነገርኳችሁ በግልጽ ማየት ትችላላችሁ፡ ይህ... ይህ ለውጥ፡ ምድር መለወጥ አለባት። እንደዚህ ባለ ሁኔታ ልትይዘው አትችልም። ቤተክርስቲያን አትቀጥልም... ወይም፡ ዓለም ከሺህ ዓመቱ መንግስት በኋላ፡ ሳትለወጥ፡ እንዲሁ ልትቀጥል አትችልም። አያችሁ? እንዲህ ያለውን ስፍራ በውስጧ ለመያዝ፡ የግድ መለወጥ አለባት።

363 ልክ እንደዚሁ፡ እርሱ በውስጣችን እንዲያድር፡ ሁኔታዎችን ለማመቻቸትና ስፍራን ለማዘጋጀት በቅዱስ እሳቱ መለወጥ አለብን፥ ይኸውም፡ መንፈስ ቅዱስ ነው።

364 አሁን አስተውሉ፡ በአዲሲቱ ምድር ውስጥ ብዙ መኖሪያ ይኖራል። ኧ-ህ። አያችሁ፡ ብዙ መኖሪያ! ትታደሳለች፡ ይህ እውነት ነው፡ በእሳት፡ ሆኖም ከዚያ በኋላ ባህር አይኖርም። አስተውሉ፡ ከተማይቱ አንድ ሺህ አምስት መቶ ማይልስ ስኩዌር ናት።

365 አሁን እነዚህን ልኬቶች ስንስል በደምብ አዳምጡ። ስሌዳውን ላጥፋው፡ ለአንድ አፍታ ታገሱኝ።

366 ከእግዚአብሔር የሆነ ጥልቅ መገለጥ ይኸውላችሁ። እዚህ፡ እዚሁ ላይ እቆማለሁ። ከእነዚህ አንዳቸውም... የቀረውን ጌታ ቢፈቅድ፡ ወደፊት አመጣዋለሁ።

367 አሁን ምድሪቱ... እንግዲህ፡ ወደ ራእይ መጽሐፍ ብትገልጡ፡ በክንድና በምዕራፍ እንዴት እንደለካው ማየት ትችላላችሁ። ሁለት-ሺህ ሦስት መቶ... ስለዚህ አሁን ከ—ከተማይቱ፡ "አንድ ሺህ አምስት መቶ ማይልስ" ስኩዌር ሆና እንደተለካች እናገኛለን፡

368 ምን ያህል ርቀት እንደሚደርስ ታውቃላችሁ? በዚህ ሳምንት፡ ለክቼዋለሁ። ከሜይን እስከ ፍሎሪዳ፡ እንዲሁም ከምስራቃዊው የባህር ዳርቻ እስከ ሚሲሲፒ ምዕራብ ድረስ፡ ስድስት መቶ ማይልስ ይደርሳል። በሌላ አነጋገር፡ የዩናይትድ ስቴትስ ግማሽ የሚያህለው፡ ለከተማይቱ ብቻ ይሆናል ማለት ነው።

እናንተም፡ "ምንም መኖሪያ ቦታ የለም" ትላላችሁ።

369 ባህሩ ሲወገድ ቦታ ይኖራል፡ ምክንያቱም አራት አምስተኛ የሚጠጋው በውሃ የተሸፈነ ነውና። ልክ ነው? ፍንዳታው ባህሩን ያደርቀዋል፡ ምድርን ያፈነዳታል። ኦህ፡ ማይ! አስታውሱ፡ አንድ ሺህ አምስት መቶ ማይልስ ስኩዌር ማይልስ፡ እንዴት ያለች ከተማ ናት! እና፡ ባህሩ እንደተወገደ፡ ግን፡ አስታውሱ።

370 "ስፋቷና ከፍታዋም እኩል ነው።" ይህም **ወደዚህ** አንድ ሺህ አምስት መቶ ማይልስ፡ **ወደዚያ** አንድ ሺህ አምስት መቶ ማይልስ፥ አንድ ሺህ አምስት መቶ ማይልስ፥ ርዝመቱ በስፋቱ በከፍታው ያደርገዋል። አንድ ሺህ አምስት መቶ ማይልስ፡ አስቡት፡ የሚያንጸባርቅ ወርቅ። ከተማይቱም በዙሪያዋ ቅጥር ነበራት።

371 አሁን፡ አሁን፡ እኩል በመሆናቸው፡ ብቻ የግድ… “ቅጥሮቹና መሰረቱ እኩል ነበሩ፡” ይላል፡ ይህ ማለት ግን የግድ ኪዩብ ወይም ስኩዌር ነው ማለት አይደለም። ልኬቶቹ አንድ ዓይነት የሆኑበት፡ ሌላ መልክዓ ምድራዊ መለኪያ አለ፡ እሱም፡ ፒራሚድ ነው። አራት ማዕዘን፡ “አራት ማዕዘን ሆና ተቀምጣለች፡” ቅጥሮቿም እኩል ነበሩ።

372 እስቲ ልሳለው። አያችሁ፡ ርዝመት፡ ስፋት፡ ከፍታ። ዓለም መኖሯ እርግጥ እንደሆነ ሁሉ፡ እኛም ወደ አንድ ነገር ውስጥ ልንገባ ነው። አያችሁ? አስተውሉ፡ **የዚህ** ማዕዘን ልኬቶች ሁሉም በትክክል እኩል ናቸው፡ ርዝመቱ በ—በከፍታው። ያንን የሚያረጋግጥ፡ ሌላ መለኪያ አለ፡ እርሱም ፒራሚድ ነው።

373 ይህ፡ በዚህ መልኩ መሆኑ፡ በግብጽ ያለውን የሄኖክን ምልክት በትክክል ይመልሳል፡ ፒራሚዱን። ይመልሳል አይደል? ሄኖክ፡ ከጥፋት ውሃ በፊት፡ መጽደቅ በቀረበ ጊዜ፡ አንድ ምልክት አመጣ፡ በዚህም ፒራሚድ ውስጥ ወደ ንጉሱ ክፍል የሚወሰዱ ሰባት ደረጃዎች አሉ። የፒራሚዱን ልኬቶች አጥንታችሁ የምታውቁ ከሆነ፡ የሚመጣውን ሰው ተቀብሎ፡ ከንጉሱ ጋር ለማስተዋወቅ፡ በሰባተኛው ደረጃ ላይ ምን እንደሚመጣ ተመልከቱ። በዚያ የቆመው የማን ሰፍራ እንደሆነ ተመልከቱ፡ እናንተም የምትኖሩበትን ዘመን፡ በፒራሚዱ ውስጥ ታያላችሁ።

374 አሁን፡ እግዚአብሔር ሦስት መጽሐፍ ቅዱሶችን ሰራ። አሁን፡ ምንም ትርጉም የሌለው የፒራሚድ ትምህርት አለ፡ ነገር ግን እውነተኛ ፒራሚድ አለ። አያችሁ? አስተውሉ። አሁን፡ እግዚአብሔር፡ የመጀመሪያው መጽሐፍ ቅዱስ… ሦስት ሰራ። ሁሉም ነገር በሦስት መሆን አለበት።

375 ኢየሱስ ሦስት ጊዜ ይመጣል። ሙሽራውን ለመዋጀት፡ አንዴ፡ መጣ፥ በሚቀጥለው ጊዜ፡ ሙሽራውን ለመውሰድ፥ በሚቀጥለው ጊዜ ደግሞ፡ ከሙሽራው ጋር። አያችሁ?

376 አሁን ምን ያህል ውብ እንደሆነ አስተውሉ። አያችሁ? በዚሁ ፒራሚድ ውስጥ ሰባት ደረጃዎች ነበሩ፡ ከዚያም የንጉሱ ክፍል አለ። እኛም ንጉሱ ዙፋኑን ከመውሰዱ በፊት፡ በሰባተኛው የቤተክርስቲያን ዘመን ውስጥ እንገኛለን። አስታውሱም፡ ፒራሚዱ፡ መቼም ቢሆን የማዕዘን ራስ አልነበረውም።

377 የእግዚአብሔር የመጀመሪያው መጽሐፍ ቅዱስ በሰማያት ውስጥ ነበረ፡ እርሱም ዞዲያክ ነው፥ እርሱም ይጀምርና እያንዳንዱን ዘመን ያስቀጥላል። የመጀመሪያው፡ የዞዲያክ መጀመሪያ፡ ድንግል ናት፥ እርሱ መጀመሪያ እንዴት እንደመጣ፡ የሚያሳይ ነው። በዞዲያክ ውስጥ የመጨረሻው ምስል አንበሳው ሊዮ ነው፥ እርሱም ሁለተኛውን ምጽአት ያመለክታል። ልክ ከዚያ በፊት የተሻገሩ ዓሳዎች አሉ፡ እርሱም እኛ አሁን የምንኖርበት፥ የካንሰር ዘመን ነው።

378 ከዚያ በኋላ አንድ ፒራሚድ ነበረ፡ እርሱም የሄኖክ ነው፡ እርሱም በትክክል መሰከረ። ወደ እሱ ለመግባት ጊዜ አይኖረንም፡ ነገር ግን፡ አንድ ቀን፡ በእግዚአብሔር እርዳታ፡ እኛ የምንኖርበትን ዘመን ልኬት፡ በትክክል እንዴት እንደሚያስቀምጥ አሳያችኋለሁ። አያችሁ?

379 አስተውሉ፡ ዳሩ ግን አሁን ያለን ይህ መልክዓ ምድራዊ መለኪያ፡ ልኬቶቹ እኩል የሆኑት፡ የ—የግድ ኪዩብ መሆን አለበት ማለት አይደለም። አስተውሉ፡ ይህ የግብጽን… ወይም በግብጽ ያለውን የሄኖክን ምልክት ይመልሳል።

380 ምድር በእሳት ጥምቀት፡ በምትነጻበት ጊዜ፡ ይህች ምድር እንደምትፈነዳው ዓይነት፡ የእሳተ ገሞራ ፍንዳታ ይኖራል፡ ይህም እንደ ፒራሚድ-ያለ ተራራን ወደ ላይ ያነሳል። አያችሁ? ይህን ለማድረግ በቂ ሰፍራ አለ! ይህ ሁሉ ነገር ይለወጣል። መላው ገጽታ ይለወጣል። ገባችሁ? እንደ ፒራሚድ-ያለ ተራራን ወደ ላይ ያነሳል።

381 ይህ ቃሉ ካደረገው ቃሉን በትክክል የሚገጥም ይሆናል፡ በእርግጥም ያደርገዋል። አሁን አስተውሉ፡ ምክንያቱም፡ በኢሳይያስ 65፥25 ላይ፡ አሁን ባነበብነው ክፍል፡ እንዲህ ብሏል።

> **በተቀደሰው ተራራዬ ሁሉ አይጎዱም አያጠፉምም፡ ይላል እግዚአብሔር**።

382 ኦህ! "የተቀደሰው ተራራዬ ሁሉ!" አስታውሱ፡ ሁልጊዜም "ተራራ" ነው።

383 ቅጥሮቹ ቀጥ ብለው ወደ-ላይና-ወደ ታች ቢሆኑ ኖሮ፡ ከተማይቱ ከውጭ ብቻ ልትታይ ትችል ነበር... ወይም ከውስጥ፡ ዙፋኑ ከውስጥ ብቻ ሊታይ ይችል ነበር፥ ዳሩ ግን ከውስጥ ብቻ እንደሚታይ አስተውሉ።

ነገር ግን አሁን የኢሳይያስ 4፥5ን ተሰፋ እናያለን። እስቲ እናንብበው።

384 ቸኩላችኋል እንዴ? [ጉባኤው፡ "አይ" አለ።—አርታዒ።] አትቸኩሉ፡ አሁን አትቸኩሉ። እ—እ—እኛ አሁን ወ—ወደ አንድ የተለየ ነገር ላይ ደርሰናል፡ በ—በጣም አስፈላጊ ጊ—ጊዜ ላይ ነን እዚህ ጋር በሚገባ መረዳት ይኖርባችኋል። ምክንያቱም፡ ይህንን ግልጽ ማድረግ እፈልጋለሁ። ከዚያም እንደገና ወደዚህ ስንመለስ፡ በ—በምን፡ ጉዳይ ላይ እየ—እየተነጋገርን እንዳለን፡ በሌላ ጊዜ፡ በሚኖረን ጥናት ላይ አሳያችኋለሁ።

385 ኦህ፡ ጌታ ኢየሱስ ይመስገን! ቃላቱ እንዴት ሊወድቁ እንደማይችሉ፡ እዚህ ጋር ተመልከቱ። አሁን እዚህ ኢሳይያስ ውስጥ ተመልከቱ። እንደገና ማግኘት ከቻልኩ ልመልከት፡ እዚህ ጋር ጽፌዋለሁ፡ አንድ ደቂቃ ብቻ። ኢሳይያስ 4፥5። አሁን አዳምጡ፡ እርሱ ስለ ጌታ መምጣት እየተናገረ ነው፡ ሴቶች እንዴት ሥነ ምግባር የጎደላቸው እንደሚሆኑ። ኦህ፡ እንዲህ አለ፡ "ሰባት ሴቶች... " አዳምጡ፡ እስቲ እናንብበው፡ እዚህ ጋር ተመልከቱ፥

> **በዚያም ቀን ሰባት ሴቶች፡ የገዛ እንጀራችንን** እንበላለን፡... **የገዛ ልብሳችንንም እንለብሳለን፡ ሰምህ ብቻ በእኛ ላይ ይጠራ፥ መሰደባችንንም አርቅ ብለው፡ አንዱን ወንድ ይይዙታል።**

386 ያ እኛ አሁን የምንኖርበት፡ የፍጻሜ ዘመን ነው፥ ጋብቻ፡ ፍቺና፡ ዝሙት፡ እንዲሁም ሌላም ነገር ሁሉ የበዛበት።

> **በዚያም ቀን የእግዚአብሔር ቁጥቋጥ ለጌጥና ለክብር ይሆናል፡... ከእስራኤልም ወገን ላመለጡ... ሰዎች... የምድሪቱን ፍሬ ለትምክሕትና ለውበት ይሆናል።** (ከዚያ ሁሉ ፍርድ እንዴት እንዳመለጣችሁ! አያችሁ? )
>
> **እንዲህ ይሆናል፡ በጽዮን የተረፈ፡ በኢየሩሳሌምም** ቅሪት የ**ሆነ፡ ይሆናል**... (እስቲ እንመልከት።)... **በኢየሩሳሌምም፡ ቅዱስ ይባላል፡ ይህም በኢየሩሳሌም ለሕይወት የተጻፈ ሁሉ፡** አያችሁ፡

**ጌታም የጽዮንን** ቈነጃጅት **እድፍ ባጠበ** ጊዜ፡ (አስታውሱ፡ ያች ሁልጊዜም ሙሽራይቱ ናት፡ አያችሁ)... **የኢየሩሳሌምንም ደም ባነጻ ጊዜ** (ያ የአይሁድ ቀሪዎች ናቸው፡ እንዲሁም ሙሽራይቱ፡ አያችሁ)... **በፍርድ መንፈስና፡** በሚያቃጥል...

387 ያ ሁልጊዜም እግዚአብሔር የመጨረሻውን ፍርዱን ሲያደርግ፡ የሚሰጠው የእግዚአብሔር ፍርድ ነው። ይጠራችኋል፡ ያጸድቃችኋል፡ ወደ ቤዛነትም ያመጣችኋል፥ ከዚያም ፍርዱ በእናንተ ላይ ይፈነዳል፡ መንፈስ ቅዱስና እሳቱም ኃጢአትን ያነጻል። ከዚያም የእርሱ ትሆናላችሁ።

388 በእሳትና፡ “በሚያቃጥል መንፈስ” ሲያነጻት፡ በምድርም ላይ የሚያደርገው ያንኑ ነው። አሁን ተመልከቱ። አዳምጡ! ዝግጁ ናችሁ?

**ጌታም በጽዮን ተራራ ላይ ባለ ማደሪያ ሁሉ፡ በ**ጉባኤ**ዋም ላይ በቀን ዳመናንና፡ ጢስን በሌሊትም... የሚበራ የእሳት ብርሃን ይፈጥራል፥ በክብርም ሁሉ ላይ መጋረጃ ይሆናል።**

389 [ወንድም ብራንሃም በሰሌዳ ላይ በሰዕል አሰረዳ—እርታዒ።] “በዚያ ቀን፡ ጌታ፡ በዚያ ራስ ላይ፡ በቀን የሚበራ የብርሃን እሳትን ይፈጥራል።” ቀጥሎም፡ “መጠለያ፡ ማረፊያ፡ መሸሸጊያ ይሆናል” ይላል። አስተውሉ፡ መጽሐፍ ቅዱስ የተናገረውን፡ በትክክል ያደርገዋል። ቅጥሮቹ ቀጥ ብለው ወደላይ-እና-ወደ ታች ቢሆኑ ኖሮ፡ ልታዩት አትችሉም ነበር። የግድ ዘንበል ማለት አለበት። “የተቀደሰው ተራራዬ ሁሉ... ” “ይህንን ብርሃን በዚህ ተራራ ላይ ይፈጥራል፡ እርሱም መከላከያ ይሆናል።” ኦህ፡ ያንን መዝሙር እንዘምራለን፥

ኦህ፡ ያች ከተማ በጽዮን ተራራ ላይ፡
እንግዳ ብሆንም፡ አሁንም እወዳታለሁ፥
አሁንና በእነዚያ ዘመናት ሁሉ፡
ከኮረብታው ላይ ወዳለችው ወደዚያች ከተማ ስደርስ።
(አያችሁ? )

390 አስተውሉ፡ ሲና ተራራ በእሳት ዓምድ ውስጥ ሆኖ ለእስራኤል በተናገረ ጊዜ፡ እግዚአብሔር በላዩ ላይ የወረደበት ስፍራ ነበረ። ተራራ ላይ ወረደ፡ በሲና ተራራ።

391 በመገለጥ ተራራ ላይ፡ “የምወደው ልጄ ይህ ነው፥ እርሱን ስሙት፡” ብሎ ባወጀ ጊዜ፡ በጴጥሮስ፡ በያዕቆብና፡ በዮሐንስ ፊት፡ በብርሃን ዓምድና በሚያንጸባርቅ ብርሃን፡ ተራራው ላይ ወረደ። በዚያም፡ እርሱ፡ ከሙሴና ከኤልያስ ጋር አብሮ ታየ፥ አንደኛው የተነጠቀው፡ ሌላኛው ደግሞ ከሞት የተነሳው። ክብር ይሁን!

392 አዲሲቱ ከተማና አዲሲቱ ምድር፥ አዲሱ ፍጥረት፥ ዙፋኑ በእሷ ላይ ያለበት፡ በተራራው ላይ ያለች ከተማ። [ወንድም ብራንሃም በሚቀጥሉት ጥቂት አንቀጾች በሰሌዳ ላይ ሰዕሎችን ይስላል—እርታዒ።] ዙፋኑ **እዚህ** ላይ፡ ከላይ፡ ነዋሪዎቹም፡ ወደ-ላይና-ወደ ታች፡ በዚህ ተራራ ላይ ይኖራሉ።

393 በዙሪያው ያለው ቅጥር፡ አስራ ሁለት መሰረቶች ነበሩት። በእያንዳንዳቸውም ላይ በአሮን የደረት ኪስ ላይ የነበረው ድንጋይ ነበረበት፡ እርሱም አስራ ሁለቱን የእስራኤል ነገድ ይወክላል።

394 በበሮቹም ላይ፡ ልክ በምድረ በዳ እንደነበረው ቤተ መቅደስ፡ በምድረ በዳ እንደነበረው ድንኳን በትክክል የተቀመጡ፡ አራት በሮች ነበሩአቸው። በእያንዳንዱ በኩል፡ ሦስት ሦስት ሐ—ሐዋርያት፡ አስራ ሁለቱ ሐዋርያት እንደነበሩ፡ አስተውሉ። እያንዳንዱ… ከፍታውም መቶ አርባ-አራት ክንድ ነበረ። መቶ አርባ-አራት ክንድ ማለት በትክክል ሁለት መቶ አስራ ሰድስት ጫማ ነው፡ ያም እያንዳንዱን ትልቅ ድንጋይ ወደ ሃያ-ጫማ የሚያህል ርዝመት እንዲኖረው ያደርገዋል፡ ያ በበሩ ላይ ያለው የደረት ኪስ፡ በከተማይቱ ዙሪያ ያለውን ያንን ቅጥር ይሰራል።

395 አሁን፡ ከተማይቱ፡ በቅጥሩ አናት ላይ አታርፍም፡ ምክንያቱም፡ አንድ ሺህ አምስት መቶ ማይልስ የሆነች ከተማ፡ ያንን ልታደርግ አትችልምና። ልክ እንደ አሮጌዋ ኢየሩሳሌም በሮች፡ በቅጥሩ በኩል ወደ ውስጥ የምትገቡበት **ይህ** ቅጥር ነው። በቅጥሩ በኩል፡ ወደዚያ ትገባላችሁ።

396 እያንዳንዳቸውም፡ አስራ ሁለቱን መሰረቶች ይዘው ነበር፡ እያንዳንዳቸውም መረግድና ልዩ ልዩ ድንጋዮች ነበሯቸው፡ እነርሱም አስራ ሁለቱን የእስራኤል ነገድ ይወክላሉ።

397 ሐዋርያቱም፡ እያንዳንዳቸው፡ ከዚያ ትልቅ፡ አንድ ጠንካራ-ዕንቁ ከሆነው በር በላይ፡ የአንድ ሐዋርያ ስም ተቀምጦበታል። ኢየሱስ፡ “በአስራ ሁለቱ የእስራኤል ነገድ ላይ ልትፈርዱ፡ በአስራ ሁለት ዙፋን ላይ ትቀመጣላችሁ” አላለምን? ወደ ከተማይቱ ሲገቡ፡ ሊፈርድ፡ በበሩ ላይ የተቀመጠው ማን ነው? ኦህ፡ ማይ! ይሄውና አያችሁ። ኢየሱስ በገባው ቃል መሰረት፡ የምድር ነገስታት ወደ ከተማይቱ ሲገቡ፡ በሐዋርያዊው ዳኛ ፊት ይቀርባሉ። ኦህ፡ ማይ!

398 በዚህ ዙፋን ላይ፡ በላዩ ላይ፡ አንድ ሺህ አምስት መቶ ማይልስ ከፍታ ላይ፡ መላው ዓለም የዓለምን ብርሃን፡ ኢየሱስን፡ በዓለም አናት፡ በቤተክርስቲያን አናት፡ በጽዮን ተራራ አናት ላይ በዙፋኑ ላይ ተቀምጦ ያየዋል፥ ይህም አንድ ሺህ አምስት መቶ ማይልስ ነው፡ የዩናይትድ ስቴትስ ግማሽ የሚያህል መጠን አለው፡ በዓለም ዙሪያ ልታዩት እስክትችሉ ድረስ ወደ ላይ ከፍ ይላል፡ አንድ ሺህ አምስት መቶ ማይልስ ከፍታ።

399 **በዚህ** ወደ ላይ-እና-ወደ ታች፡ የተዋጁት ይኖራሉ። ከንጹህ ወርቅ የተሰሩ ቤቶች ይኖራሉ። መንገዶች፡ መናፈሻዎችና፡ አትክልት ሰፍራዎች ይኖራሉ። የሕይወት ወንዝም ይመጣል፡ ከዙፋኑ ይፈልቃል፡ በትንንሽ እርከኖችና፡ ኦህ፡ ደረጃዎች ላይ ይፈሳል። የሕይወት ዛፍም በእያንዳንዱ ግቢ ውስጥ ያብባል፥ ፍሬውንም፡ በዓመት አስራ ሁለት ጊዜ ይሰጣል፡ በየወሩ የተለየ ፍሬ ያፈራል።

400 የምድር ነገስታትም ወደ እርሷ ይመጣሉ ክብራቸውንም ያመጣሉ። ነገስታቱ በዚያ በሰላም ሲኖሩ፡ “ቅጠሎቹም ለሕዝብ መፈወሻ ናቸው።” ወደ ውጭ ሲወጡ፡ ከአንድ ዛፍ ላይ **እንዲህ** ያለ ቅጠል፡ ይወስዳሉ። የእግዚአብሔር ቁጣ እንደበረደ አብስራ፡ የሆሊ ቅጠልን፡ ወደ መርከቢቱ ይዛ እንደተመለሰችው ርግብ። ስለዚህ ክብሩን ወደ ሙሽራይቱ ክፍል ወደዚህ ወደ ከተማይቱ አምጥቶ፡ ንጉሱ ሲወጣ፡ ለጎረቤቱ ንጉስ ቅጠል ይዞ፡ “እኛ ለዘለዓለም በሰላም ውስጥ ነን፡” ይለዋል። አሜን! የሕዝቦች መፈወሻ! “ሁሉ ተጠናቋል። ወንድሜ ሆይ፡ በአንድ ወቅት አንዳችን ለአንዳችን ደም ተፋጅተናል። ተደስተናል፡ ጮኽናል፥ ተኩሰናል፡ ልጆችን አቃጥለናል፡ ሁሉንም

ነገር አድርገናል። አሁን ግን ሰላም አለ፡ ፈውስ።" በሽታ የመፈወስ ፈውስ አይደለም፥ ሁሉም ተጠናቋል። የሕዝቦች መፈወሻ! አሜን!

401 ዙፋኑ ከፍታዋ ላይ ያለባት ከተማ። ራእይ 21፥23፡ "መብራትም አያስፈልጋትም፡ በጉና ጌታ አምላክ መብራቷ ናቸውና።" አያችሁ? ጌታ አምላክ የእስራኤልን ልጆች በምድረ በዳ የተከተላቸው ያ የዕሳት ዓምድ ነው። ወደ ዙፋኑም ዐርጓል፡ በዚያ ፍጹም መንግሥት ውስጥ… ጊዜው… "እግዚአብሔር ሁሉ በሁሉ ይሆን ዘንድ፡ ኢየሱስ መንግሥቱን፡ ለአብ አሳልፎ የሚሰጥበት መንግሥት።" ኢየሱስ እዚህ ዙፋኑ ላይ፡ እንደ ዮሴፋችን ሆኖ ይቀመጣል። ንጉሡም በጽዮን ተራራ አናት ላይ የሚኖረው ያ ብርሃን ነው፡ ቅዱስ ብርሃኑም ከተማይቱን በሙሉ ያጥለቀልቃታል። ሃሌሉያ!

402 አንድ ሺህ አምስት መቶ ማይል ወደ ላይ፡ እንዲሁም አንድ ሺህ አምስት መቶ ማይልስ ስኩዌር፡ የእግዚአብሔር ገነት በዚያች ከተማ ሁሉ ውስጥ ተገንብቷል፥ መንገዶቿ፡ ጎዳናዎቿ! ራእይ 21ን አንብቡ፡ ትክክል መሆን አለመሆኑን እዩ። አያችሁ፡ "በጉ ብርሃኗ ስለሆነ፡ በዚያ መብራት አያስፈልጋቸውም።" ተቀምጦም፡ በሺህ አምስት መቶ ማይል ከፍታ፡ ዙፋኑ ይታያል።

403 **እንደዚህ** ቀጥ ብሎ ወደ ላይ አይወጣም። እንደ ፒራሚድ ወደ ጎን ዘንበል ያለ ነው። ርቀቱ ግማሽ ቢሆን ኖሮ፡ እንደምታዩት፡ ከአንድ ከተማ ወደ ሌላኛው ከተማ ልክ **እንደዚህ፡** ይዘረጋ ነበር… አሁን ካስተዋላችሁ፡ ከአንዱ የከተማዋ ጫፍ ወደ ሌላኛው ጫፍ ነው።

404 ከፈለጋችሁ እዚህ ጋር ትንሽ ነገር ጣል ላድርግላችሁ እችላለሁ። እዚህ ያለውን ትንሽ ቡድን አስተዋላችሁን? የሚሸፍነው ቦታ፡ ልክ ይህንን ክፍል ያህል ነው። ጆርጂያ፡ ካሊፎርኒያ፡ እስከ ሳስካችዋን፥ ከካንሳስ፡ እስከ ሜይን ሮክ-ባውንድ የባህር ዳርቻ፥ የተሰበሰቡት እነዚህ ናቸው። እዚህ ጋር የተወከለው በግምት ያንኑ ነው፡ ወደ አንድ ሺህ አምስት መቶ ስኩዌር ማይል የሚጠጋ ስፋት።

> ኦህ፡ ከምሥራቅና ከምዕራብ ይመጣሉ፡
> ከሩቅ አገር ይመጣሉ፡
> ከንጉሣችን ጋር ሊበሉ፥ ሊመገቡ… (በምን ላይ? "ሰው በእንጀራ ብቻ አይኖርም።" በእንጀራ፡ በቃል!)… እንደ እንግዶቹ ሆነው ሊመገቡ፥
> እነዚህ መንገደኞች እንዴት የተባረኩ ናቸው!

መናገር ካለብኝ፡ በዓለም ውስጥ፡ እንደ እነርሱ ያለ ህዝብ አይቼ አላውቅም።

> ኦህ፡ የተቀደሰ ፊቱን ሲመለከቱ
> በመለኮታዊ ብርሃን እያበሩ፥
> የጸጋው ተካፋዮች የሆኑት ብፁዓን፡
> በዘውዱ ውስጥ እንዳሉ ዕንቁዎች ያበራሉ።
> ኦህ፡ ኢየሱስ በቅርቡ ይመጣል፡
> መከራችንም ያኔ ያበቃል።
> ኦህ፡ ጌታችን በዚህች ቅጽበት ቢመጣስ?

405 ብዙም አይቆይም። ሁሉም ነገር ፍጹም ነው። በመልክዓ ምድር አቀማመጥ፡ ሰዶም፡ መልእክተኞቹ፥ ሁሉም ነገር ልክ በትክክል ተቀምጧል። አያችሁ? ምን ማለት ነው? አስቡት እስቲ፡ አንድ ሺህ አምስት መቶ ማይል ስኩዌር ከሆነው ተመሳሳይ ሰፋት፡ ወደዚህች አንዲት ትንሽ ማደሪያ ድንኳን መምጣት።

406 እግዚአብሔር ስለዚያች ትንሽ የፍልስጤም ሰፍራ ትንሽዬ ቦታ ስትሆን፡ አያችሁ፡ ለምን ያን ያህል አሰቦ ተጨነቀ? ነገር ግን ልክ እዚያ ውስጥ ነው ቤተ መቅደሱ የተቀመጠው። አዲሲቷ ኢየሩሳሌም የምትወጣው፡ ልክ እዚያ ነው። "ደብረ ዘይት፡ የደብረ ዘይት ተራራ ይሰነጠቃል፡ ወደ ቀኙና ወደ ግራ ይከፈላል፡" እርግጥ ነው፡ ከሰር ወደ ላይ ስትገፋ ይከፈላል። እነርሱ እንደሚሉት፡ **እንደዚህ**፡ ወደ ጎን አይደለም የሚገፋው። "በዚያ ቀን ቅዱስ እግሮቹን በተራራው ላይ በሚያቆምበት ጊዜ፡" ወደ ላይ ነው የሚገፋው። አስተውሉ፡ በዙፋኑ ላይ፡ አንድ ሺህ አምስት መቶ ማይል ወደ ላይ ከፍ ይላል!

407 አስታውሱ፡ በአንድ ወቅት፡ ሰይጣን በተራራ ጫፍ ላይ፡ ሊፈትነው ሞክሮ ነበር። አያችሁ?

408 አዲሲቷ ከተማ አሥራ ሁለት መሠረቶች አሏት፡ እንዳየነው፡ አሥራ ሁለቱ የአበው አለቆች፥ መቶ አርባ አራት ክንድ፥ የአሮን የደረት ልብስ ሆኖ፥ አሥራ ሁለቱ የዕንቍ ደጆች፡ የአሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት ስም።

409 ኢየሱስ፡ የማዕዘን ራስ ሆኖ፡ በዙፋኑ ላይ የቆመው፡ ቅዱሳኑ "የነገሥታት ንጉሥ፡ የጌቶች ጌታ" ብለው አክሊል ሲያቀዳጁት ነው። እርሱም የማዕዘኑ ራስ ነው

410 የኪስ ቦርሳዬን አልያዝኩም። ነገር ግን በኪስ ቦርሳችሁ ውስጥ ካያችሁ፡ የአንድ ዶላር ኖት ካላችሁ፡ የዩናይትድ ስቴትስ ማኅተም አላቸው፥ በአንደኛው ጫፍ፡ የጦር መሣሪያዎችን፡ የጦር ካባን የያዘ፡ ንስር አለ፥ በሌላኛው ጫፍ፡ ደግሞ ፒራሚዱ አለ፡ በላዩም ላይ ሁሉን-የሚያይ ዓይን አለው። አያችሁ፡ ምን እያደረጉ እንደነበር አላወቁም። በእርሱም ላይ በላቲን ተጽፏል፡ ይህ "ታላቁ ማኅተም" ነው፡ የሚል ታገኛላችሁ። ምን እያደረጉ እንደነበር አላወቁም። ቀያፋም ትንቢት እየተናገረ መሆኑን አላወቀም ነበር።

411 [ወንድም ብራንሃም በሰሌዳ ላይ አሰረዳ—አርታዒ።] ታላቁ ማኅተም ይኸውላችሁ። **ይኸውላችሁ**፡ አያችሁ፡ ከተማይቱ። **እንደዚህ** ጠፍጣፋ አራት ማዕዘን አይደለም፡ አያችሁ፡ ነገር ግን እንዲታይ ወደ ላይ ያጋደለ ነው። በዚህም በተቀደሰው የጌታ ተራራ ላይ፡ ጌታ በተራራው አናት ላይ ይወርዳል፥ ይሄውና **እዚህ**። ለዚህ ነው የማዕዘኑ ራስ በሄኖክ ያልተቀመጠው። አያችሁ? ለዚህ ነው የማዕዘኑ ራስ አሁን መምጣት ያለበት። ተራራውም ወደ ላይ ይገፋል፡ የጌታም ተራራ ይሆናል።

412 **እዚህም** ውስጥ የተበዡት ይኖራሉ። **እነዚህ፡** ጎዳናዎችና ትላልቅ አውራ ጎዳናዎች፡ እንደነበሩት፡ ፓርኮች፡ የሕይወት ወንዝም ይፈሳል፡ ልክ በእርሱ ውስጥ ያልፋል። እያንዳንዱም ቤት ከሚያንጸባርቅ ወርቅ የተሠራ ይሆናል። መንገዶቹም ከወርቅ የተሠሩ ይሆናሉ። የሕይወት ዛፎችም በዚያ ይኖራሉ፡ አሥራ ሁለት ዓይነት ፍሬንም ያፈራሉ። የምድር ነገሥታትና የተከበሩ ሰዎችም

ክብራቸውንና ሞገሳቸውን ወደ በሮቹ ያመጣሉ። በዚያም ሌሊት ስለሌለ፡ በሮቹ በሌሊት አይዘጉም።

በጉ መብራቷ በሆነባት በዚያች ከተማ፡
ሌሊት በማይመጣባት በዚያች ከተማ፥
ከድካምና ከጭንቀት ነፃ የሆነ መኖሪያ እዚያ አለኝ፡
ኦህ፡ በጉ መብራት ወደሆነበት ወደዚያ እሄዳለሁ።

413 አሁን መ—መንደሮች፡ ከተሞች፡ ቤቶችና፡ መኖሪያ ሰፍራዎች፡ ሰ—ስለዚያ እየተናገሩ እንደሆነ አይታያችሁምን? እነዚህ የተፈጥሮ ነገሮች ሁሉ ጥላ ናቸው።

414 እንደ እጄ ጥላ፡ በርቀት ያረፈ፡ እንደ ምሳሌ እንውሰድ። አዎንታዊ ነገር ከመኖሩ በ—በፊት... ማለቴም አሉታዊ ነገር ከመኖሩ በፊት፡ አስቀድሞ አዎንታዊ ነገር መኖር አለበት። እንግዲህ፡ ተመልከቱ፡ ያ ጥላ፡ አሥራ ሁለት ጣቶች ያሉኝ ያስመስላል፡ ነገር ግን ይበልጥ እያቀረባችሁት ስትመጡ፡ ተ—ተሰብስቦ አንድ ይሆናል፡ ከዚያም ጥላው ከራሱ ከእጁ ጋር ይዋሃዳል።

415 ለዚህም ነው፡ ብዙ ጊዜ፡ ሰዎች ሦስት ወይም አራት አማልክት ያሉ ይመስላቸዋል። በቀድሞዎቹ ተሃድሶዎች ውስጥ በጣም ወደ ኋላ እየተመለከታችሁ ነው። አያችሁ? አሁን ወደዚህ ቀረብ በሉና፡ አጥርታችሁ ስትመለከቱ አንድ ብቻ ሆኖ፡ ታገኙታላችሁ። በትክክል።

416 አንዲት ሙሽራ አለች፥ እንጂ አንድ ደርዘን፡ የሐይማኖት ተቋም አይደለም። ነገር ግን አንዲት ሙሽራ ብቻ አለች፡ እነርሱም፡ ከመላው... ምድር የተውጣጡ፡ ለዚህ አስቀድመው የተወሰኑና፡ በመንግሥቱ ውስጥ ያላቸውን ሰፍራ ለይተው ማወቅ የሚችሉ የተመረጡት ናቸው።

417 በዚህ ዙፋን ላይ፡ ተመልከቱ፡ በጣም ከፍ ያለ ነው! አዲሲቷ ከተማ፥ ከመሠረቶቿ ጋር፥ አሥራ ሁለት ደጆች፥ ኢየሱስ፡ የማዕዘኑ ራስ፥ ሐዋርያት፡ በአሥራ ሁለቱ ነገዶች ላይ ሲፈርዱ ተመልከቱ።

418 የሄኖክ ፒራሚድ በቀኑ ውስጥ በማንኛውም ሰዓት ምንም ዓይነት ጥላ አያጠላም። እዚያው ፒራሚዶቹ ባሉበት፡ በግብፅ ነበርኩ በመልክዓ ምድር አቀማመጥ፡ በዚህም ታላቅ የጂኦሜትሪ ቅርጽ ሰፋት ውስጥ በጣም የተስተካከለ ነው፥ ይህም፡ ፀሐይ የትም ብትሆን፡ በፒራሚዱ ዙሪያ ምንም ጥላ አይኖርም። እንዴት እንደሆነ አያችሁ?

419 በዚያም ከቶ ሌሊት አይኖርም። በተራራው ጫፍ ላይ ያለው እርሱ፡ በክብሩ ያጥለቀልቀዋል። የክብሩ ብርሃን ሁልጊዜ በዚያ ይኖራል። በዚያ ሌሊት አይኖርም። ኢየሱስ፡ የማዕዘኑ ራስ!

420 አሁን አስተውሉ። ስለዚህ፡ የተበዡት በብርሃን ውስጥ ይመላለሳሉ። አሁን፡ "በብርሃን እንመላለሳለን፡ በዚያ ውብ ብርሃን" ብለን እንዘምራለን። በውስጣችን የሆነ የሚጣራ ነገር አለ። "ከሞት ወደ ሕይወት ተሻግሯል።" ምክንያቱም ያ እየጠበቀን ነው። አያችሁ? የሚሰማን፡ ባህሪው ይህ ነው።

421 በእውነት፡ ይህ... ዝግጁ ናችሁ? አብርሃም ሲፈልጋት የነበረችው ከተማ ይህች ናት። አያችሁ? ነቢይ በመሆኑ፡ ያች ከተማ የሆነ ቦታ እንዳለች ያውቅ ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲሁ ይላልና። የኖረባትን ከተማ ትቶ ሄደ፡ ሄዶ

ተመለከተ፥ የት እንደሄደ ተመልከቱ፡ በትክክል እርሰዋ ወደ ምትሆንበት ስፍራ። አያችሁ? አያችሁ፡ ነቢይ በመሆኑ፡ “ፈጣሪዋና ሰሪዋ እግዚአብሔር የሆነላትን ከተማ ይጠብቅ ነበር።”

422 ኢየሱስ በመለኮታዊ እጆች፡ መለኮታዊ ከተማን፡ ሊያዘጋጅ ሄዷል፥ መለኮታዊ አርክቴክት፥ በመለኮት-ለተገዙ ሰዎች፡ አስቀድመው ለተወሰኑ ሰዎች። እርሱ ሊያዘጋጅ ሄዷል።

423 አብርሃም እርሰዋን ይፈልግ ነበር። “እግዚአብሔር የሠራትንና የፈጠራትን ከተማ ይፈልግ ነበርና፡ እንግዳና መጻተኛ መሆኑን መሰከረ።” ያ ነቢይ፡ የሆነ ቦታ እንዳለች አውቆ ነበር! ዮሐንስ ሰትወርድ አያት፡ አብርሃም ግን ያኔውኑ በምድር ላይ ያለች መሰሎት ነበር። ለምን? የእርሰዋን ንጉሥ፡ መልከጼዴቅን አገኘው፡ አሥራትም ሰጠው። “አባትና፡ እናት የሌሉት። የሕይወቱ መጀመሪያም ሆነ መጨረሻ የሌለውም።” አብርሃም አገኘው፡ ከተማይቱ በምትነሣበት በትክክለኛው ስፍራ፡ የተበዙት በሚኖሩበት፡ በተቀደሰው የጌታ ተራራ ላይ የጌታ እራት በሉ። ኦህ፡ ማይ!

424 ያ ጊዜ እንዲሁ አያቆምም። አይ፡ እኛ በጊዜ ውስጥ ነን፥ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ወደ ዘላለም እንገባለን።

425 ኦህ፡ ቅዱስ ተራራ! ከሚያንጸባርቅ ወርቅ የተሠሩ መንገዶች፡ ጎዳናዎች፡ ቤቶችና፡ ፓርኮች ይኖራሉ። ይህንን ማንበብ ከፈለጋችሁ፡ ራእይ 21፥18 ላይ ተመልከቱ። የሕይወት ዛፍ በዚያ ይኖራል፥ አሥራ ሁለት የተለያዩ ፍሬዎች፡ በየወሩ፡ የተለያዩ ታፈራለች። እነዚህን ፍሬዎች የሚበሉ ሰዎች፡ በየወሩ፡ ምግባቸውን ይቀይራሉ።

426 እ—እርሱ ከ... ለድል ነሺዎች ብቻ ነው። ያንን ታውቃላችሁ? ለሐይማኖት ተቋማት አይደለም።

“እውነትህን ነው፡ ወንድም ብራንሃም፡” ትላላችሁ?

427 ለአንድ ደቂቃ ያህል፡ ወደ ራእይ 2 ከፍተን፡ እንመልከት። ራእይ 2፥7። አሁን ይህ በእርግጥ እውነት መሆኑንና አለመሆኑን እንመልከት። ራእይ 2፥7 እንዲህ ይነበባል።

**ጆሮ** ያለው**ም፡ መንፈስ የሚለውን ይሰማ...**

428 አሁን፡ አስታውሱ፡ አሁን ለአይሁዶች እየተናገረ አይደለም። ይህች ቤተ ክርስቲያን ናት፡ አሕዛብ።

**መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን፡ ጆሮ ያለው ይሰማ፥ ድል ለነሣው በእግዚአብሔር ገነት መካከል ካለው፡ ከሕይወት ዛፍ እንዲበላ እሰጠ**ዋለሁ**።**

429 “እውሬውን ድል ለነሱ፡ ምልክቱንም ድል ለነሱ፡ ድል ለነሱት ብቻ፡” ይህም ካቶሊካዊነትን፡ ፕሮቴስታንትነትን፡ የሐይማኖት ተቋምነትን ነው፡ “አውሬውን፡ ምልክቱን፡ የሰሙን ፊደል ድል ለነሱ።” “የሚያረክስ ነገር ወደማይገባበት በሮች የመግባት መብት፡ ወደ ሕይወት ዛፍ የመግባት መብት ይኖረዋል።” አያችሁ? እስቲ አስቡት። አሁን፡ ጥቂት ወደፊት ሰንሄድ፡ ለአፍታ ታገሱ። የሕይወት ዛፍ ለድል ነሺዎች ብቻ ይሆናል።

430 ቅጠሎቹ ለሕዝብ መፈወሻ ይሆናሉ። ይኸውም፡ በዚያ የሚኖሩት ነገሥታት፡ ክብራቸውን አምጥተው፡ በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት ሲያስቀምጡት ክብራቸውን ይዘው ይመጣሉ። ልክ እዚያ እንዳሉት፡ አሥሩ... አሥራ አንዱ ነገዶች፡ እያንዳንዳቸው፡ ከዐሥር አንድ ለሌዋ እንዳመጡለት ነው፡ አያችሁ። ከተባረከችው ምድር... ክብራቸውን ሲያመጡ፡ በዚያ፡ ከሕይወት ዛፍ ላይ፡ የወይራ ቅጠል... ወይም የሕይወት ዛፍ ቅጠል ቀንጥሰው፡ አብረው ይወጣሉ። ከእንግዲህ ጦርነት የለም። ሁሉም ነገር በሰላም ነው። ቅጠሎቹ መታሰቢያ ናቸው፡ ለሕዝብ መፈወሻ ናቸው።

431 ያው ተመሳሳይ ዛፍ፡ እንደ አዳም ሳይሆን፡ እርሱ... በኤደን ገነት ውስጥ የሕይወት ዛፍ ነበረ፡ ባይወድቅ ኖሮ ሊበላው ይችል ነበር። ያ የሕይወት ዛፍ፡ አዲሱ... ወጣትነቱ ዘወትር፡ እንደሚቀጥል ሁልጊዜ ያስታውሰው ነበር። አያችሁ?

432 ለሕዝቡም እንዲሁ ይሆናል። ቅጠሎቹም ለሕዝብ መፈወሻ ይሆናሉ፥ አስተውሉ፡ አሁን ለበሽታ አይደለም። ልክ እንደ አዳም ተመሳሳይ መብት ይኖራችኋል፡ ልክ እንደ እርግ-... ርግብ የወይራ ቅጠል እንደያዘችው፡ ሁሉም... እያንዳንዱ ንጉሥ ቅጠል ይወስዳል።

433 አስተውሉ፡ የሕይወት ወንዝ፡ ምናልባትም ብዙ ትናንሽ ጅረቶች ተደማምረው ይፈጥሩት ይሆናል። አሁን፡ በዚህች ምድር...

434 በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ እጨርሳለሁ። በዚህች ምድር... ወይም፡ አሁን ላቆም ነው። አሁን ወደ ሠላሳ ገጾች የሚጠጉ፡ **ይህን** የሚያክል ተጨማሪ ማስታወሻዎች አሉኝ። አዎን። ተመልከቱ።

435 በ—በዚህ ሕይወት፡ በቀደም ምሽት እንደሰበክሁት ተራሮች ውስጥ ሆኖ ያንን የሚፈልቅ ምንጭና፡ ሕይወት-ሰጪ ውኃውን ከማግኘት የበለጠ፡ ጥማትን የሚያረካ ነገር፡ ከቶ አይቼ አላውቅም። ደክሟችሁና ጠምቷችሁ፡ ሄዳችሁ በጥሩ ጅረት አጠገብ ትወድቃላችሁ፥ ከምድር በታች በመቶዎች የሚቆጠሩ ጫማዎች፡ ጀርሞች ሊሄዱ በማይችሉበት ጥልቀት ውስጥ፡ ንጹሕ፡ እውነተኛ፡ ሕይወት-ሰጪ ውኃ ይፈልቃል። ያንን እናደንቃለን። ያ ትንሽ ነው። አሁን፡ ምድር ብዙ የሚያረኩ የውኃ ጅረቶች አሏት። በምትጠሙበትና በምትሞቱበት ጊዜ፡ ከዚያ ጥሩ፡ ቀዝቃዛ ውኃ ስትጠጡ፡ በሕይወት እንድትኖሩ ይ—ይረዳችኋል።

436 ነገር ግን ይህኛው ከየት እንደሚመጣ ተመልከቱ። ከዙፋኑ፡ ሕይወት-ሰጪ ምንጮቹን የሚያገኘው ከዚያ ነው። እግዚአብሔር ከተቀመጠበት፡ ከዙፋኑ ሥር ይመጣል።

437 ሁሉም፡ ይህች ምድር ሁሉ፡ አሁን የምንኖርባት ይህች ምድር፥ ክርስቲያንም ሆነ አረማዊ፡ እያንዳንዳቸው፡ ቤተ መቅደሶች አሏቸው። ይህን አስባችሁበት ታውቃላችሁ? አብያተ ክርስቲያናት፡ ሁሉም አሏቸው።

438 ይህኛው ግን ምንም የለውም። መጽሐፍ ቅዱስ፡ "በእርሰዋም መቅደስ አላየሁም። ጌታ አምላክና በጉ መቅደሰዋ ናቸውና" ይላል። በጉ መብራቷ ነው። በጉ ቤተ መቅደሱ ነው። በጉ ዙፋኑ ነው። በጉ ሕይወቱ ነው። እርሱ ያ ቤተ መቅደስ ነው። አያችሁ፡ እነዚህ ቤተ መቅደሶች ሁሉ የሚያመልኩት ነገር አላቸው፥ በዚህች ከተማ ግን፡ የአምልኮው ማዕከል እርሱ ነው። እርሱ ከሕዝቡ ጋር ነው። የመንፈሱ ብርሃን የፒራሚድ ከተማዋን ያጥለቀልቃታል።

439 ጴጥሮስና ዮሐንስ፡ በተራራው አናት ላይ እንደነበሩት ነው። ብርሃኑ የተራራውን ጫፍ ሸፈነው፡ ድምፅም መጣ፡ “በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው፡” አለ።

440 በራእይ 21፥3ና 4፥ “የእግዚአብሔር ማደሪያ ከሰዎች ጋር ነው።” እግዚአብሔር ሰውን በመዋጀት፡ በእነዚህ ሦስት ሂደቶች፡ በሰው ውስጥ አድሯል። አሁን እግዚአብሔር ምድርን ሊዋጃትና ከምድር ካወጣቸው፡ የምድር ተገዢዎቹ ጋር፡ በምድር ላይ ሊያድር ነው። በኃጢአትም ምክንያት ወደቀች፡ ነገር ግን... እንድትቀጥል ማድረግ ነበረበት። አሁን ግን እኛ አካሏ የሆንባትን፡ ያችን የወደቀችውን ምድር ሊዋጅ ኢየሱስን ላከው። “ከራሳችሁ አንዲት ጠጉር ስንኳ አትጠፋም።” ኢየሱስ እንዲሁ ብሏልና። “በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ” አለ። አያችሁ? ለምን? እናንተ የምድር አካል ናችሁ።

441 አስተውሉ፡ ሚስቴ ፀጉሬን እንዳጣሁ ስትነግረኝ ያደረግኩት ትንሽ ቀልድ ነበረኝ። አንዳቸውንም እንዳላጣሁ ነገርኳት።

እርሷም፡ “የት ናቸው ታዲያ” አለችኝ?

442 እኔም፡ “እኔ ሳላገኛቸው በፊት በነበሩበት ቦታ” አልኳት። የትም ይሁኑ፡ ቁስ አካል ናቸው፥ የትም ቢሆኑ፡ እኔን እየጠበቁኝ ነው። አያችሁ? በትክክል። አንድ ቀን፡ ወደ እነርሱ እሄዳለሁ።

443 ይህ አሮጌ ሥጋ፡ እየተሸበሸበና እየወደቀ፡ ትከሻውም እየጠበበ፡ ጉልበቱ እየታመመ፡ ጉሮሮውም—እየጎረነነ ይሄዳል። ይህም ምንም ችግር የለውም። በባሕር ውስጥ ልትቀብሩት ትችላላችሁ፡ መለከቱ ግን ይቀሰቅሰኛል!... ? ... አዎን፡ ወዳጄ። ከእነዚህ ቀናት በአንዱ፡ እንለወጣለን። እኔ የተዋጀው የዚህ ዓለም አካል ነኝ። እናንተ በዓለም ውስጥ ናችሁ፡ ነገር ግን ከዓለም **ከኮስሞስ** ምንም የላችሁም። እናንተ በተለየ ሥርዓት፡ በተዋጀ ሥርዓት ውስጥ ናችሁ።

444 አስተውሉ፡ “የእግዚአብሔር ማደሪያ ከሰዎች ጋር ይሆናል።” አስተውሉ፡ “የቀድሞው ሥርዓት አልፏል።” ይህ፡ ይህ ነገር፡ አልፏል። ይህ ማለት መንግሥተ ሰማያት ከሰው ጋር ልትኖር ወርዳለች ማለት ነው። አያችሁ? ሰማይና ምድር ተቃቅፈዋል።

445 ልክ ርግብዋ የሰው ልጅ በነበረው፡ በኢየሱስ ላይ፥ በዚያ የምድር አካል ላይ በወረደች ጊዜ፡ እርሱ የምድር አፈር፡ ሰው ነበረ። እግዚአብሔር፡ ከዚያች ከአንዲት ትንሽ የሕይወት-ዘር፡ በመፍጠር ኃይል መጣ። በዚያም ውስጥ የነበረው ያ ደም... በዚያ ደም ውስጥ የነበረው ሕይወት ወደ እግዚአብሔር አረገ፡ ደሙ ግን ምድርን የራሱ ለማድረግ፡ በምድር ላይ ተንጠባጠበ።

446 ከቃየል የዘር ህዋስ፡ ተላልፎ በመጣው ደም የተነሳ፡ አያችሁ፥ አሁን ልክ የመጀመሪያውን አዳም ሲፈጥር እንደተጠቀመበት ዓይነት የመፍጠር ኃይል ይዞ ይመለሳል፡ ይሄውና ሁለተኛው አዳም። በዚያም በፈሰሰው ሴል በኩል፡ ቃየል (በኃጢአት) ያንን የጻድቁን የደም ሴል ባፈሰሰበት ቦታ፡ አያችሁ፡ አሁን ይህ የደም ሴል አለ... ምክንያቱም፡ እርሱ አቤልን ገደለው፡ አቤል ግን በግብረ ሥጋ ግንኙነት የተወለደ ነበር።

447 ይህኛው ግን በግብረ ሥጋ ግንኙነት አልተወለደም። “የእግዚአብሔር ፍጥረት ነበረ፡ መጀመሪያው፡” ምድርንም ዋጀ። እንዲሁም እናንተ

የተሠራችሁበት፡ ካልሲየም፡ ፖታሽ፡ ፔትሮሊየም፡ የኮስሚክ ብርሃን ሁሉ፡ የተዋጀ ነው። “አንዲት የራስ ጠጉር እንኳ አትጎዳም። በመጨረሻውም ቀን አስነሣዋለሁ።”

448 ከዚያስ ምን? እግዚአብሔር በምድር ላይ ሊኖር ይወርዳል። የራሱ አካል የሆነው፡ የዚህ የምድር፡ ክፍል ነው። ለጽድቃችን አስነሣው፡ እኛም ያንን በማመንና ያንን በመቀበል ጸድቀናል። በጥላዎች ውስጥ አስተውሉ፡ ኢየሱስ... በጥላው ውስጥ፡ ኢየሱስ ሰው ይሆናል፥ እኛን ለመዋጀትና፡ እነዚህን ሁሉ ነገሮች እውን ለማድረግ፡ እግዚአብሔር... የሰውን ሰፍራ እንዲተካ አስቀድሞ ተወሰኖ ነበር።

ከዚህች ከተማ ውብ ግንቦች፡ ውጭ ያለውን ነገር፡ አስተውሉ።

449 አሁን “ከተማይቱን” ተረድታችኋል? እያችሁ፡ ቅዱስ ተራራ ነው። [ወንድም ብራንሃም በስሌዳ ላይ ያስረዳል—አርታዒ።] “በተቀደሰው ተራራዬ ሁሉ ላይ የሚጎዳ ወይም የሚያጠፋ ነገር አይኖርም፡ ይላል ጌታ።” ከተማይቱ አራት ማዕዘን አይደለችም። ተራራ ናት። ር—ርዝመቷ፡ ስፋቷና ከፍታዋ እኩል ናቸው፡ እያችሁ፥ ወደ**ዚህ** አንድ ሺህ አምስት መቶ ማይል፡ ወደ**ዚያ** አንድ ሺህ አምስት መቶ ማይል፡ ዙርያዋ ሺህ አምስት መቶ ማይል፥ እንዲሁም ከፍታዋ አንድ ሺህ አምስት መቶ ማይል። ስለዚህ ልክ እንደ ፒራሚድ ያለ፡ ትልቅ ተራራ ነው፡ ከተማይቱም በተራራው ላይ ናት። ክብር!

450 የእግዚአብሔር ገነት፡ የዓለም ብርሃን፡ ያ ፍጹም መንግሥት፡ ይሄውና። ሰባተኛው ቀን አይደለም፥ የዘላለም የሆነው ነው! እያችሁ? የሺህ ዓመቱ መንግሥት አይደለም፥ አዲሲቱ ምድር ናት! እያችሁ?

451 በሺህ ዓመቱ መንግሥት ውስጥ እያለፈች ሳለች፡ በማንጻት ሂደትዋ ውስጥ እያለፈች ነው፡ ነገር ግን አሁንም መቃጠል አለባት። እያችሁ? ማለት፡ ደሙ ሕዝቡን ዋጀ፡ ይህ መታሰቢያ መሆኑን... ለዚያ ሺህ ዓመት፡ ዋጋው መከፈሉን ያሳያል። ነገር ግን ከዚያም ልክ እንደ እናንተ፡ የዚህች ከተማ ወኪሎቹ፡ ልዑካኑ፥ በእሳት መንጻት አለበት።

452 ስለዚህ ብትሞቱ ሆነ በሕይወት ብትኖሩ፡ ምን ልዩነት ያመጣል? ዛሬ ቢመጣ፡ ወይም ከመቶ ዓመት በኋላ፡ ወይም ከሺህ ዓመት በኋላ ቢመጣ፡ እስኪለወጥ ድረስ ዝምብዬ አርፋለሁ።

453 ስለዚህ፡ ሽማግሌ ወንድና አሮጊቷ ሴት፡ ተስፋ አትቁረጡ። [ወንድም ብራንሃም በስሌዳ ላይ ያስረዳል—አርታዒ።] እናንተ **እዚህ** ላይ ውክልና ካላችሁ፡ በዚህ በእግዚአብሔር ባህሪ ውስጥ፥ **ይህ፡** እግዚአብሔር፥ ይህ ካላችሁ፡ **እዚህ** ከተወከላችሁ፡ እናንተ ልትጠ... በዘላለማዊው ውስጥ ናችሁ። ከዚያም ከሰባተኛው ቀን ተሻግራችሁ፡ ወደ ሰምንተኛው ከገባችሁ፡ በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ወደ ዘላለማዊው ገብታችኋል፡ **በዚህ** ውስጥ ተካትታችኋል። አሁን፡ ዝም ብላችሁ በስሜት ላይ የምትታመኑ ከሆነ፡ ወይም እየዘለላችሁ፡ ወይም፡ “**ይህንን** አደርጋለሁ። ሰባተኛ ቀኔን እጠብቃለሁ። ሥጋ አልበላም፡” የመሳሰሉትን ነገሮች የምትሉ ከሆነ፡ ያ ያም ሆነ ይህ፡ ይጠፋል። እያችሁ? **ይህኛው** ግን ዘላለማዊው ነው። እያችሁ? ይህ ዘላለማዊው ነው፡ ከዳስ በዓል በኋላ ያለው በዓል። እያችሁ?

454 የዳስ በዓል የመጨረሻው በዓል ነበረ፡ ሰባተኛው በዓል። አሁን እኛ በዳስ በዓል ሥር እያመለክን ነው፡ በሰባተኛው የቤተ ክርስቲያን ዘመን።

455 በሺህ ዓመቱ መንግሥት፡ እንደገና፡ በሰባተኛው ቀን፡ በዳስ በዓል ሥር እንሆናለን።

456 ነገር ግን፡ ከዚያም፡ ከሰባተኛው ቀን በኋላ፡ ቅዱስ ጉባኤ ይኖረናል፡ ወደ ዘላለማዊው እንመለሳለን። እንዴት? መጥቶ በዋጀንና ወደ ኋላ በመለሰን፡ **የዚህ** ክፍል እንደነበርን እንድናውቅ ባደረገን በዚያ ዘላለማዊው።

457 አሁን አካል መሆናችሁን እንዴት ታውቃላችሁ? ምክንያቱም፡ ያ፡ የዘመኑ ቃል፡ የዘመኑ ተስፋ ነው። ምንድን ነው እርሱ? ወደ መጀመሪያው ቀን፡ ወደ መጀመሪያው መመለስ ነው። "የልጆችንም ልብ ወደ አባቶች ይመልሳል፡" ይህም የጴንጤቆስጤን እውነተኛነት እንደገና በማምጣት ነው፡ ስሜቶችን አይደለም፥ ለቀኑ እንደተገባው ቃል፡ በጠዋቱ ብርሃን የታየው ያው ልጅ፡ የምሽቱን ብርሃን ይገልጣል። አሜን አሜን!

458 የት ነን፡ ወዳጆቼ፡ የት ነን? ዝም ብለን የራዕይ፡ ምዕራፍ 11 ለአይሁዶች እንዲገለጥ... አሁን ከመንገድ ገለል ለማለት ብቻ እየጠበቅን ነው፥ በትክክል፡ ንጥቀት እየመጣ ነው።

459 ተመልከቱ፡ ከቅጥሩ ደጆች ውጭ፡ በአዲሲቱ ምድር ላይ ተዘርግተው፡ ሕዝቦች በዘላለማዊ ሰላም ይኖራሉ። አሁንስ ምን? የተከበሩ ነገሥታት ክብራቸውን ወደ እርስዋ ያመጣሉ። በዚያ ምንም ኃጢአት ሊኖር አይችልም። ፀጉሯን-የተቆረጠች ሴት ከእንግዲህ ወደዚያች ከተማ አትገባም። ያንን አረጋግጥላችኋለሁ። አጫጭር ልብሰ-የሚለብሱ፡ ሲጋራ-የሚያጨሱ፥ አመንዝሮች፡ ጋለሞታዎች፡ ወይም ውሽታሞች፡ ጣዖት አምላኪዎች፡ ምንም ቢሆኑ፡ ወደዚያች ከተማ አይገቡም። አይ፡ ሁሉም ያበቃል። ኃጢአት ይጠፋል። "ቅድስናዋን የሚያረክስ ምንም ነገር በዚያ አይገባም።" እርሱ ያለው ያንን ነው። "ሁሉም ለዘላለም፡ አልፏል።"

460 ወደ ሜዳዎቿና በበሮቿ ዙሪያ ተመልከቱ፥

> ድቡ ገር ይሆናል፡ ተኩላውም ይገራል፥
> አንበሳውም ከበጉ ጋር ይተኛል፥
> ከጫካ የወጣ አውሬ፡ በሕፃን ይመራል፥
> አሁን ካለሁበት ተፈጥሮ እለወጣለሁ።

461 ይህ ሞት በሚሞተው ሥጋዬ ውስጥ እየሠራ፡ እርጅና እየተጫነኝ፡ እኔ እለወጣለሁ።

462 መዝሙሩን ሰምታችኋል? "ድቡ ገር ይሆናል። ተኩላውም ይገራል።" አይዘልም፡ ተነስቶ ሊገድላችሁ አይሞክርም። በመንገዶቹ ላይ አብሯችሁ ይራመዳል።

ማን ነው ሊወርሰው ያለው? የተዋጁት። እነማን ይሆናሉ?

አስተውሉ፡ አሁን ማስተማር የምችለው በጥላዎች ብቻ ነው። አስተውል፡ ወንድም ሊ።

463 ከነቢዩ ኖኅ ጋር በአዲሲቱ ምድር ላይ የወጣው ማን ነው? ከእርሱ ጋር ወደ መርከቢቱ የገቡት። ልክ ነው? በዚያ ላይ የሚራመደው እርሱ ነው። እያችሁ?

በውኃ ጥምቀትዋ ካለፈች በኋላ፡ በአዲሲቱ ምድር ላይ የወጡት፡ በመልእክቱ አማካኝነት ከኖኅ ጋር የገቡት ናቸው

464 አሁን ከኢየሱስ ጋር የሚገባው ነው። ወደ እርሱ እንዴት ትገባላችሁ? በአንድ መንፈስ፥ እርሱም ቃሉ ነው። የእርሱ አካል ትሆናላችሁ። እናንተ የእርሱ የትኛው አካል ናችሁ? በዚህች ሰዓት ሕያው የሆነውን ቃል፡ በመለየት ነው። በሺህ ዓመቱ መንግሥት ከእርሱ ጋር ትወጣላችሁ። የምትወጡት ያኔ ነው። አስተውሉ፡ አዲስ ትውልድ አይደለም። ንቅለ ተከላ!

“ኦህ፡ ወንድም ብራንሃም፡” ትላላችሁ! ኦህ!

465 አስተውሉ፡ እግዚአብሔር ኤልያስን አስነስቶ፡ ከሃያ-አምስት መቶ ዓመታት በፊት ወስዶት፡ ለአይሁዶች ነቢይ እንዲሆን፡ ወደ ምድር መልሶ ትራንስፕላንት ካደረገው፡ ለሙሽራይቱማ ምን ያህል አብልጦ ያደርግ ይሆን!

466 ኖኅ ከመርከቢቱ ከወጣ በኋላ፡ ከጥፋት ውኃው ከወጣ በኋላ ለኖኅ የተነገረውን አስተውሉ፡ ልክ ከዚህ በፊት ከአዳም ጋር እንደነበረው ነበር። በአዲሲቱ ምድር ላይ ከወጣ በኋላ፥ “ብዙ፡ ምድርንም ሙሉአት፡” አለው፡ ከጥፋት ውኃው በኋላ። አስተውሉ፡ ልክ በመጀመሪያው አዳም እንደነበረው፡ “ያፈራ ዘንድ፡ ምድርንም ይሞላ ዘንድ ነበር።”

አሁን እዚህ ጋር በትክክል ማየት ትችላላችሁ። አሁን በደምብ አድምጡ።

467 አዳም “እንዲበዛና ምድርን እንዲሞላ” ነበረ። ልክ ነው? ኖኅም፡ ከአዲሱ በኋላ፡ (ዓለም ከጠፋች በኋላ)፡ “እንዲበዛና ምድርን እንዲሞላ” ነበረ። ገባችሁ? አሁን የእባቡ “ዘር” ምን እንደሆነ አታዩም? ምድርን የሞላው ምንድን ነው? ተረድታችኋል? እሺ። አሁን ሰይጣን ሔዋንን እንዴት እንዳገኛት ታያላችሁ። ለዚህ ነው ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሞት በምድር ላይ የነገሠው። እንዲሁም ሰማያት፡ ምድር፡ እውሬ፡ አትሞስፌር፡ ሁሉም በእርሱ ምክንያት በእግዚአብሔር የተረገሙ ናቸው። እርግማኑ ያ ነው፡ ምክንያቱም ሰይጣን አስቀድሞ ወደዚህች ደረሰ።

468 ኢየሱስ ወደ አብ ሊዋጃት መጣ። ይህንን ለማድረግ፡ የእርሰዋ አካል ሆነ፥ አሁን እንዳሳየኋችሁ ነው። ከዚያውም ራሱ አፈር፡ ኢየሱስ ራሱ፡ ከነበረው ክፍል፡ በመዋጀቱ፥ በእርሱ በኩል የእግዚአብሔር መገለጫዎች ሁሉ ከምድር ጋር ተዋጅተዋል።

469 እርሱ የተነገረው ቃል ነበረ። እኛ የተዋጀነው የእርሱ አካል ነን። እንግዲያውስ፡ ማወቅ ከቻላችሁ! አያችሁ?

470 ፈሪሳውያን ነን ይሉ ነበር። ነገር ግን፡ የመጀመሪያ ምሳሌዬን አያችሁ፡ እነርሱ ያ የነበሩት በአእምሮ እውቀት ብቻ ነበር። ቃሉ ልክ በፊታቸው ሲገለጥ ማወቅ አልቻሉም። “ይህ ሰው ርኩስ መንፈስ አለበት፡” አሉ።

471 አሁን፡ ዛሬ፡ እኛ ሐሰተኛ ነቢያት ተብለናል። በሐይማኖተኛ ሰዎች፡ አያችሁ፡ በታላላቅና ተሰጥኦ ባላቸው ሰዎች ሊባል የሚችለውን፡ ቆሻሻ ነገር ሁሉ ተብለናል። አያችሁ፡ ዝም ብለው አይገባቸውም። አያችሁ?

472 የውኃ ጥምቀቷ እርሰዋን ለማንጻት በቂ አልነበረም፥ የእነርሱም በቂ አይደለም። በደሙ፡ መቀደሷ፡ መለሳት፡ የራሱ አደረጋት። ልክ ሙሽራይቱን

እንዳነጻት፥ የእሳት ጥምቀቱ ግን አነጻት። ልክ እንደ መጽደቅ፡ መቀደስ፡ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት።

473 እንደነገርኳችሁ፡ አዲስ ዘርን አስነሳለሁ ብሎ ተስፋ አልሰጠም፡ ነገር ግን የወደቁትን ሊዋጅ ተስፋ ሰጥቷል። አ—አስቀድመው የተወሰኑት፡ ቃል እንደገባው ይወርሱታል። እርሱም የማይለወጥ እግዚአብሔር ነው፥ ያንን እናውቃለን።

474 አስታውሱ፡ ከንጥቀት በኋላ፡ እግዚአብሔር ኤልያስን በመውሰድ፡ በሕዝቡ መካከል የነቢይነት ስፍራውን እንዲይዝ፡ ዳግም ወደ እነርሱ መለሰው፥ በቅርቡም ይህንኑ ያደርጋል። እነዚህን ሃያ-አምስት መቶ ዓመታት፡ በሕይወት፡ አቆየው። እንደገና ሊገለጥ ነው።

475 እንደገና አስተውሉ፡ ሙሴን ከሙታን አስነሳው። መቃብሩ የት ነው? ማንም ሊያገኘው ይችላልን? የይሁዳን መልእክት አንብቡ። አያችሁ? የመላእክት አለቃው፡ የመላእክት አለቃው፡ ከሰይጣን ጋር፡ ስለ ሙሴ ሥጋ፡ በተከራከረ ጊዜ፡ "ደፍ... ጌታ ይገስጽህ፡" አለው። እዚህም ጴጥሮስ፡ ያዕቆብና ዮሐንስ እዚያ ቆመው እየተመለከቱት ነበር፡ በመገለጥ ተራራ ላይ፡ ልክ እዚያ ሊኖሩባት ተራራው በሚነሳበት ምድር ላይ። አያችሁ?

እርሱም ሊዋጃት መጣ።

476 አያችሁ፡ በዚያን ጊዜ የተነጠቀችው ቤተክርስቲያን፡ ተወክላ ነበረች፥ ያንቀላፉትም፡ ተወክለው ነበር። የት ቦታ? [ወንድም ብራንሃም በሚቀጥሉት ጥቂት አንቀጾች በጥቁር ሰሌዳ ላይ በሥዕል አሳየ—እርታዒ።] በከተማይቱ ውስጥ፥ በተራራው ጫፍ ላይ። አያችሁ?

477 ጴጥሮስ፡ ያዕቆብና፡ ዮሐንስ፡ እየተመለከቱ ነበር፥ ሦስት፡ ምስክር። እንደ ሰማያዊ ምስክር፥ ኤልያስ፡ ሙሴና፡ ኢየሱስ ነበሩ። አያችሁ?

478 የሞተውና ከሙታን የተነሳውም፡ ሙሴ በዚያ ነበረ። በህይወት የነበረው፡ የንጥቀት ምሳሌ፡ ኤልያስም ነበረ። ሁለቱም በዚህ በተቀደሰው ተራራ ላይ ተወክለው ነበር።

479 አዳኙ፡ ኢየሱስም፡ ነበረ። እግዚአብሔር፡ ከበላዩ **እንደዚህ**፡ በጋረደው ጊዜ፡ "የምወደው ልጄ ይህ ነው፡" አለ።

480 ታስታውሳላችሁ፡ ኢየሱስ፡ ከዚያ ከአንድ ቀን በፊት ሲናገር፡ እንዲህ አለ፡ "እውነት እላችኋለሁ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት በኃይል ተመስርታ እስኪያዩ ድረስ፡ ሞትን የማይቀምሱ አሁን እዚህ ከቆሙት አንዳንዶቹ አሉ" ብሎ ነበር።

481 ምን ነብ እር? ከሞት የተነሱትና የተነጠቁት ቅዱሳን፡ በአንድነት፡ እርሱን በአየር ላይ ለመቀበል አብረው ተነጠቁ። እግዚአብሔር ከላይ ሲጋርደው፡ ኢየሱስም በዚህ ጥላ ስር ቆሞ ሳለ፡ "በእርሱ ደስ የሚለኝ፡ የምወደው ልጄ ይህ ነው፡" ሲል፡ ያ የአዲሲቱ መንግሥት ሥርዓት ነበር። ኦህ፡ ወንድሜ፡ እህቴ!

482 ሞት አይለውጣችሁም። ሞት የሚለውጠው የመኖሪያ ስፍራችሁን ብቻ ነው። አያችሁ?

483 አስታውሱ፡ ሳሙኤል ሞቶ፡ ለሁለት ዓመታት ተቀብሮ በነበረበት ጊዜ፡ በገነት ውስጥ ነበረ። የዓይንዶርዋ ጠንቋይም አስጠራችው፡ ሳኦልም አወቀው፡ እርሷም፡ ደግሞ አውቃው፡ በግንባርዋ ተደፋች። እርሱ ቅንጣት ታክል እንኳ፡

አልተለወጠም ነበር። ሞቶ ከሁለት ዓመት በኋላም ያው ሳሙኤል ነበረ፡ አሁንም ነቢይ ነበረ። "ነገ በጦርነት ትወድቃለህ፡ ልጅህም ከአንተ ጋር፡ ነገ በዚህ ሰዓትም ከእኔ ጋር ትሆናላችሁ፡" አለው። ልክ እንደዚያውም ሆነ።

484 አያችሁ? ለራእይ 11፡ ሙሴና፡ ኤልያስ ሲመለሱ፡ አሁንም ነቢያት ይሆናሉ። ሃሌሉያ!

485 በዚያ ማዶ፡ በዚያች አገር፡ በጉ ብርሃንዋ በሆነባት ከተማ ውስጥ፡ ወንድም ማኪኒ፡ ያኔ አውቅሃለሁ። ሕዝቤ ሆይ፡ የዘውዴ ዕንቁዎች፡ አውቃችኋለሁ። ከምስራቅና ከምዕራብ፡ ወደ ከተማይቱ ሲመጡ፥ ርዝመቷና ስፋቷ ሺህ አምስት መቶ ማይል ሲሆን፡ አራት ማዕዘን ሆና የተሠራችው ያቺ ከተማ፡ በዚያ ትቀመጣለች። እግዚአብሔር በተራራው ላይ፡ ኢየሱስም በዙፋኑ ላይ በሚቀመጡበት፡ በዚያ በተቀደሰው ተራራ ላይ ትቀመጣላችሁ። ዮሴፍ በገነት ውስጥ ሊመላለስ ሲወጣ፡ የወርቅ መለከት ሲነፋ፡ የእግዚአብሔር ልጆችም እንደዳኑ አውቀው፡ በጉልበታቸው ተንበርክከው ያመልኩታል። አያችሁ? አሜን! ሃሌሉያ!

> አንዳንዴ ሰማይን ናፍቃለሁ፡
> በዚያም የማየውን ክብር፥
> አዳኜን ሳየው ምንኛ ደስታ ይሆናል፡
> በዚያች ውብ የወርቅ ከተማ!
>
> ወደዚያች ውብ ከተማ እየተጓዝኩ ነው
> ጌታ ወዳዘጋጀት... [በካሴቱ ላይ ባዶ ቦታ አለ—
> አርታዒ።]

486 ኢሳይያስ፡ በኢሳይያስ 9፥6 ላይ እንዲህ አለ፡ "ለእድገቱና ለሰላሙም ፍጻሜ የለውም። አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል፥ ስሙም ድንቅ መካሪ፡ የሰላም አለቃ፡ ኃያል አምላክ፡ የዘላለም አባት ተብሎ ይጠራል። አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል፥ ለእድገቱና ለሰላሙም ፍጻሜ የለውም።" እንስሳት እንኳ በዚያ ይሆናሉ። ኦህ፡ ማይ!

> ድቡ ገር ይሆናል፡ ተኩላውም ይገራል፥
> አንበሳውም ከበጉ ጋር ይተኛል፡
> ከጫካ የወጣ አውሬ፡ በሕፃን ይመራል፥
> ግን እለወጣለሁ፡ አሁን ካለሁበት ተፈጥሮ እለወጣለሁ።

487 ያ ቀን ሲመጣ፡ ወደዚያች ከተማ እሄዳለሁና። ወደዚያች ውብ ከተማ እየተጓዝኩ ነው! አሁን የሚቤዠው ኃይል በሙሉ ልቤ ይሰማኛል።

488 ይህ እንደዚህ ካልሆነ፡ ህይወቴን በከንቱ አጥፍቻለሁ፥ ለሌሎችም አሳሳች ነገሮችን አስተምሬያለሁ። ነገር ግን ለዚህ ዘመን የሰጠውን ተስፋ ስመለከት፡ እና የጸና መሆኑንም ሳየው፥ እንዲሁም ይህ የአንድ-ሺህ-አምስት-መቶ ስኩዌር ማይል ጉባኤ ሳይ፡ ከየሐይማኖት ተቋማት ከዘሮች እና ከየሐይማኖት መግለጫዎችና ከሌሎችም ነገሮች ተጠርተው፡ በአንድ ላይ የተሰበሰቡትን ምርጦች ስመለከት፥ ቃሉ እራሱን ሲያጸና ሳየው፡ ያለ አንዳች የጥርጣሬ ጥላ፡ በዚያ ቀን የዘውዴ እንቊዎች፡ በዓለም ላይ ካሉ ነገሮች ሁሉ አብልጠው እንደሚያንጸባርቁ፡ አውቃለሁ።

489 ጊዜው ይመጣል! ሰዎች፡ እዚህ የምንሰበሰበው በከንቱ አይደለም። ያንን ጊዜ ብቻ እየጠበቅን ነው። በጣም፡ በጣም ረፍዷል፡ ዳሩ ግን ኢየሱስ አሁንም በጣም፡ በጣም ቅርብ ነው። እና፡ ክብሩም፡ ድንቅ ነው። “ስሙም መካሪ ተብሎ ይጠራል።” ያቺን ከተማ፡ ልታዩዋት ትችላላችሁን? ሙሽራይቱና ሙሽራው የሚሰፍሩባት፡ ዳግመኛም የማይ...

490 አሁን፡ በመቶዎች የሚቆጠሩ ማይሎችን አሽከርክረን እዚህ ለመቀመጥና ቃሉን ለመመገብ ስንመጣ ድንቅ እንደሆነ ካሰባችሁ፡ ይህም ጥላ ብቻ ሆኖ ሳለ፡ ከእርሱ ጋር በከተማይቱ ውስጥ ስንኖር ምን ይመስል ይሆን! ጎረቤታችሁ ሆኜ ከእናንተ-አጠገብ ስኖር፡ ከእነዚያ ዛፎች ስንበላ፡ በእነዚያም መንገዶች ላይ ስንመላለስ፡ በእነዚያ የወርቅ መንገዶች ላይ ወደ ምንጩ ስንሄድ፡ ከምንጩም ስንጠጣ፡ መላእክት በምድር ላይ እያንዣበቡ፡ መዝሙራትን እየዘመሩ፡ ወደ እግዚአብሔር ገነቶች ስንገባ፡ ኦህ፡ ያ ቀን ምንኛ ድንቅ ቀን ይሆናል! ሁሉንም ይክሳል። መንገዱ ሻካራ ይመስላል፡ አንዳንዴም ይከብዳል፡ ነገር ግን፡ ኦህ፡ እርሱን ሳየው በጣም ትንሽ ይሆንልኛል፡ በጣም ትንሽ። ሰዎች የተናገሩብን መጥፎ ስሞችና ነገሮች፡ በእግዚአብሔር ውብ፡ ውብ በሆነችው ከተማ ውስጥ እርሱን ሳየው ምን ይሆኑ ይሆን?

491 አንገታችንን ዝቅ እናድርግ።

ለውቧ ከተማ ተመድቤአለሁ
የራሱ ለሆኑት ጌታዬ ያዘጋጃት፡
በዘመናት የተዋጁ ሁሉ
በነጩ ዙፋን ዙሪያ “ክብር!” የሚዘምሩባት።
አንዳንድ ጊዜ የሰማይ ቤቴ ትናፍቀኛለች፡
ክብሩንም በዚያ አያለሁ፥
አዳኜን ሳየው እንዴት ያለ ደስታ ይሆናል፡
በዚያች ውብ የወርቅ ከተማ!

492 በፍጥሞ ደሴት፡ ዮሐንስ አያት!

493 የተወደድክ ኢየሱስ ሆይ፡ ይህ ተስፋ፡ ተስፋዬ ከዚህ ባነሰ ነገር ላይ አልተገነባም፡ ጌታ ሆይ። ታላቁ ንጉሥ ሆይ፡ የልቤ እናት፡ ያቺ ከተማ ናት። አምላክ ሆይ፡ እባክህ፡ ከዚህ ውስጥ ማንም እንዲጠፋ አታድርግ። የጌታን መምጣት እየጠበቅን፡ ዛሬ፡ ህይወታችንን ዳግመኛ እንድንመረምር አድርገን፡ ጌታ ሆይ። እነዚያ ክርስቲያኖች በአንበሶች በተበሉበት፡ በዚያ፡ በታላቁ የሮም ኮሎሲየም ውስጥ ያሉት፡ የተበገኙት ሁሉ፡ አንድ ቀን አፈሩ ፈንድቶ ይወጣል!

494 በክብር ኮረብታዎች ላይ የመቃብር ስፍራዎች አይኖሩም። በየትኛውም የበር እጀታ ላይ የሐዘን ጉንጉን አበባ ከቶ አይንጠለጠልም። በእርሱ ላይ እንባ አይንጠባጠብም። አይ፡ አይ። የተቆለለ-አፈር አይኖርም። ማዕበልም አይመታውም። በዚያ ሁሉም የተሞላ ክብር ይሆናል።

495 እርዳን፡ ጌታ ሆይ። እዚህ... ለዚህ ለበጉ የሰርግ እራት፥ ለዚህ ሺህ ዓመት የሚሊኒየም ግዛት፡ የጫጉላ ጊዜው ካለቀ በኋላ ወደ ከተማይቱ ለመግባት የተጠሩትን አግዛቸው። ሚሊኒየሙ የጫጉላ ጊዜ ብቻ ነው። ከዚያም እርሷ፡ ሙሽራይቱ፡ የእርሱን... ሙሽራው ሙሽራይቱን ወደ ቤቱ ይወስዳታል። የእርሷ

ነው። ሙሽራዋ፥ የራሱ ሙሽራ። ኦህ፡ ከታጨበት ጊዜ ጀምሮ፡ ቤት ሊያዘጋጅ ሄዷል።

496 ቃል ለሆነው ለእርሱ ታማኞች እንድንሆን አድርገን፡ እርሱ ቃል ነውና። ሌሎች ምንም ያህል እኛን ለማንቋሸሽ ቢሞክሩ፡ ከእርሱም ሊያርቁን ቢሞክሩ፥ ጌታ ሆይ፡ ወደ አንተ አቅርበን።

> እንዳንድ ጊዜ የሰማይ ቤቴ ትናፍቀኛለች፡
> ክብሩንም በዚያ እያለሁ፥
> አዳኜን ሳየው እንዴት ያለ ደስታ ይሆናል፡
> በዚያች ውብ የወርቅ ከተማ!

497 የሙሽራውና የሙሽራይቱ የወደፊት መኖሪያ! እርሱ እየተመለሰ ነው... [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ አለ—አርታዒ።]... ወደ ሰርጉ እራት፥ ለሦስት ቀን ተኩል ይሆናል። ከዚያም በሚሊኒየሙ፡ በጫጉላ ጊዜያችን ዳግመኛ እንመለሳለን። ከዚያም እ—እርሱ ከተማይቱን ወደ እይታ ሊያመጣት ነው። ሙሽራው ሙሽራይቱን ሳርፕራይዝ ሊያደርጋት እንደሚወስዳት፡ ያቺ ትንሽ ሙሽራ የወደፊት ቤቷን ስትመለከት እንዴት በድንጋጤ ትቆም ይሆን! በእምነትም፡ ዛሬ፡ ጌታ ሆይ፡ በዚያ ማዶ እናየዋለን። ልክ እዚህ ምድር ላይ ይሆናል። አንተ ቃል ገብተሃል።

498 ከእነዚህ ቀናት በአንዱ፡ ቤተክርስቲያንህ ሙሉ በሙሉ ትቤዣለች። ከዚያም ዓለምህ፡ የተቀሩትም ቅንጣቶች ይዋጃሉ። በመጀመሪያ ግን ከዓለም የተሰራውን ሥጋቸውን፡ ህዝብህን ዋጅተሃል።

499 እግዚአብሔር ሆይ፡ እርዳን። ስለዚያ በትክክል እርግጠኛ ያልሆነ ሰው ቢኖር፡ ጌታ ሆይ፡ አሁን ይቀበሉት።

500 ረጅምና ሞቃታማ እንደነበር አውቃለሁ፡ ነገር ግን፡ ሰዎች፡ ሁልጊዜ እዚህ አንቆምም። ሁልጊዜ እረኛችሁ አልሆንም። ግልጽ እናድርገው።

"ወንድም ብራንሐም፡ መንገድ አለ?"

501 አዎ፡ የቃሉ አካል ሁኑ፡ የዛሬው ቃል አካል። የሙሴ ዘመን ቃል አካል መሆን አይቻልም፥ ያ ክፍል ተሰርቶ አልቋል፡ ያኛው እግር ነበር። አሁን እኛ ራስ ላይ ነን። ይህ ክርስቶስ ነው። ወደ ኋላ በሉተር ዘመን እንደነበረው፡ የእጆች ዘመን አይደለም፡ በጭራሽ። ይህ የራስ ጊዜ ነው። ክርስቶስ፡ የማዕዘን ራስ፡ ወደ አካሉ ይመጣል።

502 ስለ አቋምህ ሙሉ በሙሉ እርግጠኛ ካልሆንክ፡ ባለህበት ቦታ ሆነህ እንዳይህ ብቻ፡ እጅህን ታነሳለህ? ሌሎች ሁሉ ራሳቸውን ዝቅ ያድርጉ። እግዚአብሔር ይባርካችሁ።

503 እንዲህ በሉ፡ "ወንድም ብራንሐም፡ በጸሎት አስበኝ። እዚያ መገኘት በጣም እፈልጋለሁ! እ—እንዳያመልጠኝ አልፈልግም፡ ወንድም ብራንሐም። እ—እየፈተሸኩ ነው፡ የምችለውን ሁሉ እያደረግሁ ነው፡ ነገር ግን አሁን ጸልይልኝ፡ ትጸልይልኛለህን?" እግዚአብሔር ይባርካችሁ።

504 አሁን ስለእርሱ እያሰባችሁ ሳላችሁ፡ ዝም ብላችሁ ጸልዩ፡ እንዲህ በሉ፡ "አምላክ ሆይ..." በራሳችሁ ልብ ውስጥ ነው። እያችሁ፡ በልባችሁ ውስጥ

የሚጎትት፡ የሚኮረኩር ነገር ከተሰማችሁ፡ ያ ነው። ያ ባሕርይ ራሱን ለማሳየት እየሞከረ ነው።

ለውቧ ከተማ ተመድቤአለሁ
ለእርሱ ለሆኑት ጌታዬ ያዘጋጃት፥
በዘመናት የተዋጁ ሁሉ
በነጩ ዙፋን ዙሪያ "ክብር!" የሚዘምሩባት።
አንዳንድ ጊዜ የሰማይ ቤቴ ትናፍቀኛለች፡
ክብሩንም በዚያ እያለሁ፥
አዳኜን ሳየው እንዴት ያለ ደስታ ይሆናል፡
በዚያ ውብ የወርቅ ከተማ!

505 የሰማይ አባት ሆይ፡ አሁን ተቀበለን፡ ጌታ ሆይ። ክብር ትቶ የወረደው፡ ታላቁ እረኛ፡ ታላቁ ቤዛ የሆነው እረኛ፡ ከመገለጫዎቹ መካከል የሆኑት አንዳንዶች በታላቁ ሸለቆዎች መጥፋታቸውን፡ በዚያም ትንሿን በግ ሊውጡ የተዘጋጁ ተኩላዎቹ እና አ—አውሬዎች መኖራቸውን ስላወቀ፥ እርሱ ወርቃማ ኮሪደሮቹን ትቶ፡ ወደ ምድር ወርዶ ከእኛ አንዱ ሆነ፡ ስለዚህም የእግዚአብሔርን ፍቅር ለእኛ ሊገልጥልን ቻለ። በዚያም አገኛቸው፡ አንዳንዶቹን በየሐይማኖት ተቋማት ውስጥ፡ አንዳንዶቹን በመጥፎ ስም ቤቶች ውስጥ፡ አንዳንዶቹን በጎዳናዎች ላይ፡ ዕውር ሆነው፡ አንዳንዶቹን በአጥርና በአውራ ጎዳናዎች ውስጥ አገኛቸው፡ ነገር ግን አብ እንዲበዙ አስቀድሞ የወሰናቸውን ሁሉ ዋጃቸው።

506 ይህንን የቃሉን አካል ለዘመናችን እንድንኖር፡ አዘዘን። በዚያ ዘመን የነበረውን፡ የሉተርን ታላቅ የተሃድሶ እናያለን፡ የዌስሊን፥ እንዲሁም የጴንጤቆስጤን። አሁን የከተማይቱን የማዕዘን ራስ እየተጠባበቅን ነው። ኦ አምላክ ሆይ፡ ለዚህ ዘመን የተሰጠንን ዘመንና ተሰፋ እናውቃለን፡ ይህ እንዴት ዳግመኛ እንደሚመለስ እናውቃለን። "የምሽቱ ብርሃን ፍሬዋን ያበሰላታል። እነሆም እንዲህ ይሆናል ቀንም ሆነ ሌሊት የማይሆን ቀን ይመጣል፡ እንደዚያም ሊባል ይችላል፡ ሲመሽ ግን ብርሃን ይሆናል።"

507 ያው የከበረው የእግዚአብሔር ልጅ እዚህ ምድር ላይ በሰው ሥጋ ተገልጦ፡ የፈሪሳውያንን፡ የሰዱቃውያንን የሄሮድሳውያንንና የመሳሰሉትን ዓይኖች አሳውሮ፡ ተሰፋው ራሱን በትክክል እንዲኖር አደረገው።

508 ዛሬም ይደገማል፥ ቃሉ ልክ እንደነበረው እየተገለጠ ነው። ቃሉ፡ የልብን ሚስጥር በማወቅ፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንደተናገረው፡ ሊሻር በማይችለው መልኩ፡ ልክ እንደነበረው ሆኖ እየተገለጠ ነው። እግዚአብሔር ሆይ፡ ይህን እንድናስተውል፡ እርዳን።

509 አሁን እጃቸውን ያነሱትን እነዚህን እርዳቸው። ትንሽ ጠበቅ አድርገው ይታጠቁ፥ የሰላምን ወንጌል ጫማ ያድርጉ፥ ሙሉውን የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ይልበሱ፥ የራስ ቁሩን ወደ ታች ይጎትቱ፥ የእምነትን ጋሻ ያንሱ፥ ከዛሬ ጀምሮ፡ ወደፊት ይገስግሱ። ይሁንልን፡ ጌታ ሆይ።

510 ከጥቂት ጊዜ በኋላ፡ እንጠራለን፡ ከዚያም ንጥቀት ይመጣል። ልክ እንደ ሄኖክ፡ ትንሽዬ ቡድን፡ ወደ ላይ ይወሰዳል።

511 ከዚያም፡ “የእግዚአብሔርን ትእዛዛት የሚጠብቁ፡ የሴቲቱ ዘር ቅሬታዎች፡” አይሁዶች፡ “የኢየሱስ ክርስቶስ ምስክር ያላቸው፡” አህዛብ፡ እንደ ውሻ ይታደናሉ፡ “ስለ ምስክርነታቸውም ህይወታቸውን ይሰጣሉ።”

512 ከዚያም፡ በአንድ ታላቅ ጧት፡ የሚሊኒየሙ መባቻ፡ የ—የጫጉላው ጊዜ ይጀምራል።

513 “ከዚያም የቀሩት ሙታን ሺህ ዓመት እስኪፈጸም ድረስ በህይወት አልኖሩም።” ከዚያም፡ በሺህ ዓመቱ መጨረሻ ላይ፡ ፍርድ ነበረ፡ ይህም ካም በመርከቧ ውስጥ እንደነበረ የሚያሳይ ነበር። ካም አሁንም በቅሬታው ውስጥ በዚያ አለ። የሰሙትና የጠሉት ሊፈረድባቸው ግድ ነው።

514 አሁን፡ ጌታ ሆይ፡ በሰርጉ እራት ጥሪ ውስጥ እንጂ፡ በእነርሱ መካከል እንዳንቆጠር ይሁንልን። ምክንያቱም፡ ዛሬ ኢየሱስ በመካከላችን እንዳለ እናውቃለንና። ከእርሱ ጋር እንገባለን፥ ከዓለም ወጥተን፡ ወደ እርሱ። ወደዚያች ከተማ ወደፊት እንራመድ፥ ከእርሱ ጋር እንውጣ።

515 እያረጀሁ ነው፡ ጌታ ሆይ። ብዙ የምሰብካቸው ሰብከቶች አልቀሩኝም። ነገር ግን በእርግጥ በአንተ ታምኛለሁ። አባቴ አብርሃም እንዳደረገው፡ ያቺን ከተማ እየተጠባበቅኩ ነው። በውስጤ እየመጣች እንደሆነ የሚነግረኝ አንዳች ነገር አለ። ጌታ ሆይ፡ ብርሃኑን ለማስራጨትና እነርሱን ለመጥራት፡ በየቦታው እየሞከርኩ ነው። ጌታ ሆይ፡ ከእነዚህ ውስጥ አንዱ እንኳ...

516 ከጥቂት ጊዜ በፊት፡ ያንን እንዴት በሚያምር ሁኔታ፡ ገለጥክልኝ። አንድ ሺህ አምስት መቶ ማይል ያህል ዙሪያ ካለው ሰፋት፡ **ከዚህም ከዚያም** ብቻ፡ ያቺ ከተማ እስክትገለጥ እየጠበቁ፡ ዛሬ ወደ አንድ ትንሽ ሰፍራ፡ በአንድነት ተሰብሰበዋል። እኛ እንግዶችና መጻተኞች እንደሆንን እንመስክራለን። የተገለልን ነን። አህዛብ፡ ዓለም፡ ይስቁብናል ያፌዙብናልም፥ የሐይማኖት ተቋማት ያንቋሽሹናል፥ እኛ ግን በእንደዚህ ዓይነት ነገሮች አንናወጥም። የቃሉ አካል አድርገን፡ ጌታ ሆይ፡ የማንናወጥ አድርገን። “በመጨረሻው ዘመን እንዲህ ይሆናል።” ጌታ ሆይ፡ እኛ እንሁን፡ በእነርሱ መካከል የምንቆጠር እንሁን። በኢየሱስ ሰም እንጠይቅሃለን። አሜን።

517 ታምናላችሁ? እጃችንን **እንደዚህ** ከፍ እናድርግ።

ለውቧ ከተማ ተመድቤአለሁ
ለእርሱ ለሆኑት ጌታዬ ያዘጋጃት፥
በዘመናት የተዋጁ ሁሉ
በነጩ ዙፋን ዙሪያ “ክብር!” የሚዘምሩባት።
አንዳንድ ጊዜ የሰማይ ቤቴ ትናፍቀኛለች፡
ክብሩንም በዚያ አያለሁ፥
ኦህ፡ አዳኜን ሳየው እንዴት ያለ ደስታ ይሆናል፡
በዚያ ውብ የወርቅ ከተማ!

518 አሁን፡ በዚያች ከተማ ውስጥ አብረን የምንኖር ከሆነ፡ ዝም ብላችሁ ከአንድ ሰው ጋር ተጨባበጡና፡ እንዲህ በሉት፡ “እግዚአብሔር ይባርክህ፡ መንገደኛ። ከየት ነህ? ከሉዊዚያና፡ ጆርጂያ፡ ሚሲሲፒ? እኔም መንገደኛ ነኝ። ያቺን ከተማ እየተጠባበቅኩ ነው” በሉት።

519 ያቺን ከተማ እየተጠባበቅኩ ነው፡ ወንድም ኔቪል፡ በዚያ ማዶ። እዚያ ማዶ እየደረስን ነው... ? ... ወንድም ካፕስ፡ አሁንም፡ ዛሬ ማታ፡ ያቺን ከተማ እየተጠባበቅኩ ነው።

ክብሩንም በዚያ አያለሁ፥
አዳኜን ሳየው እንዴት ያለ ደስታ ይሆናል፡
በዚያች ውብ የወርቅ ከተማ!

ኦህ፡ ድቡ ገር ይሆናል፡ ተኩላውም ይገራል፥
አንበሳውም ከበጉ ጋር ይተኛል፡ ኦህ፡ አዎን፥
አውሬውም ከ... በህጻን ይመራል፥
እለወጣለሁ፡ አሁን ካለሁበት ፍጥረት እለወጣለሁ፡ ኦህ፡ አዎ።

ኦህ፡ አንድ ቀን በሸለቆው ውስጥ ለእኔ ሰላም ይሆናል፥
ኦህ፡ በሸለቆው ውስጥ ለእኔ ሰላም ይሆናል... (ልክ ነው! አዎ!)
ከእንግዲህ ሀዘን አይኖርም፡ ከእንግዲህ ትካዜ አይኖርም፡ ከእንግዲህ የማየው መከራ አይኖርም፥
በሸለቆውም ውስጥ ለእኔ ሰላም ይሆናል!

520 ዛሬ ጧት፡ የማይታየው ንጉሣችን ይገለጣል። ያኔ ቢል ዳውችን ዘጠና ዓመት ሆኖት አላየውም። እኔንም አምሳ ዓመት እንደሞላኝ አታዩኝም። ነገር ግን በዚያ ቀን፡ እለወጣለሁ።

የዱር አውሬም፡ በህጻን ሲመራ፥
እለወጣለሁ፡ አሁን ካለሁበት ፍጥረት እለወጣለሁ።

521 ደስ አይላችሁምን? ሸበቶች ይጠፋሉ፥ የጎበጡ ትከሻዎችም ይቃናሉ። ነገር ግን የማይሞት፡ ውበት፡ በእርሱ አምሳያ ይቆማል፡ ፀሐይን ያሰንቃል። ኦህ፡ ድንቅ ነው!

... ለእኔ፡ ኦህ፡ ጌታ ሆይ፡ እማጸናለሁ፥
ከእንግዲህ ትካዜ አይኖርም፡ ከእንግዲህ ሀዘን አይኖርም፡ ከእንግዲህ የማየው መከራ አይኖርም፥
በሸለቆውም ውስጥ ለእኔ ሰላም ይሆናል።

522 እዚህ የተገኘነው ለዚህ ነው። ከእናንተ መካከል ለጉዞው ጥንካሬ የሚፈልግ ስንቱ ነው? እግዚአብሔር ይስጠን! በሰውነታችሁ የታመማችሁ፡ የቆሰላችሁ ወታደሮች ስንት ናችሁ? አሥራ ሁለት፡ ወይም ከዚያ በላይ ይሆናል። የማይታየው ንጉሥ፡ እርሱ እዚህ እንዳለ ታምናላችሁ? የሚታዩ ነገሮች፥ የማይታዩት በሚታየው በኩል ይገለጣሉ። አካላዊ ሰውነቱን ካልሆነ በቀር፡ ትናንትና፡ ዛሬ፡ እስከ ዘላለምም ያው ነው። አሁን፡ በእኔ በኩል ይህንን የሰበከው የእርሱ መንፈስ ከሆነ፡ እርሱ እዚህ በነበረበት ጊዜ ያደረጋቸውን ሰራዎች ያደርጋል። ኦህ፡ ምንኛ ድንቅ ነው!

ወደ ተሰፋይቱ ምድር እየተጓዝኩ ነው፡
ወደ ተሰፋይቱ ምድር እየተጓዝኩ ነው፥
ኦህ ከእኔ ጋር አብሮ የሚመጣ ማነው?

ወደ ተስፋይቱ ምድር እየተጓዝኩ ነው።

በተዘረጉ ሰፊ ሜዳዎች ሁሉ
ዘላለማዊ ቀን ያበራል፥
እግዚአብሔር ወልድ ለዘላለም ይነግሳል፡
ሌሊቱንም ያሰወግዳል።

ኦህ፥ ወደ ተሰፋይቱ ምድር እገባለሁ፡
ወደ ተሰፋይቱ ምድር እገባለሁ፥
ኦህ ከእኔ ጋር አብሮ የሚመጣ ማነው?
ወደ ተሰፋይቱ ምድር እገባለሁ።

523 በዚያ ማዶ አምሰት መቶ ሰዎች ወደ ወንዙ ሲገቡ፡ የጌታ መልአክ በሲና ተራራ ላይ እንዳደረገው፡ እርሱን እንዳገኘሁት ለማረጋገጥ፡ በሚታይ ሁኔታ ሲገለጥ፡ ያ የመጀመሪያው ቀን ነበር። ወደ ወንዙ ገባሁ፡ በመቶዎች የሚቆጠሩትም ለጥምቀት ያንኑ መዝሙር እየዘመሩ ነበር። በዚያ ፎቶ ላይ የምታዩት ያው የብርሃን አምድ፡ ወደ ታች እየወረደ፡ መጣ፥ ወደ ታች እየወረደ፡ ልክ እዚህ ወንዙ ላይ ወርዶ፡ እንዲህ አለ፡ “መጥምቁ ዮሐንስ ለመጀመሪያው መምጣቱ መንገድ ጠራጊ ሆኖ እንደተላከ፡ ይህ መልእክትም ለሁለተኛው መምጣት መንገድ ጠራጊ ይሆናል” አለ። አያችሁ? ይሄውና፡ አያችሁ።

ኦህ ከእኔ ጋር የሚሄድ ማን ነው?
ወደ ተሰፋይቱ ምድር እገባለሁ።

524 ያው የብርሃን አምድ እዚህ ከእኛ ጋር አለ። ይህን ታውቃላችሁ? አንዳንዶቻችንን ለአንድ ነገር ፈጥሮናል፥ አንዳንዶቻችንን ደግሞ ለሌላ ነገር። በህንፃው መካከል እንዳለ፡ ያለ አንዳች ጥርጥር፡ ካመናችሁ፡ ራሱን ለእናንተ እንደሚያረጋግጥ አምናለሁ። ያረካችኋልን? ወደ እያንዳንዳችሁ ካልደረስኩ... ወደ ሁለት ሰዓት እየተቃረበ ነው፡ ነገር ግን እናንተ... ይልቁንም፡ ከሰባት ሰዓት ጥቂት አልፏል። ካመናችሁ፡ በእኛ ላይ ይውረድ! እምነታችን የት አለ? አያችሁ፡ ያንን ማመን አለባችሁ። ቅንጣት ታክል፡ ካልተጠራጠራችሁ፡ ይሰራል።

525 ቃ—ቃል የሆነውን፡ የክርሰቶሰን መለኮታዊ ህልውና አውቃለሁ። መጽሐፍ ቅዱሰም፡ “ቃሉ... በሁለት በኩል ከተሳለ ሰይፍ ይልቅ ኃያል ነው፡ እሰከ አጥንት ቅልጥም ድረሰ ይቆርጣል፡ በ—በልብ ውሰጥ ያለውንም ሀሳብ ይመረምራል፡ የልብንም ሚሰጥር ይገልጣል” ይላል።

526 ተመልከቱ። ምክንያቱም፡ ከዓመታት በፊት፡ እነዚያን ነገሮች አላውቅም ነበር። ሳላውቅም፡ ሰናገረው፡ ያደረገውን ተመልከቱ። እርሱ፡ “አሁን ሰዎችን በእጃቸው ትይዛቸዋለህ፡ ምንም ነገር አታሰብ፡ የተነገረህን ባሕርይ ብቻ ተናገር። እጢ ነው በል፡ ምንም ይሁን ምን” አለ። ከዚያም፡ “ያንን ማድረግ የማያሰፈልግህ ጊዜ ይመጣል” አለ። አያችሁ? አያችሁ? “በእነርሱ ውሰጥ ያለውን ነገር ራሱ ይለያል።” ሁሉንም ዓይነት ማሰመሰሎች አይተናል፡ ያንን እናውቃለን፡ ቢቻል የተመረጡትን እንኳ እሰከ ማሳት ድረሰ። የቀረው ነገር ከቃሉ ጋር እንዴት እንደሚሄድ ተመልከቱ፡ ከዚያም ትክክል መሆኑን ወይም አለመሆኑን ታውቃላችሁ። ነገር ግን፡ አሁንም፡ ኢየሱሰ ትናንትና፡ ዛሬ፡ እሰከ ዘላለምም ያው ነው።

527 እዚህ ውስጥ የታመማችሁ፡ የማላውቃችሁ ሰንቶቻችሁ ናችሁ? እጃችሁን አውጡና፡ “እ—እንደማታውቀኝ አውቃለሁ፡” በሉ። ኦህ፡ በሁሉም ቦታ፡ ያለ፡ ይመስለኛል። ማድረግ ያለባችሁ ብቸኛው ነገር ማመን ብቻ ነው።

እመን ብቻ፡ እመን ብቻ፡
ሁሉም ነገር ይቻላል፡ እመን ብቻ፥
እመን ብቻ፡ እመን ብቻ፡
ሁሉም ነገር ይቻላል፡ እመን ብቻ።

528 ኢየሱስ፡ “በሰዶም ዘመን እንደነበረ፡ የሰው ልጅ በመጨረሻው ቀን በምድር ላይ ሲገለጥ እንዲሁ ይሆናል። የሰው ልጅ ሲገለጥ፡ ወይም፡ በመጨረሻው ቀን ራሱን ሲገልጥ” አለ። አሁን፡ በቀደሙት ዘመን አይደለም፡ በመካከለኛው ዘመን አይደለም፥ በመጨረሻው ዘመን፡ እያችሁ፡ ይገልጣል። አሁን ደግሞ በመጨረሻው ዘመን ውስጥ ነን። የሰዶም አቀማመጥ ልክ በትክክል ነው፡ ሁሉም ነገር፡ መልእክተኞቹ፡ ልክ አንድ ዓይነት ናቸው።

529 ከአብርሃም ቡድን ጋር ተጠርታ ለነበረችው ለ—ለትንሿ ቅሬታ ምን ሆነ? አንድ አካል በሰው ሥጋ፡ በመካከላቸው መጣ፥ በሰው ሥጋ ተወክሎ፥ ከእነርሱ ጋር እየበላ፡ ከእነርሱ ጋር እየጠጣ፡ እነርሱ የሚበሉትን ያንኑ ምግብ እየበላ፡ ሁሉንም ነገር እያደረገ ነበር። በመካከላቸው ቆሞ፡ መልእክቱን ተናገረ። ከዚያም፡ “ይህንን ታላቅ ነገር ላደርግ ነው” አለ።

530 አብርሃምም እንዲህ እያለ ማሰላሰሉን ቀጠለ፡ “ይህ ነው እንዴ? ከተማ ሰጠባበቅ ነበር። ንጉሡ ይህ ነው? ”

531 እርሱም፡ እሷ ድንኳን ውስጥ ከኋላው ሆና፡ “ሳራ ይህንን ለምን ተጠራጠረች፡” አለ?

532 የሳራን ሀሳብ፡ ስለመረመረ፡ “ጌታ አምላክ፡ ኤሎሂም!” አለ አብራሃም።

533 የማዕዘን ራስ ወደ አካሉ ሲመጣ፡ በመጨረሻው ቀን ሲገለጥ ይህ ዳግመኛ እንደሚደገም ኢየሱስ ተናግሮ ነበር። ሊቤዥ... የራሱን ሊወስድ የሚመጣው፡ እርሱ የተቤዠው ነው። እርሱ ከእኛ ጋር እዚህ አለ።

534 አሁን፡ እጃቸውን ያወጡት ወደ አሥራ ሁለት ገደማ፡ ወይም ከዚያ በላይ፡ የሚሆኑ ብቻ ናቸው። ግዚአብሔር እያንዳንዳችሁን ሊፈውሳችሁ እንደሚችል አምናለሁ። በትክክል። እንደምትፈወሱም አምናለሁ። በእንደዚህ ዓይነት ጊዜና በእንደዚህ ዓይነት ድባብ ውስጥ... አንድ ሰው አንዳች ነገር ሳያውቅና፡ ሳይረዳ፡ በእንደዚህ ዓይነት ሰፍራ ውስጥ፡ ዝም ብሎ መቀመጥ ይችላል ብዬ አላምንም።

535 እንድትጸልዩ እፈልጋለሁ። ህመማችሁ ምን እንደሆነ፡ በ—በ—በልባችሁ እንድትይዙ እፈልጋለሁ፡ እያችሁ፡ ከዚያም መጸለይ ጀምሩ፡ እንዲህ በሉት፡ “ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ ይህንን ግለጥ። ም—ምን እንደሚያመኝ እየነገርኩህ ነው። አሁን ደግሞ አንተ ወንድም ብራንሐም እውነት ነው ብሎ የተናገረውን ለመፈጸም፡ ዛሬ ስለ አንተ በተናገረው በዚህ መልእክት ውስጥ፡ መንፈስ ቅዱስህን ወደ እርሱ ላክ፡ እውነት እንደሆነ አውቃለሁ። አሁን፡ ግለጥልኝ፡ ጌታ ሆይ። ተናገረኝ” በሉ።

536 አሁን እዚህም እዚያም፡ ተበታትኗል። ስለዚህ ዝም ብላችሁ ጸልዩ፡ እግዚአብሔርም እንደሚያደርገው፡ በሙሉ ልባችሁ እመኑ።

537 አሁን እኔን እንድትመለከቱኝና፡ እንድትጸልዩ እፈልጋለሁ። ጴጥሮስና ዮሐንስ፡ "ወደ እኛ ተመልከት" እንዳሉት። እርሱ አንዳች ነገር ይፈልግ ነበር፡ ሊቀበልም ተዘጋጅቷል። እናንተም አንዳች ነገር ትፈልጋላችሁ፡ ልትቀበሉም እንደተዘጋጃችሁ አምናለሁ። "ወደ እኛ ተመልከት፡" አለው።

538 እርሱም፡ "ብርና ወርቅ፡ የለኝም፥ ነገር ግን ያለኝን፡ ይህንን እሰጥሃለሁ" አለው።

539 አሁን፡ ፈውስ፡ ምንም የለኝም። ያ ሁሉ በክርስቶስ ውስጥ ነው። ነገር ግን ያለኝን፡ የእግዚአብሔርን ስጦታ፡ እርሱን እንድታምኑ፡ እምነትን እሰጣችኋለሁ። አሁን፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ እያንዳንዳችሁ ተፈወሱ። እመኑ። አያችሁ? "ብታምን!"

540 እዚያ የተቀመጠችው ሴት፡ እኔን እየተመለከተችኝ ነው። ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት፡ እያለቀሰች፡ ስትጸልይ ነበር። የሚያስቸግራት የታይሮይድ ህመም አለባት። አላውቅሽም። ለእኔ እንግዳ ነሽ። ያ እውነት ነው፡ አይደል እንዴ። [እህትየዋ፡ "ልክ ነው" አለች።—አርታዒ።] የዚህ አካባቢ ሰው አይደለሽም። ከቺካጎ ነሽ። ወይዘሮ አሌክሳንደር። ያ ልክ ከሆነ፡ እጅሽን አውለብልቢ። አሁን ተፈውሰሽ ወደ ቺካጎ ተመለሺ።

541 እርሷ ምን ነካች? ያቺ ደም ይፈሳት የነበረችው ሴት የነካችውን ያንኑ ነገር ነው፡ የልብሱን ጫፍ፡ የእኔን አይደለም።

542 እዚህ ህዝቡ መካከል የተቀመጠች አንዲት ምስኪን ሴት አለች፡ እንድትረዳኝ ማድረግ ከቻልኩ እንይ። ራስሽን ወደ ጎን ያዞርሽው። አላውቅሽም። ለእኔ እንግዳ ነሽ፡ ነገር ግን በሆድ ህመም እየተሰቃየሽ ነው። ባልሽ ከአንቺ አጠገብ ተቀምጧል። በጆሮው ላይ አንዳች ችግር አለበት። ስምሽ ዛፕ ነው። ለእኔ እንግዶች ናችሁ። የዚህ አካባቢ አይደላችሁም። ከሚቺጋን ናችሁ። ልክ ነው፡ እጃችሁን አውለብልቡ። በሰላም፡ ወደ ሚቺጋን ተመለሱ። እምነታችሁ አድኗችኋል። "ብታምኑ፡ ሁሉ ይቻላል።"

543 እዚያ ጋር የጉሮሮ ህመም ያለባት ምስኪን ሴት፡ እዚሁ ጫፍ ላይ የተቀመጠች፡ ከጆርጂያ የመጣች፡ ነጭ የለበሰች። ተፈውሰሻል፡ ወደ ጆርጂያ፡ ተመለሽ። ኢየሱስ ክርስቶስ ይፈውስሻል። ታምኚያለሽ?

544 እዚያ የተቀመጠችው ሴት፡ እኔን እየተመለከተች፡ ልክ በወንበሩ ጫፍ ላይ ያለችው። የሳይነስ ህመም አለባት። ካመነች፡ እግዚአብሔር ይፈውሳታል። ወይዘሮ ብራውን፡ በሙሉ ልብሽ እመኚ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ... ለእኔ እንግዳ ነሽ፡ ነገር ግን እሱ ያውቅሻል። እ-ህ። ታምኚያለሽ? እጅሽን ከፍ አድርጊ። በትክክል።

545 እዚህ አልጋ ላይ የተኛችው። ወደዚህ እንድትመለከት ንገሯት። እየተሰቃየች ነበር፡ አሁንም እየቀጠለ ነው። ልፈውሳት ብችል ኖሮ፡ አደርገው ነበር፡ ወዳጄ። መፈወስ አልችልም። እርሷ የዚህ አካባቢ ሰው አይደለችም፥ ከሩቅ ነው የመጣችው። ከሚዞሪ ነሽ። ህመሞችሽ የውስጥ ናቸው። ነገር ግን በሙሉ ልብሽ ካመንሽናል ካልተጠራጠርሽ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ሊፈውስሽ ይችላል፥

ተፈውሰሽም፡ ወደ ሚዙሪ በመመለስ፡ ምስክርነትሽን መስጠት ትችያለሽ። ታምኚያለሽ? እንግዲያውስ ተቀበይው፡ አልጋሽን ይዘሽ፡ ወደ ቤትሽ ሂጂ። ኢየሱስ ክርስቶስ ይፈውስሻል።

546 ታምናላችሁ? ይህ የዘላለሙ ንጉሥ መገኘቱ መለያ ያ ነው። አሁን በሙሉ ልባችሁ፡ ታምናላችሁ? አሁን፡ በእርግጥም በዚህ ህንፃ ውስጥ፡ ክብ ስርቷል። በሙሉ ልባችሁ ታምናላችሁ? በህልውናው ውስጥ እንዳላችሁ ታምናላችሁ?

547 አሁን፡ ከዚህ መንግሥት ልዑካን አንዱ እንደሆናችሁ ታምናላችሁ፡ ትቀበላላችሁም? እጃችሁን አውጡ። ኢየሱስ፡ "ያመኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሏቸዋል። በድውዮች ላይ እጃቸውን ይጭናሉ፡ እነርሱም ይድናሉ" ብሏል። እኛ እርስ በርሳችን ነን፥ እናንተ የእኔ አካል ናችሁ፡ እኔም የእናንተ አካል ነኝ፥ ሁላችንም የክርስቶስ አካል ነን። አሁን፡ በአንድነት፡ እጃችንን እርስ በርሳችን ላይ እንጫን።

548 እዚሁ ጋር፡ በአልጋ ላይ የነበረችው ሴት ተነስታለች፡ እየተንቀሳቀሰች ነው፡ ተፈውሳ ወደ ቤቷ እየተመለሰች ነው። አሜን።

549 ብታምኑ፡ እናንተ፡ እያንዳንዳችሁ፡ ተፈውሳችኋል። አሁን እጃችሁን እርስ በርሳችሁ ጫኑ፡ እናንተም የዚህ የክርስቶስ አካል ናችሁ። እጃችሁን ለጫናችሁበት ሰው፡ ልክ በምትፈልጉት መንገድ ጸልዩለት።

550 ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ እዚህ እንዳለህ እናውቃለን። አንተ ንጉሣችን ነህ፥ በመካከላችን ራስህን ገልጠሃል። ስለዚህ ህልውና እናመሰግንሃለን። እንዲሁም፡ ጌታ ሆይ፡ "ይህንን ተራራ፡ 'ተነቀል' ብትሉት፡ ሳትጠራጠሩ፥ የተናገራችሁት እንደሚሆን ብታምኑ፡ ይሆንላችኋል፡ የተናገራችሁትን ማግኘት ትችላላችሁ" ብለሃል።

551 እንግዲያውስ፡ ለዚህ ትእዛዝ በመታዘዝ፡ ሊወድቅ ለማይችለው ለእግዚአብሔር ቃል በመታዘዝ፡ ከከተማይቱ አሥራ አምስት መቶ ማይል ስኩዌር ሰፍራ የመጣን፡ የአንተው ልዑካንህ በመሆን፡ ለተሸነፈው ዲያቢሎስ፡ ለሰይጣን፡ "ፍጻሜህ መቃጠል ነው። እኛ አራት ማዕዘን ከሆነችው ከተማ የመጣን ልዑካን ነን፡ በጉ ብርሃንዋ ከሆነባት ከተማ። እኛ ኢየሱስ ክርስቶስ በጸጋው ቤዛ ያደረገው፡ የተገለጠው የሁሉን ቻይ የእግዚአብሔር ባሕርይ ነን" እንለዋለን።

552 አንተ ሰይጣን፡ ውጣ፡ እዚህ ያለውንም እያንዳንዱን በሽተኛ ልቀቅ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም። ቃሉን ስላመኑና የእግዚአብሔር ሀሳብ ባሕርያት ስለሆኑ፡ የተዋጁት የተቀደሱ እጆች፡ አሁን እነዚያ እጆች እርስ በርሳቸው ላይ ተጭነዋል። ከእንግዲህ ልትይዛቸው አትችልም። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ውጣ!

553 አሁን፡ በጌታ በኢየሱስ ስም፡ አሁን፡ እርሱ እዚህ አለ። ቃሉ እርሱ እዚህ እንዳለ ይናገራል። መገኘታችሁና እምነታችሁ፡ እናንተ፡ ከልዑካኑ አንዱ እንደሆናችሁ ይናገራል። ልናሳየው በምንችለው በእያንዳንዱ መልክዓ ምድራዊ መለኪያ እንኳ፡ ልክ ነው። እናንተ የተዋጃችሁ የእግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶች ልጆች እንደሆናችሁ መገንዘብ ትችላላችሁን? **ይህ** ቤታችሁ እንደሆነ ታውቃላችሁ? የምትሄዱት **እዚህ** ነው።

554 እዚህ የመጣችሁትም ለዚህ ነው፡ ወደ ክርስቶስ የመጣችሁት ለዚህ ነው፡ ቃሉን እየተመገባችሁ ነው። በተገለጠው የእርሱ ባሕርያት ብቻ፡ እዚህ፡ እንደዚህ ዓይነት ጊዜ ሊኖራችሁ ከቻለ፡ ወደ ህልውናው ስንገባ ምን ይመስል ይሆን? ኦህ፡ ድንቅ ይሆናል! እያንዳንዳችሁ በሽተኛውን የመፈወስ፡ በበሽተኛው ላይ እጃችሁን የመጫን መብት አላችሁ። እያንዳንዳችሁ የማጥመቅ መብት አላችሁ።

555 በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ያልተጠመቀ ሰው እዚህ ካለ፡ የጥምቀት ገንዳው ክፍት ነው።

556 ያው ነው ልትደርሱበት የምትችሉት ብቸኛው መንገድ፥ ኧ-ህ፡ ልክ ነው፡ እያንዳንዱን ቃል መታዘዝ ነው። አስታውሱ፡ በመጀመሪያ፡ የቃሉ አንድ ትንሽ ክፍል መለወጥ፡ በምድር ላይ ላለው ኃጢአት ሁሉ ምክንያት ሆኗል። ኢየሱስ፡ "ከዚህ አንድ ቃል የሚያጎድል፡ ወይም በእርሱ ላይ አንድ ቃል የሚጨምር ማንም ቢሆን፡ አይገባም" ብሏል። ይህንን እንዳደረገ ወዲያውኑ፡ ሰሙ ከህይወት መጽሐፍ ይሰረዛል።

557 በቤተክርስቲያን ውስጥ፡ ከኢየሱስ ክርስቶስ ስም ውጪ በሌላ መንገድ ማንም ሰው የተጠመቀበት ቦታ፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የለም። በዚያ መንገድ ካልተጠመቃችሁ፡ ብታደርጉት ይሻላል።

558 "ኦህ፡" "ምንም ለውጥ አያመጣም፡" ትላላችሁ። ለሔዋን አምጥቶባታል።

559 ሰይጣን እንዲህ አላት፡ "ኦህ፡ በእርግጥ፡ እግዚአብሔር፡ እግዚአብሔር እንደሚያውቅ ታውቂያለሽ... " እርሱ ግን፡ አደረገው። እንዲህ ብሏልና።

560 የመንግሥተ ሰማያትን ቁልፎች ለጴጥሮስ ሰጠው፡ በጴንጤቆስጤ የታሰረው ደግሞ ለዘላለም የታሰረ ነው። ሙሽራይቱ ዳግመኛ ለእይታ-የቀረበችበት ምክንያት ይህ ነው፡ ለሁለተኛ ጊዜ፥ ልክ በመጀመሪያው ቀን እንደነበረው ሁሉ፡ በመጨረሻውም ቀን የተጠራች ቤተክርስቲያን መኖር አለባት፡ ልክ በትክክል። ዛፉ ከስሩ ተነስቶ፡ ወደ ሙሽራይቱ ዛፍ ደርሷል፡ በዚያን ጊዜ እንዳደረገው፥ ከሁለት እሁዶች በፊት እንዳልኩት፡ ወደ ከተማይቱ እንድትወስድ እንደገና፡ የእግዚአብሔር አውራ ሆናለች።

እግዚአብሔር ይባርካችሁ። "አሁን እምናለሁ።"

561 ሰይጣን ተሸንፏል። ያውቃል። በምድር ላይ ነው፡ እንደሚያገሳ አንበሳ እየዞረ ነው። እስኪያበቃለት ድረስ፡ ኦህ፡ ብዙም አልቀረውም። ጊዜውን ያውቃል። እንደሚያገሳ አንበሳ እየዞረ ነው።

562 ነገር ግን፡ አስታውሱ፡ የሰላም አለቃ በአጠገባችን ቆሟል፥ ታላቁ መለኮታዊው። የማንነቴ አርክቴክት፡ እኔን አሁን የሆንኩትን አድርጎ የሠራኝና፡ እናንተንም አሁን የሆናችሁትን አድርጎ የሠራው አርክቴክት እዚህ አለ። ህንፃው በትክክለኛው ቦታ፡ እንዴት እንደሚገጣጠም የሚያውቀው፡ አርክቴክት ነው፡ ከአርክቴክቱ በተሻለ ማን ያውቃል? እርሱም እዚህ እንዳለ፡ ራሱን ሊያረጋግጥ፡ እዚህ አለ።

563 አሁን እርሱ የተመሰረተው በእምነታችሁ ላይ ነው። እመኑ፡ ብቻ እመኑ! ኧ-ህ።

ለውቧ ከተማ ተመድቤአለሁ
የራሱ ለሆኑት ጌታዬ ያዘጋጃት፡
በዘመናት የተዋጁ ሁሉ
በነጩ ዙፋን ዙሪያ “ክብር!” የሚዘምሩባት።
አንዳንድ ጊዜ የሰማይ ቤቴ ትናፍቀኛለች፡ (ይህ ሁሉ ሲያበቃ!)
ክብሩንም በዚያ አያለሁ፥
አዳኜን ሳየው እንዴት ያለ ደስታ ይሆናል፡
በዚያች ውብ የወርቅ ከተማ!

564 አስታውሱ፡ በቤተክርስቲያን ውስጥ፡ ዛሬ ማታ የጌታ እራት ይሰጣሉ። አሁንም፡ እዚሁ ከተማ ውስጥ ካላችሁ፡ መምጣት ከፈለጋችሁ፡ እንድትገኙ እንፈልጋለን። አንድ ቀን፡ ከእርሱ ጋር ለምንበላው ነገር፡ መታሰቢያ ነው።

565 እወዳችኋለሁ። እንዴት እንደምገልጸው አላውቅም። የምድር ጨው እንደሆናችሁ አስባለሁ። በዓለም መካከል ያላችሁን ሥነ ምግባር እሰማለሁ፡ ከዚያም በእናንተ ላይ የበለጠ እምነት እንዲኖረኝ ያደርገኛል።

566 ዳሩ ግን፡ አስቡ፡ ይህቺ ትንሽ ቡድን፡ እንደዚህ የተዋበችው፡ ከእለታት በአንዱ ቀን፡ ትበተናለች። ስለዚህ እናልማለን። ነገር ግን ዳግመኛ ከመገናኘታችን በፊት ከመካከላችን አንድ ሰው ቢያልፍ፡ እኛ፥

ያኔ በማለዳው፡ በሚያበራው ወንዝ ዳርቻ አገኛችኋለሁ፡
ሀዘን ሁሉ ሲጠፋ፡
በሮቹ ሲከፈቱ፡ በበሩ አጠገብ እቆማለሁ፡
እጅግ አድካሚው፡ የህይወት ጉዞ ሲያበቃ።

ያኔ በማለዳው፡ በሚያበራው ወንዝ ዳርቻ አገኛችኋለሁ። (መሀል ላይ ጠፋብኝ።)
... በወንዙ ዳርቻ ደግሞም በንጥቀት የቀድሞውን ትውውቅ እናድሳለን፥

ያኔ አያችኋለሁ፡ አውቃችኋለሁ።

ያኔ በማለዳው፡ በምላበሰው ፈገግታ ታውቁኛላችሁ፡
ያኔ በማለዳው፡ በዚያች አራት ማዕዘን ሆና በተሰራችው፡ ከተማ አገኛችኋለሁ።

567 ትወዱታላችሁ? “እስክንገናኝ!” አሁን እንነሳ። **የኢየሱስን ስም ይዛችሁ ሂዱ**፡ ዜማውን ስጠን።

568 ትወዱታላችሁ? እርሱ ድንቅ አይደለምን? ይህ እውነት እንደሆነ ታምናላችሁ? በእግዚአብሔር ጸጋ፡ ወደዚያ እያቀናችሁ ነውን? እዚያ እስክንደርስ ድረስ፥

የኢየሱስ ስም ካንተ ጋር ውሰድ፡
ወጥመድ ሲኖር ይታደግሃል፥
ፈተና ሲበዛ ሁከት ሲሆን ዙርያህ፡
በጸሎት ቅዱስ ስሙን ተንፍስ።

ዳግመኛ እስክናያችሁ ድረስ፡ ልታደርጉት የሚገባው ይኸው ነው። መልካም።

የኢየሱስ ስም ካንተ ጋር ውሰድ፡
የሀዘንና... [አንድ ሰው እንዲህ አለ፡ “ዛሬ ማታ? ”—
አርታዒ።] (አይ።)
ደስታና መጽናናት ይሰጣል፡
በሄድክበት አትለየው።

ድንቅ ስም፡ ኦ ውብ ስም!
የምድር ተስፋ የሰማይ ደስታ፥
ድንቅ ስም፡ ኦህ ውብ ስም!
የምድር ተስፋ የሰማይ ደስታ።

569 አሁን፡ መልእክቴን አቋርጬ ማለፍ ነበረብኝ። አንድ ቀን፡ እግዚአብሔር ቢፈቅድ፡ ተመልሼ እነዚህን “ጎዳናዎችን” እወስዳቸዋለሁ፡ እንሰተንም፡ አያችሁ፡ ተጨማሪ ጊዜ ልናገኝ በምንችልበት ጊዜ እናያለን። በቂ ጊዜ አትቆይም ብላችሁ ስትጮኹ ነበር። ዛሬ ግን፡ ቆይተናል። ሞቃት ነው። ዳሩ ግን፡ አሁን፡ እግዚአብሔር ይባርካችሁ። ያንን ዝማሬ ወድጄዋለሁ።

570 በቀደም ምሽት የውጪውን ድምፅ ማጉያ ሲያጠፉት፡ አንድ ጎረቤት እዚህ፡ እንዲህ አለ፡ “መልእክቱን በጣም ወድጄዋለሁ፡ ነገር ግን ያንን ያማረ ዝማሬ፡ አያችሁ፡ በውጪ በኩል ለምን አጠፋችሁት፡” አለ? ስለዚህ፡ ጎረቤት፡ ዛሬ ጧት እያዳመጥክ ከሆነ፡ በጀፈርሰንቪል ውስጥ ከሁሉ የተሻሉ ጎረቤቶች ያሉን ይመስለኛል። መኪኖቻችንን በቤቶቻቸው ፊት ለፊትና በሌሎችም ቦታዎች እናቆማለን፥ ምንም አይሉም፥ ዝም ብለን እንቀጥላለን። ስለዚህ፡ አሁን እናመሰግናቸዋለን።

571 አቤት፡ እንዴት ድንቅ ነው! እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሁን።

... ድንቅ ስም፡ ኦህ ውብ ነው!
የምድር ተስፋ የሰማይ ደስታ።

እስክንገናኝ!

572 አንገታችንን ዝቅ እናድርግ። ፓስተሩ በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ፡ ያሰናብተናል። እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሁን!

... በኢየሱስ እግር ስር እንገናኛለን፥ (በታላቋ ከተማ፡
በዙፋኑ ላይ።)
እስክንገናኝ! እስክንገናኝ!
እስክንገናኝ እግዚአብሔር ከናንተ ጋር ይሁን...

64-0802 የሰማያዊው ሙሽራና የምድራዊቷ ሙሽሪት የወደፊት ቤት
ብራንሃም ተበርናክል
ጀፈርሰንቪል, ኢንዲያና ዩ.ኤስ.ኤ

AMHARIC

©2026 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰቢያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው®።

ለተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ቢፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

Voice Of God Recordings
P.O. Box 950, Jeffersonville, Indiana 47131 U.S.A.
www.branham.org